# የውጊያዎች ሁሉ አውራው ውጊያ

እናመሰግናለን፡ ወንድም ኦርማን። ጌታ ይባርክህ።

2 እንደምን አደራችሁ፡ ወገኖች። ዛሬ ጠዋትም እንደገና እዚህ በመገኘቴ ደስ ብሎኛል፡ ይመስለኛል፡ እኔም፡ ጉባኤውም፡ ያልጠበቅነው እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። አንድ ነገር እያነበብኩ ቆይቻለሁ... አመሰግናለሁ፡ የኔ እህት። ጌታም ትንሽ ነገር ለቤተ ክርስትያኑ እንዳመጣለት ፈልጎ፡ በልቤ ውስጥ የሞላኝ ይመስለኛል፡ ይህን ለማድረግም ጊዜው አሁን ነው። አሁንም...

3 ዛሬ እሁድ እዚህ እንደምንገኝ ሳላውቅ፡ እንደደረስኩ፡ ለቤተክርስቲያን መልእክት—እንዳለኝ አሳውቄያለሁ። እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው እሁድ፡ መልእክቱን ለማምጣት እፈልጋለሁ። ረዘም ያለ ጊዜ ይኖረናል፡ ስለዚህ፡ ምናልባት በዚያ ጊዜም፡ እስከ አሰራ-ሁለት ተኩል፡ እስከ አንድ ሰዓት ድረስ ላያልቅ ይችላል። በልቤ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቆይቷልና፡ እንደሚመስለኝም ለምን ረዘም ላለ ጊዜ ከአገልግሎት ርቄ እንደቆየሁ ለህዝቡ ማብራራት እንዳለብኝ አስባለሁ። በሰብከት መኃል ነካክቼዋለሁ፡ ይሁን እንጂ መውጣት ባለበት ሁኔታ ጎልቶ አልወጣም። ስለዚህ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው እሁድ፣ ጊዜ ወስጄ፡ ምክንያት እና ለምን የሚለውን፡ ቃሉን መሰረት ባደረገ መልኩ፡ ምን እየተካሄደ እንዳለ፡ እና፡ ይህ ሁሉ ለምን እንደሚሆን አሳውቃችኋለሁ። ምክንያቱ፡ ምናልባት ከዛ በኋላ ወድያውኑ ወደ መስክ እወጣለሁ። በምን መንገድ እንድሄድ እንደሚመራኝ ለማየት እየጠበቅኩ ነው። ባለፈው...

4 ከሁለት፡ ወይም ከሦስት ምሽቶች በፊት፡ ሆስፒታል ለገባች ሴት እንድጸልይ፡ ወደ እኩለ ሌሊት ገደማ ስልክ ተደውሎልኝ ነበር። ደውለው፡ “ጸልይላት፡” አሉኝ። የነገሩኝ ሰም አሁን... ረስቼዋለሁ፡ የቤተ ክርስትያን ታማኝ እህት፡ ደጓ ሴት፡ የጥቁሯ እህታችን፡ ወይዘሮ ጀምስ ቤል፡ ጓደኛዋ ናት አሉኝ። የነገሩኝ ስም፡ ሺፐርድ ይመስለኛል። ከአልጋዬ ወርጄ ተንበረከኩ፡ ለሚስቴም—ነገርኳት። ስልኩ ሲጮኽ፡ እሷንም ቀስቅሿት ነበርና። “ለወይዘሮ ሺፐርድ፡ መጸለይ አለብን፡ የደወለችው እህት፡ የወይዘሮ ጄምስ ቤል ጓደኛ ናት፡” አልኳት። ስለዚህ ጸለየንላት፡ ወደ መኝታችን ቤታችን ተመለስን።

5 በማግስቱ፡ አሰር ወይም አሰራ አንድ ሰአት ላይ፡ እንደገና ተደወለ። የደወለው ቢሊ ነበር። እርሱም፡ የወ/ሮ ቤል ጓደኛ፡ ወ/ሮ ሺፐርድ አይደለችም፡ ወ/ሮ ቤል ራሷ ናት፡ አለኝ። “ወ/ሮ ቤል፡ በከባድ ሁኔታ፡ ሆስፒታል ገብታለች።” ወደ ሆስፒታሉ ተቻኩዬ ወጣሁ፡ ይሁን እንጂ ጌታ ወደ ቤት ጠርቷታል። ስለዚህ ወ/ሮ ቤል፡ አረፈች።

6 ወ/ሮ ቤል፡ ለብዙ ዓመታት እዚህ ቤተ ክርስቲያን ከእኛ ጋር ታማኝ ተካፋይ ነበረች። ባለቤቷ፡ ጄምስ፡ እና እኔ፡ ከአባቴ ጋር፡ ከብዙ ዓመታት በፊት፡ እዚህ፡ አብረን፡ ሠርተናል... ከብዙ አመታት በፊት፡ ምናልባት ሠላሳ፡ ወይም ከዚያ በላይ፡ ከፐንሲልቫኒያ፡ ወደዚህ እስከ ኮልጌት ድረስ፡ እነዚህን ሃዲዶች ሰርተናል። እና እህት ቤል ደግ ሰው ነበረች። ሁላችንም እንወዳታለን።

7 ጊዜ የማይሰጥ የሐሞት ከረጢት ጥቃት እንደገጠማት ተረድቻለሁ፡ በሰዓቱ... ችግሯን በደንብ የሚያውቀው፡ ሐኪሟ፡ ከከተማ ውጪ ነበረ። አዲስ ሐኪም ሊያያት መጥቶ—የአደጋ ጊዜ ቀዶ ጥገና እንዲደረግላት አዘዘ፡ ልትተርፍ አልቻለችም። እና—የሷ... እንደሚመስለኝ... እኔ እንደገባኝ ከሆነ፡ መደበኛው ሐኪሟ ቢኖር—ቀዶ ጥገና አያዝላትም ነበር፡ ምክንያቱ ወፍራም-ናት ሐሞት ከረጢቷም ተጎድቷል። ይመስለኛል፡ በውስጡ እንደ ጠጠር፡ መሳይ ነገሮች ነበሩ፡ ጌታም—ምሕረቱን አግኖላታል። በፊትም በተደጋጋሚ እነዚያን ጥቃቶች ሲያጋጥሟት ቆይቶአል፡ ጌታ ግን ይፈውሳት ነበረ። አሁን ግን ይህ እንዲሆን ግድ ነበረ... እንደው፡ ሙሉውን በሚዛን ከለካነው፡ እንዲህ እንላለን፡ እግዚአብሔር እህት ቤልን ጠርቷታል፣ መሆን የነበረበትም በዚህ መንገድ ነው፡ አያችሁ።

8 እንዴት እንደሳታት እንጃ... ወደ ልቤ የመጣችው፡ ወይዘሮ... ሺፐርድ መሰላኛለች። ወይዘሮ ሺፐርድን አላውቃትም። ምናልባት፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ልትኖር ትችላለች፡ ምናልባትም ካየኋት የማውቃት ትሆናለች። ነገር ግን፡ የተባለው ወይዘሮ ሺፐርድ ነበር። ምናልባት ሁሉም እንደዚያ እንዲሆን፡ ተደርጎስ ቢሆን... በዚያ ሁኔታ ውስጥ የገባችው ወይዘሮ ቤል መሆኗን አውቄ ቢሆን ኖሮ፡ ምናልባት ወዲያውኑ ሄጄ ስለ እሷ እማልድ ነበር። አያችሁ፡ ምናልባት፡ እግዚአብሔርም፡ እንዳንሄድ፡ ፈልጎን ይሆናል። ስለዚህ፡ "እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።"

9 እህት ቤል ጌታችንን እንደምትወደው እርግጠኛ ነኝ። ጥሩ ሴት ነበረች። እሷ፡ በመካከላችን አንዷ ነች። በእኛ ዘንድም፡ የቀለም መለያየት የለም። የእግዚአብሄር ቤተሰቦች የቀለም ልዩነት አያስምሩምና። ቀይ ይሁን፣ ቡኒ፣ ጥቁር ወይም ቢጫ ብንሆን ነጭም፣ ምንም ለውጥ የለውም። ምንም ይሁን ምን እኛ በክርስቶስ ወንድም እና እህቶች ነን። ስለዚህ—እንወዳታለን። እንደ ጉባኤው፡ ሁላችንም ትናፍቀናለች። ከኋላ ጥግ ላይ፡ ደመቅ ያሉ፡ የእህት ቤል፡ ጎርናና፡ "አሜኖች" እጅግ ይናፍቁኛል። ወደ ቤት ስትሄድም፡ ስለ ጌታ ኢየሱስ ትናገራለች።

10 በትክክክል ከተረዳሁትም፡ እስከ ጥቂት ደቂቃዎች በፊት በፍጹም አላወቅኩም ነበር፡ ቀብሯ ግን እዚሁ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጸም ይመስለኛል። [ወንድም ኔቪል "ትክክል ነው፡" አለ።—አርታዒ።] የፊታችን ማክሰኞ ["አንድ ሰዓት።"] አንድ ሰዓት ላይ። ቀብር ሥነ ሥርዓቱን ማስፈጸም ያለብን እኔ እና አንተ ይመስለኛል። ["ትክክል ነው።"]

11 እንደው ግን፡ እንደ ጉባኤ፡ ዛሬ ማለዳ እንደ ደካሞች፡ አንገታችንን ዝቅ እንዳለ፡ እህታችን ቤል ለማክበር፡ ለአፍታ በእግራችን እንቆማለን።

12 ሕይወትን የሚሰጥ እና የሚነሣ፡ የሕይወት አምላክ፡ ብሏል ኢዮብ የኦሪቱ፦ "እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ፡ የጌታ ስም ይባረክ እንዳለ።" ከጥቂት አመታት በፊት፡ እህት ቤልን፡ በታላቁ በእግዚአብሔር የጋራችን መንግስት ዜጋ እንድትሆን፡ በመካከላችን የላክሃት አንተ ነህ። በመካከላችን ሳለች ስለነበራት መነቃቃት እናመሰግንሃለን፡ መዝሙር መዘመር እና መመስከር የምትወድ፡ እልል እያለች እስክትጮኽ ድረስ በመንፈስ የምትሞላ ነበረች። ለእሷ፡ ለማዳን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል፡ አታፍርም ነበር።

ዓመታቶቿ ሁሉ አስቆጥራለች፡ ሁላችንም መልስ የምንሰጥበት ጊዜ ግን ደረሰባት። አንተም በመገኘትህ ሥር እንድትሆን፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከእኛ ወሰደሃታል። ምክንያቱ፡ ከዚህ በተለየን ጊዜ፡ ወደ እግዚአብሔር መገኘት መሄዳችን፡ የማይቀር ነው።

13 አምላክ ሆይ፡ ስለ ሁሉም እናመሰግንሃለን። ባሏን ወዳጄን፡ ጄምስን እንድትባርከው እንጸልያለን፡ ወንድ ልጇ፡ ሴት ልጆቿ፡ እነዚያ ሁሉ ባርካቸው። ልጇ ጀርመን ካለበት ከጦር ሃይሎች፡ ስለ ሞተች እናቱ፡ በምድር ላይ፡ የመጨረሻውን ክብር ለመስጠት፡ በበረራ እየመጣ እንደሆነ፡ ሰምተናል። ዛሬ ጠዋት የዚያ ወጣት ልብ እንዴት እየተንቀጠቀጠ ይሆን። ጌታ ሆይ፡ ለእርሱም፡ እግዚአብሔር እንዲባርከው፡ እጸልያለሁ። እንደው፡ ቤተሰብ ለማስተዳደር... አድካሚ የስራ ሰዓታት ሲያሳልፍ፡ እየዋለሁና፡ ጂሚን ባርከው። ይህ ታላቅ ቤተሰብ እንዳይለያይ እጸልያለሁ፡ ከአድማስ ባሻገር ባለችው ምድር ግን የዚህ ቤተሰብ መንኮራኩር በጭራሽ የማትሰበር ትሆናለች።

14 ጌታ ሆይ፡ አሁን ዕቃ ጦሩን እና ጥሩሩን ትንሽ ጠበቅ አርገን፡ አጥብቀን፡ ከሳምንት በፊት ከነበረው ጦር የሚያንሰው ጋር ለመዋጋት፡ ወደ ስልፍ እንውጣ። እኛ ስንዋጋ እንድትረዳን፡ እንድትደግፈን እና እንድታበረታን አንድ ቀንም፡ ሁላችንም በአንድነት ከአድማስ ወዲያ ማዶ እንድንሰበሰብ እንጸልያለን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና። ኣሜን።

15 አሁን የተሰናበተችው የእህታችንን ነፍስ ይማር። የቀብርዋ ሥነ ሥርዓት—እሁድ ወይም ማክሰኞ፡ እዚህ እንደሚሰበክ ይህን ማሳሰብ እወዳለሁ፡ እንዲህ ይሆናል... መምጣት የሚፈልጉ ሁሉ እንዲመጡ እንጋብዛለን። ወንድም ኔቪል ዝግጅቶቹ አጠናቆ እንደያዘ እገምታለሁ፡ ዛሬ ነው ያዘጋጀሃቸው። እንግዲህ፡ አሁን፡ ዛሬም...

16 ከኋላ ለወንድም እና ለእህት ሰላውተር አንድ ቦታ ብታገኙላቸው። ኢያችሁ፡ በጣም እንኳል። እህት ሰላውተር፡ የሰልክ ጥሪሽ ደርሶኛ፡ ለሌዋ እህት ሰላውተር... በራቢት ፊሸር፡ በቱላረሚያ ለታመመችው ልጸልይ ወጥቼ ነበር። በእርግጠኝነት መጥፎ ደረጃ ላይ ደርሳ ነበር፡ ጤናማ እንደምትሆን ግን በእግዚአብሔር እንተማመናለን።

17 አሁን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት ከፍለን እናነባለን። ዛሬ ጠዋት፡ ጊዜ ወስጄ ማስተማር እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱ፡ ከአሪዞና ከተመለስኩ ጊዜ ጀምሮ፡ ጉሮሮዬ፡ ትንሽ አሞኛል።

18 እና አሁንም፡ የሚቀጥለውን እሁድ፡ እንዳትረሱት፡ ቢሊ—ማስታወቂያዎቹን አስቀድሞ በፖስታ የላከ ይመስለኛል። ረዘም ያለ ጉባኤ ይሆናል ብለን እናምናለን፡ ስለዚህ በተቻላችሁ መጠን አስቀድመው ኑ። ልክ ዘጠኝ-ተኩል፡ ወይም፡ አስር ሰዓት ማለቴ ነው፡ መጀመር እንፈልጋለን። እና ምናልባት፡ እስከ አንድ ወይም አንድ-... ምናልባት፡ አሥራ ሁለት-ተኩል፡ አንድ ሰዓት ድረስ፡ ሊቆይ ይችላል፡ ይህም፡ ሦስት ወይም አራት ሰዓት፡ ወይም ከዚያ በላይ፡ መጠቀም እፈልጋለሁ፡ ቃሉን ጽፉችሁ ያዙ። እርሳስ እና ወረቀት ይዛችሁ ኑና፡ በደንብ ያዙት። ጥያቄ ካላችሁ፡ አምጡ—ጠይቁ፡ ኢያችሁ፡ መርዳት የምንችለውን ያህል፡ ገለጻ ልናደርግ እንችላለን።

19 አሁን፡ ከሁሉ አስቀድመን፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት ቃላት እናንብብ። ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ ማንበብ የምፈልጋቸው ሦስት ቦታዎች አሉኝ። እና በመጀመሪያ አንደኛው፡ ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ እና እርሳስ ከያዛችሁ፣ ዛሬ ጥዋት መጥቀስ የምፈልጋቸው፣ በርካታ ጽሑፎች... ማለት፡ መጥቀስ የምፈልጋቸው፡ በርካታ ቅዱሳት ቃላት ይኖራሉ። የመጀመሪያው አንደኛ ጴጥሮስ 5:8-10፣ ኤፌሶን 6:10-17፣ እና ዳንኤል 12:1-14 ይሆናል። አሁን፡ በማንበብ፡ ጊዜአችን እንጠቀምበት።

20 ምናልባት፡ ከኋላ እና ጥቂት ከጎን የቆሙ ቢኖሩም። ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁሉም መቀመጫ አግኝቷል። ግን በተቻለ ፍጥነት ጨርሰን እናንተን ለመሸኘት እንሞክራለን፡ ከዚያ ለታመሙ እንፀልያለን።

21 ዛሬ ጠዋት አንዲት ምስኪን ሴት በጸና ታማ ተኝታለች። ትላንትና፡ በጸና ታምማ እንደቆየች አውቄአለሁ። ዛሬ ጠዋትም፡ ለእሷ ከመጸለዬ በፊት—መጀመርያ፡ እንድትሰማ፡ ፈልጌአታለሁ። በርግጥ ሴቲቱ ያለችበት ሁኔታ አውቃለሁ። በጣም ታማለች፡ ነገር ግን በሽታዎች ሁሉ ያሸነፈ ታላቅ የሰማይ አባት አለን። እና ትንሽ ነገር—ይዣለሁ...

22 ወይዘሮ ውድስ ታነበው እንደሆን ጠይቄአት ነበር፡ እሷ—እሷ ግን—ጊዜ አላገኘችም መሰለኝ። አንድ የህክምና ዶክተር የተገረመበት፡ ጽሑፍ ነው። በቢሮው ውስጥ ማንም በዚህ ርዕስ እንዲያወራ እስኪከለክል ድረስ፡ ሆኖ፡ መለኮታዊ ፈውስን የሚተች ሰው ነው፡ ነርሱም ያው ነች። እና፡ በካንሰር ህመም፡ በከባድ ካንሰር የታመመ፡ ታማሚ ይመጣል። ምንም ነገር መንካት ስላልፈለገ፡ ወደ ሌላ ሕክምና ላካት። እነርሱም ምንም መንካት ስላልፈለጉ፡ መልሰው ላኳት። ጡቷ ላይ ነው... አቤት፡ ከባድ ሁኔታ ላይ ነበረች፡ ቆዳዋ ሁሉ ተብልቷል። ስለዚህ እንዲህ አደረጉ። ካንሰሩ፡ ጡቷ አልፎ፡ ወደ ጎድን አጥንቷ ወርዷል። ምን ማለቴ እንደሆን የተረዳችሁ ይመስለኛል።

23 ዛሬ በመካከላችን የተገኘው ወዳጃችን የሆነውን ኖርዌያዊው ዶክተር አስመጡ።

24 እሱም መሳርያዎቹን ሁሉ አዘጋጀ፡ በቀዶ ጥገና ጡቷን እንዲያስወግድላት እንደጠየቀችው ተረድቷልና። እጅግ ከባድ ስራ ነበር። እና—እና እሽጎቹን በሙሉ፡ አስናዳ። ነርሷ ሴትዮዋን አዘጋጅታ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል አመጣቻት፡ ከዚያም ዶክተሩ እና ረዳቱ ጡቱን ለማስወገድ... የሚጠቀሙባቸው፡ መሳርያዎችን ለማምጣት ወደ ኋላ ተመልሳ ሄደች። ፎጣዎቹ እና ሌላ ነገሮች ሁሉ በእሷ ላይ አስነጥፈዋል። እናም ጀምሩ...

25 ወደ ኋላው ዞር ሲል፡ ባለቤቷ በክፍሉ ጥግ ላይ ቁጭ ብዬ መጸለይ እችላለሁ ወይ ብሎ ጠየቀ። የሆሊነስ ሰባኪ ነውና። በዚያም በአልጋው እግር አጠገብ ተቀምጦ፡ መጸለይ ጀመረ። እርግጥ ነው፡ እንደምታውቁት፡ እሱ በዚያ በመሆኑ ዶክተሩ ደስ አላለውም። ነገር ግን እስካላየና፡ እስካልሰቀጠጠው ድረስ፡ ያው፡ “ችግር ያለበት አይመስለኝም፡ ምንም—ምንም አይደለም።”

26 ተቀምጦ፡ ሲጸልይ ሳለ፡ በክፍሉ ውስጥ መንቀጥቀጥ መጣ። ሐኪሙም... ጡት ለማስወገድ፡ መሳርያዎቹ ብዙ እሽጎችን አምጥቶ። ወደ ኋላው ዞር ብሎ ተመለሰና። ጡቷ ላይ ጠባሳ እንኳን፡ ምንም ጠባሳ አልቀረም። እሱም “ምን ሆነ—ምንድነው... ለቆ ነው? ” አለ። ከዛ በኋላ እንዲህ ጀመረ...

ነርሷም ምስክርነቷን ሰጠች። ሁለቱም ወጥተው በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ጌታን እያገለገሉ ጴንጤቆስጤዎች ሆነዋል። ጠባሳ እንኳን አልቀረም!

27 ዶክተር ሆልብሩክ ራሱ፡ እንዲህ በማለት፡ መሰከረ፦ “ከአንድ ደቂቃ በፊት፡ ሴቲቱ—ተኝታ ነበረች፡ ነርሷም አጠገቧ፡ ከባድ እና ክፉ ካንሰር ጡቷ ላይ ክፉኛ ወጥቷል። ከአንድ ደቂቃ በኋላ፡ የለቀቀበት ጠባሳ እንኳን አልነበረም።” እዚህ አሜሪካ ውስጥ ካሉት ጥሩ የህክምና ባለሞያዎች አንዱ ነው። እዚያው እንዳለሁ ወድያው አመንኩ ብሏል። ይህ ሁሉ ሲሆን፡ ቤተ ክርስትያን ውስጥ፡ ዲያቆን የነበረ ነው። አያችሁ?

28 ሰዎች ስለ ቤተ ክርስትያን ሲያስቡ፡ መኬድ ያለበት ቦታ ይመስላቸዋል፡ “በቃ፡ መልካም ሰው ለመሆን፡ ወይም ሌላ ነገር ለመሆን የሚኬድበት፡” እኮ ነው። ወዳጆች ሆይ፡ አይደለም። አይደለም። አምላክ አምላክ ነው። ድሮ እንደነበረ፡ ዛሬም ታላቅ ነው። ወደ ፊትም ዘወትር ያው ሆኖ ይኖራል። እኛም… እንዲሁ እንወደዋለን።

29 እንግዲህ፡ አሁን ለመጀመር ያህል፡ ከአንደኛ ጴጥሮስ፡ 5ኛው ምዕራፍ፡ 8ኛ እና 10ኛ ቁጥር እናነባለን።

> **በመጠን ኑሩ፡… ንቁም፡ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ፡ የሚውጠውን ፈልጎ፡… እንደሚያገሣ አንበሳ፡ ይዞራልና፤**
>
> **በእምነት…** ጸንታችሁ **ተቃወሙት፡ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።**
>
> በክርስቶስ ኢየሱስ **ወደ ዘላለም ክብሩ** የጠራችሁ፡ **የጸጋ ሁሉ አምላክ፡ ለጥቂት ጊዜ መከራን** ከተቀበላችሁ **በኋላ፡ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፡** ያጸናችሁማል፡ ያበረታችኋል፡ **ያሳርፋችኋል።**

30 ኧረ እንደው እግዚአብሔር ይመስገን! አሁን የኤፌሶን መጽሐፍ። ወደ ኤፌሶን መጽሐፍ እንከፍታለን፣ 6ኛው ምዕራፍ፡ ከ10ኛው እስከ 17ኛው ቁጥር እናነባለን፡ ምልክት አድርጌበታለሁ።

> **በቀረውስ፡ ወንድሞች ሆይ፡ በጌታና በኃይሉ ችሎት፡ የበረታችሁ ሁኑ።**
>
> **የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።**
>
> **መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፡ ከአለቆችና፡ ከሥልጣናት ጋር፡ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር— በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።**
>
> **ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወ** እንድትችሉ፡ **ሁሉንም ፈጽማችሁ፡** ለመቆም፡… **የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።**
>
> **እንግዲህ፡ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ… የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፤**

**በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤**

**በሁሉም ላይ ጨምራችሁ... የሚነበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን; የእምነትን ጋሻ አንሡ።**

**የመዳንንም ራስ ቁር፡ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፡ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው፤**

31 አሁንም ከዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ፡ ተጨማሪ ማንበብ እፈልጋለሁ። አሁን፡ ዳንኤል ምዕራፍ 12። ከ1ኛ ላይ መጀመር እፈልጋለሁ፡ ከዚህ ክፍል፡ ረዘም አድርጌ—አስራ አራት ቁጥሮችን አነባለሁ።

**በዚያም ዘመን... ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው፡ ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፡ ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ... እስከዚያ ዘመን** ድረስ፡ **እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል፤ በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ፡ እያንዳንዱ ይድናል።**

**በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፡** እኩሌቶቹ **ወደ ዘላለም ሕይወት፡... እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ** ዘላለም ጉስቍልና።

**ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፡ ብዙ ሰዎችንም** ወደ—**ጽድቅ** የሚመልሱ **እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።**

**ዳንኤል ሆይ፡ አንተ ግን፡ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ፡ ቃሉን ዝጋ—መጽሐፉንም... አትም፤ ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ እውቀትም ይበዛል።**

እኔም **ዳንኤል፡ አየሁ፡ እነሆም፡ ሁለት ሌሎች ቆመው ነበር፡ ... አንዱ በዚህ በወንዙ ዳር፡ ሌላውም... በዚያ፡ በወንዙ ዳር።**

**አንዱም ከወንዙ ውኃ በላይ የነበረውን፡ በፍታም የለበሰውን፡ የዚህ ድንቅ ፍጻሜ እስከ መቼ ነው... አለው?**

**ከወንዙም ውኃ በላይ የነበረው፡ በፍታም የለበሰው ሰው፡ ቀኝና ግራ እጁን ወደ ሰማይ አንሥቶ፡ ለዘመንና፣** ለዘመናት፣ **ለዘመንም እኩሌታ ነው ብሎ ለዘላለም ሕያው ሆኖ** በሚኖረው **ማለ፤ የተቀደሰውም ሕዝብ ኃይል መበተን በተጨረሰ ጊዜ ይህ ሁሉ ይፈጸማል ብሎ፡... ለዘላለም ሕያው ሆኖ በሚኖረው ሲምል ሰማሁ።**

32 እዚህ ማቆም እንዳለብኝ አሰባለሁ። የዚህ ሁሉ ማጠቃለያ ለማውጣት፡ ከዚህ ውስጥ፡ ርዕስ ማውጣት ከተቻለ፡ አንድ ርዕስ እወስዳለሁ፡ **የውጊያዎች ሁሉ አውራው ውጊያ**። እንደ ርዕስ መጠቀም የፈለግኩት ይህ ነው።

33 አሁን፡ ለዛሬ ጠዋት ይህንን ርዕስ የመረጥኩበት ምክንያት፡ እኔ እና፡ የዚህ ቤተ ክርስትያን፡ ሁለት ባለአደራዎች፡ አሪዞና ነበርን፡ ገና መምጣታችን ነው። በእውነቱ ከሆነ፡ በፎኒክስ፡ ከወንድም ሻሪት ጋር፡ በቤተ ክርስትያኑ ጉባኤ ለማድረግ፡ ነበር የወጣነው። ነገር ግን አንድ ወንድም—በከተማው ውስጥ ድንኳን ተክሎ፡ ጉባኤ እያደረገ መሆንኑን በተረዳሁ ጊዜ፡ ወዲያው፡ ጉባኤ

ከማድረግ መቆጠብ እንዳለብኝ ተሰማኝ። ማናቸውም በቤተ ክርስቲያናቸው እንዳይረበሹ፡ ምናልባት እሁድ ከሰአት በኋላ አደርገዋለሁ ብዬ አሰብኩ። ነገር ግን፡ እሁድ ከሰአት በኋላም፡ አገልግሎት እንደነበረው፡ አወቅኩ። እና ለመሆኑ—ጉባኤ ይኖረን ይሆን ብዬ ተጨነቅኩ።

34 እኛም ወንድሞች፡ ቀኑን ሙሉ፡ አደን ወጥተን ከማሳለፍ ይልቅ፡ በደንብ ተዘጋጅተንበት፡ ወደ ከተማው ገባንና፡ ወደ ወንድም አለን አገልግሎት ሄድን። ወንድም ኤ. ኤ. አለን ጉባኤ ጠርቶ ነበርና። ስለዚህ ወደ አገልግሎቱ ሄድን፡ ወንድም አለንም ታላቅ ስብከት ሰበከ። በጣም ጥሩ—ጊዜ፡ ጥሩ ጊዜ ነበረ፡ ወንድም አለን፡ ዘማሪዎች—እና ሌሎች፡ እንዴት እንደሚዘምሩ፡ እንደሚጮኹ፡ እና ታላቅ አገልግሎት እንዳደረጉ፡ ሰማናቸው።

35 ከዚያም በመንገዱ ሁሉ፡ የጌታን እጅ፡ አይተናል። በሄድንበት ሁሉ፡ ጌታ ኢየሱስ ከእኛ ጋር ይገናኝ ነበር። ወደ ምድረ በዳ ብቻችሁ መራቅ፡ የተለየ ነገር አለው። እንዲሁ ብቻችሁን ስትወጡ፡ የሆነ የሚቀርባችሁ፡ የተለየ ነገር አለው። እንዲህ ያሉ ቦታዎች፡ ርቄ-መሄድን የምመርጠው፡ ለዚህ ይመስለኛል። እዚህ ኪሚሆነው በበለጠ፡ ከጠላት ኃይል እጅግ ትርቃላችሁ።

36 የሚሠራበት ነገር ከሌለው ሰይጣን ጉዳት አልባ ነው ማላት ይቻላል። ያኔ... ከሌጌዎን የተባረሩትን ሰይጣኖች ታስታውሳላችሁ? እነሱ... የከፋ ነገር ማድረግ ስለፈለጉ፡ ወደ አሳማዎቹ ውስጥ መግባት ፈለጉ። ስለዚህ አጋንንቶች፡ የሚሠሩበት ሰው፡ የሚሠሩበት አካል ያስፈልጋቸዋል።

37 እግዚአብሔርም፡ የሚያደርገው በዚህ መንገድ ነው። ስራውን እንዲሰራብን፡ በእኛ ላይ ይደገፋል። እኛን መያዝ አለበት።

38 በጉዞ ላይ ሳለን፡ ብዙዎች ሕልም ይዘው ይመጡ ነበር። ጌታ ኢየሱስም በጭራሽ አንድም ሳይሳሳት፡ ፍቺውን በትክክል ሰጣቸው፡ በትክክለኛው መንገድ።

39 ከዚያም ወደ ጨዋታው መራን፡ የት እንደሆነም በጥሩ ሁኔታ ነገረን። እና፡ ታውቃላችሁ፡ በዚያ ዓይነት ሁኔታ መሆን ብቻውን፡ እንዴት ያለ ድንቅ መሰላችሁ። ብዙ ማይሎች እና ማይሎች እና ማይሎች፡ ከማንም ርቀን፡ ሲመሽ፡ በካምፕፋየር ዙርያ፡ ተቀምጠን፡ የእሳቱን ነበልባል—ከዓለት ጠርዞች ላይ ሲብለጨለጭ እናያለን። አቤት፡ ኧረ፡ ልዩ ነበረ!

40 ከሚስቱ ጋር ችግር የነበረበት ወንድም እዛ ነበር፡ እንዲህ ነበር... ከብዙ ዓመታት በፊት፡ እኔ እያገለገልኩ፡ ጉባኤ ውስጥ ሚስቱ ራሷን ቀና አደረገች። ከመድረኩ ላይ ከአንዲት—ሴት አልወጣም ያለ ክፉ መንፈስ ስለነበረ፡ ሰውን ሁሉ ራሶቻቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ፡ ጠይቄአቸው ነበር። ሴትየዋ ግን፡ ክብር በጎደለው መልኩ፡ እንዲሁ ቀና ብላለች። መድረክ ላይ በሴቲቱ ውስጥ የነበረው መንፈስ፡ ወጥቶ፡ ወደሷ ገባ። ይህም ከአስራ አራት ዓመታት በፊት ነው፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሴቲቱ በከባድ ሁኔታ ትኖራለች፡ ከባድ ሁኔታ፡ በሰነ አእምሮም ሳይቀር፡ ልክ ያልሆኑ ነገሮ እስከማድረግ ደርሳለች። ለምሳሌ፡ ከባልዋ ጋር እየኖረች፡ ባልዋን ትታ ሌላ ሰው ጋር ተጋብታለች፡ ነገር ግን እንዲህ እንዳደረገች አላውቅም ብላለች። በዚህ—ምክንያት ምርመራ አድርገውላት ነበር... እንዲህ ሲገጥማችሁ... ምን ነበር የሚባለው፡ አምኔዥያ ነው? ይህ... ነው፡ ስሙን ማን እንደሆነ። ትክክል ነው ብዬ እገምታለሁ፡ ዶክተር። ያ ግን

አይደለም። መንፈስ ነው። እና... ሴትየዋ ጥሩ ወዳጄ ነበረች። ከዚያ ምሽት ጀምሮ ግን፡ ሆን ብላ፡ ጠላችኝ። እርግጥ ነው፡ ለምን እንደ ሆነ ይገባችኋል።

41 ባሏ ሲመጣ ግን፡ በክፍሉ ውስጥ ተንበርክከን ጸለይን፡ ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደ። በቃ። ከዚያም በዚያች ሌሊት ለባሏ በሕልም ተገለጠለት። ህልም ይዞ ተመለሰ፡ ቀልድ መስሎት ነበር። በኋላ ግን፡ የሚሰቱ ፈውስ መልሷ እንደሆነ አስተዋለ። አቤት የመንፈስ ቅዱስ አሰራር!

42 ከወንድም ኖርማን እና ከሌሎቹ ጋር፡ ወደ ቱሰን ወረድን፡ በዚያም ጌታ በታላላቅ እና በኃይል በሚገለጡ ነገሮች፡ እንደገና መስራት ጀመረ።

43 አንድ ምሽት፡ እዚህ መደምደሚያ ላይ እንድደርስ ያደረገኝ፡ ከወንድም ዉድ እና ከወንድም ሶትማን ጋር ቆሜ ነበር። በዚያ ሆነን... ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ገደማ ነበርና፡ ወደ ሰማይ ቀና ብዬ እየተመለከትኩኝ፡ ታላቅ መደነቅ በላዬ መጣ። እና እንዲህ አልኳቸው፡ "ይህ ሁሉ የሰማይ ሰራዊት! እሰኪ እዩት!" "ሁሉም በፍጹም ቅንጅት ውስጥ ናቸው፡" አልኳቸው።

44 ከዛ ወንድም ውድ እንዲህ አለ፦ "ሁለት ትንንሽ ኮከቦችን በጣም ተቀራርበው አያለሁ፡ ይህም፡ ብርሃን አሰመሰሏቸዋል።"

45 እኔም አልኩት፡ "ግን፡ ወንድም ዉድ ሆይ፡ እንደ ሳይንስ መሰረት፡ በዲፐሩ መካከል፡ በትንሹ ዲፐር፡ እና በትልቁ ዲፐር፡ ከሁለት ኢንች በላይ የሚራራቁ አይመስሉም፡ ይሁን እንጂ እኛ ከነርሱ ከራቅነው በበለጠ እርስ በእርስ እጅግ የተራራቁ ናቸው። በሰዓት በሺዎች በሚቆጠሩ ማይሎች፡ ወደዚህ ምድር፡ ጉዞ ቢጀምሩ፡ ወደ ምድር ለመድረስ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዓመታት ይፈጅባቸዋል።" እኔም አልኩት፦ "በዚህ ሁሉ ታላቅ፣ ሰፊ ሥርዓት ውስጥ፣ በመነጽር ማየታቸውን ይነግሩናል፡ እዛ ማዶ ርቀው፡ ጨረቆች እና ከዋክብቶች ባሉበት፡ የመቶ ሃያ ሚሊዮን አመታት የብርሃን ጊዜን ማየት ችለዋል። እና—እና፡ በዚህ ሁሉ፡ እነዚህን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። በመካከላቸው ያቆመው ነገር አለ።"

46 እና እንዲህ አልኳቸው፡ "የሆነ ቦታ ላይ፡ አንድ ቀን አጉዪ መነጽር ባለበት ቦታ፡ ዞድያክን፡ ይህ ነው ብለውኛል፡ ከድንግል ጀምሮ፡ በካንሰር ዘመን አልፎ፡ እስከ መጨረሻ አንበሳው ድረስ፡ ሊዮ አንበሳው ድረስ ይደርሳል። የክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት፡ በድንግል ነው፡ ሁለተኛ መምጣት፡ ከይሁዳ ነገድ በሆነው አንበሳ።" እኔም አልኩት፦ "ዞዲያክን ለማየት የተቻለኝን ሁሉ ሞክሬአለሁ፡ ማየት ግን አልቻልኩም። ነገር ግን፡ ግን'ኮ፡ ያለ ነገር ነው። በዚያ የሰለጠኑ ሰዎች፡ መኖሩን ያውቃሉ። ኢዮብ አይቶታል። ሰዎችም ያዩት ነበር። በድሮ ዘመን፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ነበርና። በዚያ ሁሉ ታላቅ ሰፊ የሚሊዮኖች እና በቢሊዮኖች በሚቆጠሩ—የብርሃን ዓመታት፡ እግዚአብሔር በመካከል ተቀምጦ ወደ ታች ያያል። ጳውሎስ አሁን በእዚያ አለ። እናቴም፡ ወደታች እያየች፡ በአንድ ጥግ እዛው ትገኛለች።"

47 እና የዚያን የሰማይ ሰራዊት አሰላለፍ ሳሰበው፡ ከመካከላቸው ከሰፍራው የወጣ አንድም የለም። እያንዳንዱ፡ ጊዜውን በትክክል ይጠብቃል። የእግዚአብሔር ታላቅ ሠራዊት! ሰራዊቱ ሁሉ አሰብኳቸው፡ ጨረቃ አንዴ ከሥርዓት ውጭ ብትሆን፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ምድር እንደገና በውሃ በተሸፈነች ነበር። መኖርያችን አድርጎ፡ እግዚአብሔር፡ ምድርን ሊጠቀምባት

በፈለገ ጊዜ ወደ ነበረችበት ሁኔታ በተመለሰች ነበር። “ቅርጽ አልባ፡ ባዶ፡ ጨለማ፡ ውኃም በምድር ሰፋት ላይ ተዘርግቶ ነበረ።” አሁንም ጨረቃ ብትንቀሳቀስ፡ እንደገና ተመሳሳይ ነገር ይሆናል። የጨረቃ አለቶች ትንሽ ከምድር ሲርቁ፡ ማዕበል ይነሣል፡ መለስ ሲሉ፡ ማዕበሉም ይከተላል። የእግዚአብሔር ታላቅ ሠራዊት ነው። የእግዚአብሔር ታላቅ ሠራዊት… በዚያ እንደ ሆነ አሰብኩ…

48 ከዚያ፡ ወደ መኝታችን ሄድን። ከነዚህ ሁሉ አንዱ ቦታውን እንደማይለቅ ማሰብ ጀመርኩ። ሁሉም በየቦታቸው ተቀምጠዋል። አንዳቸው ጋር፡ በሆነ መልኩ፡ እንቅስቃሴ ከሆነ፡ በምክንያት ነው፡ ምድር ላይ ተጽዕኖ ይኖራል። አንዳንዶቹ ወደ ሌላ ቦታቸው ሲንቀሳቀሱ፡ ውጤቱን አሁን አይተናቸዋል። ውጤታማ ነው። ሁሉንም ነገር ይነካል።

49 እናም ያ ታላቅ የሰማይ ሰራዊት፡ ሁሉንም ነገር በሥርዓት እንዲሠራ፡ እንደዛው፡ ቦታውን የሚጠብቅ ከሆነ፡ የምድር ሰራዊት መዛባትስ ምን ይሆን? አንድ ሰው ከትዕዛዝ ሲወጣ፡ እንዲያው እንዴት፡ ሁሉንም ነገር ከቦታው ያመሰቃቅል ይሆን! አንድ አባል ከሥርዓት ሲወጣ ሙሉው የእግዚአብሔር ፕሮግራም ይዛባል። የመንፈስን ሥርዓት ለመጠበቅ ያለማቋረጥ መጣር አለብን።

50 በእግዚአብሔር ፊት፡ ዛሬ ጠዋት፡ ይህንን ወደ እውነተኛ የፈውስ አገልግሎት ለማምጣት፡ ዛሬ ጠዋት ከዚህ ጣራ ስር የተሰበሰብን ሰዎች፡ ልዩ በሆነ መቀናጀት… ይህንን አካል ማስጠበቅ እንድንችል፡ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን የአካል ክፍል በዚህ ጠዋት፡ በቅንጅት ውስጥ እንደሚያሰቀምጥ፡ ሰፍራችንን ብቻ አጽንተን ጠብቀን፡ የነፍስ እና የሰጋችን ድንገተኛ ፈውስ እስኪሆን ድረስ ያድርግ።

51 አሁን፡ መጀመሪያ ላይ እንዳልኩት፡ ይህች ሴት ዶክተር ሆልብሩክ ጋር… ካንሰሩ ተነሣላት። አሁንስ፡ ወደ ክሊኒኩ የመንቀጥቀጥ ድምጽ ያመጣ አምላክ፡ ጠባሳ እንኳን ሳያሰቀር ካንሰሩን ያነሳው ያው አምላክ፡ እዚህ እንዳለ አታውቁምን? እሱ የሚጠብቀው አንድ ነገር፡ የሰማይ ሰራዊቱ ሰፍራቸውን እንደጠበቁ—ሰራዊቱ ሁሉ፡ ሰፍራቸውን፡ እንዲጠብቁ ብቻ ነው።

52 አሁን፡ ከአንዱ ጦርነት ሌላ ጦርነት፡ የጦር ወሬዎችን ሁሉ እንዳሳለፍን ታውቃላችሁን? አሁንም ምድር ከቆየች፡ ብዙ ሌላ ጦርነቶች ይኖራሉ። በአጽናፍ ዓለም ውስጥ ሁለት ኃይሎች ብቻ እንዳሉ ግን ታስተውላላችሁን? አንዱ አገር ከሌላው አገር ቢለያዩ፣ አንዳችን ከአንዳችን፡ እና በልዩ ልዩ ልዩነቶች ቢኖሩንም፡ ይህ ሁሉ ከሁለቱ ኃያላን የሚነሣ ነው። ሁለት ኃይሎች ብቻ አሉና፡ ሁለት መንግሥታት ብቻ፡ ሁለት ኃያላን፡ እና ሁለት መንግሥታት ብቻ አሉ። ሌሎቹ ሁሉ፡ ትናንሽ እና ጥቃቅን ነገሮች፡ ከሁለቱም ሀይሎች ጋር የተገናኙ ናቸው። እነዚያም ኃይሎች የእግዚአብሔር ኃይል እና የሰይጣን ኃይል ናቸው። እያንዳንዱ ጦርነት፡ ሁከት፡ ሁሉም ነገር መነሻው… ያ ነው፡ የሚቆጣጠረው የእግዚአብሔር ኃይል ወይም የሰይጣን ኃይል ነው፡ ያሉት ሁለት ኃይሎች እነዚህ ብቻ ናቸውና። ያ ደግሞ የሕይወት ኃይል እና የሞት ኃይል ናቸው። እንግዲህ፡ ሁለት ኃይሎች ብቻ ናቸው።

53 ሰይጣን... የኃይሉ መነሻ፡ የተጣመመ የእግዚአብሔር ኃይል፡ በመጠቀም ነው። ትክክለኛው ኃይል አይደለም። ሰይጣን የያዘው ሁሉ፡ የተዛባ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ሞት ጠማማ ሕይወት ነው። ውሸት የተጣመመ እውነት ነው። አያችሁ? ዝሙት አላግባብ—የተደረገ፡ ጥቅም ላይ የዋለ የጽድቅ ድርጊት ነው። አያችሁ? የሰይጣን ነገር ሁሉ፡ ኃይል ቢሆንም የተጣመመ ኃይል ነው።

54 እኛም፡ ዛሬ፡ እዚሁ ተቀምጠን፡ አንደኛው ወይም ሌላኛው ኃይል ይቆጣጠረናል። ስለዚህ ክፋውን አስወግደን። አሰላለፋችን እንደ ሰማይ ከዋክብት እናድርገው።

55 መጽሐፍ ቅዱስ፡ በይሁዳ መጽሐፍ ላይ “የነውራቸው አረፋ እየደፈቁ፡” “ሰፍራቸውን የተው መላእክት፡” ይላቸዋል። ሰፍራቸውን የተው ከዋክብት መሆን አንፈልግም፡ **ይህስ** ትክክል ይሆን ወይ ብሎ ያሰባል፣ **ያስ** ትክክል ይሆን ወይ ብሎ ያሰባል፣ **ይፈጸም** ይሆን ወይ ብሎ ያሰባል፣ ይሆናል ወይ... ይቅበዘበዛሉ። እናንተ ግን አትቅበዝበዙ። በግዳጁ እንደ ጸና እውነተኛ ሰራዊት፡ እንደ ሰማይ ከዋክብት የጸናችሁ ሁኑ። አምናችሁ፡ ቁሙ! ሞት እና ሕይወት።

56 አሁን፡ አንድን ሰራዊት፣ ትክክለኛ ሰራዊት ከሆነ፣ አንድ አገር ከሌላ አገር ጋር ለመፋለም ሲያዘጋጀው፡ ከሁሉ አስቀድሞ የትኛው ትክክል የትኛው ስህተት መለየት አለበት፡ ያንን አገር ለመፋለም አቅም ይኑራቸው አይኑራቸው ይመዝናሉ። ኢየሱስም እንዲሁ አስተምሯል። እናም ሰዎች ያን ካደረጉ፡ አገሮች—ቁጭ ብለው፡ ቆም አርገው እነዚያን ነገሮች ቢያሰቧቸው፡ በሁለቱም በኩል፡ ጦርነት አይኖረንም ነበር።

57 አሁን፡ እንዲህ ሆኖ እናገኘዋለን፡ ከሁሉ በፊት፡ የአገሪቱ ጦር መሪ ቁጭ ብሎ ካላሰበ፡ ሰዎች ይህን ካላደረጉ፡ ተፋላሚው ጦር ለመግጠም እንዳልተሳሳቱ፡ ግባቸው እና አሳባቸው ልክ መሆኑን፡ በቂ ኃይል እና ጥንካሬ አለን ወይስ የለንም ብለው ቀድመው ካላሰቡበት፡ በርግጠኝነት ይሸነፋሉ።

58 የጀነራል ከስተር ከባድ ስህተቱ ይህ ነበር። ጄኔራል ካስተር፡ እኔ እንደተረዳሁት፡ ወቅቱ የአምልኮ ጊዜ ስለነበረ፡ ሐይማኖታዊ በዓላቸው ስለነበር፡ ድግስ ደግሰው ነበርና። ወደ ሱዝ ምድር እንዳይሄድ። የመንግስት ትዕዛዝ ደርሶት ነበር። ካስተር ግን ሰከረ፡ እና በቀላሉ አደርገዋለሁ ብሎ አሰበ። ትእዛዝ ይለፍ አይተላለፍ፡ መሻገር ፈለገ። በነገራችን ላይ ሄደው በንጹሐን ሰዎች ላይ ተኩሰው፡ ሰዎቹን መቱባቸው። አንዳንዶቹን መቱ መሰለኝ። ሌሎቹ በአምልኮ ሳሉ—ህዝባቸውን ለመመገብ፡ ምግብ ለማደን፡ የወጡ፡ እስካውቶች ናቸው። ካስተርም፡ እነዚህ፡ ሲያልፉ አይቶ፡ ከጎናቸው በኩል ያሉ ስለመሰላቸው፡ ወደ እስካውቶቹ ተኮሰባቸው። እና እነዚህ እስካውቶች አምልጠው፡ ተመለሱ። ምን አደረጉ? ታጥቀው፡ መጡ። የጀነራል ካስተር መጨረሻ ያ ነበር፡ አስቀድሞ፡ ቁጭ ብሎ አላሰበበትምና።

59 እዛ የመሄድ መብቱ አልነበረውም። በዚያ ምንም ጉዳይ አልበረውምና። አስቀድሞ፡ ህንዶቹን ከምስራቃዊ ጠረፍ፡ እስከ ምዕራብ ድረስ ገፍቷቸዋል። ውልም ተዋውለዋል፡ እርሱ ግን ውሉን አፈረሰ። ውሉንም ሲያፈርስ፡ ያን ጊዜ በጦርነቱ ተሸንፏል።

60 እናም ሰራዊት፡ መጀመሪያ፡ ለውጊያ ሲዘጋጅ፡ መጀመሪያ አንዳንድ ወታደሮች፡ ይመረጣሉ። የውጊያ ልምምድ ማድረግ አለባቸው። የጦር ልብስ መልበስ ይገባችኋል።

61 የውጊያዎች ሁሉ አውራው ውጊያ፡ ወደ ተግባር ለመግባት አሁን ተዘጋጅቷል ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር ሰራዊቱን እየመረጠ እንደቆየ አምናለሁ። እያለበሳቸው፣ እያሰለጠናቸው እንደቆየ አምናለሁ። የጦር ግንባሩ አሁን ተዘጋጅቷል፡ ለመጀመር በተጠንቀቅ ላይ ነው።

62 ይህ ታላቅና፡ የመጀመርያው ውጊያ የተጀመረው፡ ሚካኤል እና መላእክቱ፡ ከሉሲፈር እና ከመላእክቱ ጋር በሰማይ በተዋጉ ጊዜ ነው። የመጀመርያው ውጊያ፡ ጅማሬው በሰማይ ነው። ስለዚህ፡ የሐጢአት መነሻ፡ በምድር ሳይሆን በሰማይ ነው።

63 ከዚያም ከሰማይ ተወረወረ፡ ከሰማይ፡ ወደ ምድር ተጣለ፡ በሰው ልጆች ላይ ወደቀች። ከዚያም ውጊያው፡ ከመላእክት፡ የሰው ውጊያ ሆነ። ሰይጣንም እግዚአብሔር ለራሱ እንዲሆን የፈጠረውን፡ የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሊያጠፋ መጣ። ይህን ለማጥፋት፡ ሰይጣን፡ መጣ። ዓላማው ያ ነበር፡ ለማጥፋት ነበር። ያን ጦርነት እዚህ ምድር ላይ አሰጀመረው፡ በእኛ ውስጥ ጀመረው፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እየተቀጣጠለ ነው።

64 አሁን፡ የትኛውም ጦርነት በግንባር ከመፋጠጡ በፊት፡ መጀመሪያ አውድማ፡ ወይም ጦርነቱ የሚካሄድበት ቦታ፡ የተመረጠ ቦታ ይፈልጋሉ።

65 በአንደኛው የዓለም ጦርነት፡ የተካሄደው እና የተዋጉበት ቦታ፡ ኗሪ-ሰው በሌለበት-መሬት ነበር። እና በተመረጡ ቦታዎች መሆን አለበት።

66 ልክ እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጉ፡ የሚሰባሰቡበት ሰፍራ በሁለቱ ወገን—ኮ—ኮረብታ ነበረው። ጎልያድ ወጥቶ የእስራኤልን ሠራዊት የጠራበትም ያ ነበር። ዳዊትም የተፋለመው፡ በዚያው በሸለቆው ውስጥ ነበር፡ ጅረቱ በሚያልፍበት በሁለቱ ኮረብታዎች መካከል ሲሄድ፡ ድንጋዮቹን አነሳቸው።

67 የተመረጠ ቦታ መኖር አለበት። በዚህም፡ **እዚያ** ሄደው፡ የሚዋጉበት የጋራ—ሜዳ፡ ኗሪ-ሰው-የለለበት ቦታ አላቸው። አንዱን ጦርነት **በዚህ** በኩል፡ ሌላውም **በዚያ** በታች በኩል፡ ሌላኛው **በዚያ** ማዶ፡ አያደርጉትም። ተገናኝተው ኃይላቸውን የሚፈታተሹበት የውጊያ ግንባር አለ፡ እያንዳንዱ ሰራዊት ኃይሉን ከሌላው ሰራዊት ጋር የሚፈታተሽበት፡ የጋራ መገናኛ ቦታ ነው። አሁን፡ (ተከታተሉ) እንዲያመልጣችሁ።

68 ይህ ታላቅ ጦርነት በምድር ላይ ሲጀመር፡ የጋራ መገናኛ ቦታ መኖሩ ግድ ነበረ። ጦርነቱ የሚጀመርበት፡ የጦር ቁጣ የሚነሳሳበት፡ የተመረጠ አውድማ መኖር ነበረበት። ስለዚህ የጦር አውድማው የሰዎች አእምሮ ነው። ጦርነቱ የሚፋፋምበት ቦታ ይህ ነው። የሰው አእምሮ፡ ጦርነቱ የሚጀመርበት የጦር አውድማ ሆኖ ተመረጠ፡ ይህም ውሳኔዎች ሁሉ መነሻቸው ከአእምሮ፡ ከጭንቅላት ስለሆነ ነው። በጭራሽ፡ መነሻቸው ከድርጅቶች ሆኖው አያውቁም። በጭራሽ ከአንዳንድ ሜካኒካል ጉዳዮች ተነስተው አያውቁም። በጭራሽ አውድማዎቹ ከዚያ ጀምረው አያውቁም። ስለዚህ፡ ድርጅት፡ በጭራሽ፡ በጭራሽ የእግዚአብሔርን ስራ ሊሰራ አይችልም፡ ምክንያቱ፡

ጠላትህን የምትፋለምበት አውድማ፡ አእምሮህ ውስጥ ነው። ምርጫዎችህን የምታደርገው በራስህ መሆን አለበት። የሚፋለመው አንተን ነው።

69 በጽኑ ህመም የታመመችው፡ ይህች ምስኪን ሴት፡ ይህ ነገር በደንብ እየሰማች መሆኗን፡ እርግጠኛ እንድትሆን እፈልጋለሁ።

70 ውሳኔዎች የሚደረጉት በአእምሮ ውስጥ፡ በጭንቅላት ነው። ሰይጣን እና ውሳኔዎቹም ሁሉ፡ ከአንተ ጋር የሚገናኙበት ቦታ ያ ነው፡ እግዚአብሔርም ሰውን የሰራው በዛ መልኩ ነውና።

71 አሁን፡ (ማስታወሻዬ ላይ አይታችሁ ከሆነ) ያዘጋጀኋት ትንሽ የካርታ ስዕል ነበረች። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ... ቦርዱ ላይ፡ ስጠቀምባት ነበር። የሰው ልጅ የተፈጠረው እንደ ሰንዴ ቅንጣት ነው። ሰው ዘር ነው። የሰው ልጅ ዘር ነው። በስጋ፡ የአባታችሁ እና የእናታችሁ ዘር ናችሁ፡ ሕይወት የሚመጣው ከአባት ነው፡ ሥጋችሁም ከእናት ነው። ስለዚህ፡ ሁለቱ፡ እንቁላል እና—ደሙ፡ በሕብረት አንድ ይሆናሉ። በደም ህዋስ ውስጥ ግን ህይወት ይገኛል። በዚያ ውስጥም—ልጅ ማደግ፡ መስራት፡ ይጀምራል። እንግዲህ፡ ማንኛውም ዘር በውጭ በኩል ቅርፊት አለው፡ ውስጡ ጭማቂ ነው፡ በጭማቂው ውስጥ ግን የሕይወት ዘረ መል አለ። እኛም የተሰራነው፡ በዚህ መንገድ ነው። ስጋ፣ ነፍስ፣ እና መንፈስ ነንና። ውጫዊው አካል፡ ስጋ ነው፡ ቅርፊት ነው፡ በዛ ውስጥ ያለው፡ ህሊና እና የመሳሰሉት፡ ነፍስ ነው፤ የነፍስ ውስጥ፡ ውስጠኛው ክፍል፡ መንፈስ ነው። መንፈስም ሌላውን ሁሉ ያስተዳድራል።

72 ወደ ቤታችሁ ስትመለሱ፡ እነዚህ ትንንሽ ቀለበቶችን፡ በስዕል መልኩ ስላችሁ አስቀምጧቸው። የውጭው አካል አምስት የስሜት ህዋሳት እንዳሉት ትገነዘባላችሁ፡ እነሱም ማየት፣ መቅመስ፣ መዳሰስ፣ ማሽተት፣ መስማት ናቸው። የሰውን አካል የሚቆጣጠሩት አምስቱ የስሜት ህዋሳት እነዚህ ናቸው።

73 በአካል ውስጥ ነፍስ ትገኛለች፡ የነፍስ መቆጣጠርያም ምናብ፣ ህሊና፣ ትዝታ፡ ምክንያት እና የፍቅር ስሜት ናቸው። ነፍስን የሚቆጣጠረው ያ ነው።

74 መንፈስ፡ ግን፡ አንድ ስሜት ብቻ አለው። መንፈስ... ኦህ፡ አሁን እንወቀው። መንፈስ አንድ ገዢ ስሜት አለው፡ ያን ስሜት የሚገዛው፡ እምነት ወይም ጥርጣሬ ነው። በትክክል ነው። ይህም አንድ መግቢያ ጎዳና አለው፡ ነጻ የሞራል ምርጫ ይባላል። ጥርጣሬ መቀበል ወይም እምነትን መቀበል ትችላላችሁ፡ ሊሰራባችሁ የምትፈልጉት አንዱን በመምረጥ። ስለዚህ ሰይጣን፡ የሰውን መንፈስ በእግዚአብሔር ቃል እንዲጠራጠር ለማድረግ፡ ከዋናው ነገር ይጀምራል። እግዚአብሔር ቃሉን በዚያው መንፈስ ለማስቀመጥ፡ ከዋናው ክፍል ይጀምራል። ይኸው ይህ ነው። የሚሰራው ይህ ነው።

75 አሁን በዚች ቅጽበት፡ በዚህ ቤተ ክርስትያን ያለን ሰዎች፡ ያለ አንዳች ጥርጣሬ፡ አንድ ሆነን እያንዳንዳችን አንድ ልብ እስክንሆን ድረስ እንደ ጥላት ብንሰራ፡ ከአምስት ደቂቃ በኋላ፡ አንድ ታማሚ በመካከላችን አይኖርም ነበር። የተወሰነች ነገር ብቻ ማስተካከል በቻላችሁ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበል እንጂ፡ ፍለጋ ላይ ማንም ባልቀረ ነበር። እንግዲህ፡ ከፈለጋችሁ፡ ትግሉ የሚጀመረው፡ በእእምሯችሁ ውስጥ ነው።

76 እንግዲህ ይህ፡ የክርስትያን ሳይንስ፡ ማይንድ ኦቨር ማተር፡ አለመሆኑን፡ አስታውሱ። አይደለም... አእምሮ ሕይወት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል

ይቀበላል፡ ከዚያም ሕይወት ያመነጫል። አሳባችሁ ይሄን ሊያደርግ አይችልም። የእግዚአብሔር ቃል ግን፡ በአሳባችሁ አውታር በኩል፡ ያፈልቀዋል። አያችሁ? የክርስትያን ሳይንሶች፡ ማይንድ ኦቨር ማተር እንደሚሉት፡ ከአሳባችሁ አይደለም። ያ አይደለም።

77 አእምሮአችሁ፡ ተቀባይ ነው። ይሰበስበዋል። ከዛ አእምሮአችሁን የሚቆጣጠርስ ምንድነው? መንፈሳችሁ ነው። ስለዚህ መንፈሳችሁ ያንን የእግዚአብሔር ቃል ይቀበላል፡ በውስጡ ህይወት የያዘም እሱ ነው። ይህም ህይወትን ወደ እናንተ ያመነጫል። ወንድሜ ሆይ! ያ ሲሆን፡ ህይወት፡ በዚያ አውታር ወደ አንተ ሲመጣ፡ የእግዚአብሔር ቃል በአንተ ውስጥ ይገለጣል። "በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፡ የምትፈልጉትን ጠይቁ እና ይደረግላችኋል።"

78 ከዚያስ ያ ምን ያደርጋል? ከልብ መኃል፡ ማለትም ከነፍስ፡ እያንዳንዱን አውታር እየመገበ፡ ከዚያ ይነሣል። ችግር የሚሆነው፡ በብዙ ጥርጣሬዎች **እዚህ** ቆመን፣ **በዚያ** ያለውን ነገር ለመቀበል ስለምንሞክር ነው። ያንን አቁሙትና፡ ከእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ጋር በአውታሩ ውረዱ፡ ከዛ በኋላ፡ በራሱ ቅጽበታዊ አሰራር፡ መውጣት ይጀምራል። ዋናው ነገር ውስጥ የተቀመጠው ነው። ዋናው ነገር፡ ውስጠኛው ነው።

የሰይጣን አካሄድም ከውስጥ ነው።

79 ለምሳሌ፡ እናንተ "አልሰርቅም። አልጠጣም፡ እነዚህ ነገሮች አላደርግም።" ትላላችሁ። ያ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

80 አያችሁ፡ ውስጠኛው ነው። የቱንም ያህል ጥሩ ብትሆኑ፡ የቱንም ያህል ሥነ ምግባር ቢኖራችሁ፡ ምንም ያህል እውነተኞች ብትሆኑ፡ እነዚህ ነገሮች ጠቃሚ ናቸው። ኢየሱስ ያለው ግን፦ "ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር ነው።" አያችሁ? ከውስጥ የሆነ ነገር መከሰት አለበት። ካልተወለዳችሁ፡ አርቴፊሻል ልብስ-ነው፡ ምክንያቱ ከልባችሁ ውስጥ በፈለጋችሁት መንገድ ለማድረግ ትመኛላችሁና። አርቴፊሻል መሆን የለበትም። እውነት መሆን አለበት።

81 ይህ ሁሉ በአሳባችሁ በኩል ወደ ነፍሳችሁ፡ መውረድ የሚችልበት፡ አንድ ጎዳና ብቻ አለው፡ ይህም በነጻ የሞራል ምርጫ ነው። "ሰው በልቡ እንዳሰበ፡ እንዲሁ ነው።" "ይሁን ያላችሁት እንደሚሆን አምናችሁ፡ 'በልባችሁ ሳትጠራጠሩ፡' ይህን ተራራ፡ ተንቀሳቀስ ብትሉት፡ ይሁን ያላችሁት ሁሉ ይሆንላችኋል።" ገባችሁ አይደል? እውነቱ ይሄው ነው። አያችሁ? የጦር አውድማው ይህ ነው። አንደኛ፡ እንዲጀመር ካደረጋችሁ።

82 ነገሮች ተሰርተው ለማየት እንጓጓለን። ለእግዚአብሄር የሆነ ነገር ለመስራት እንጓጓለን። ይህች ምስኪን ሴት... ያለ ጥርጥር፡ ለመኖር ጓጉታለች። ደህና መሆን ትፈልጋለች። ሌሎችም እዚህ አሉ፡ ደህና መሆን ይፈልጋሉ። እናም እንደ ዶክተሩ፡ ስለዚያ ጉዳይ ስንሰማ፡ ስለ ሙታን ትንሣኤ፡ አምላካችን ስላደረጋቸው ታላላቅ ሥራዎች ስንሰማ፡ እንጓጓለን። በዚህ ሂደት ውስጥ፡ እንደ ህሊና የመሳሰሉ ነገሮችን፡ ለመያዝ፡ ስሜት ለመጠቀም እንሞክራለን።

83 ብዙ ሰዎች፡ ብዙ ጊዜ፡ ቃሉን በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል። እኔንም ወደ መሰውያ ስጋብዛቸው፡ በተሳሳተ መንገድ ሲረዱኝ ቆይቷል። "የመሠዊያ ጥሪ

እምብዛም አልነበርኩበትም፡” እላለሁ፡ ያ ማለት ግን ወደ መሠዊያ አትጥሩ ማለት አይደለም።

84 ነገር ግን አንድ ሰው ሌላውን ሰው በክንዱ ይዞ፡ “ኦህ፡ ወንድም ጆን፡ ታውቃለህ? እኔና አንተ’ኮ ብዙ ዘመን ጎረቤት ነበርን። ወደ መሰውያው ቅረብና፡ ተንበርከክ፡” ይለዋል። ምን እያደረገ ነው? እዚህ ስሌዳ ቢኖረኝ፡ ምን እያደረገ እንዳለ አሳያችሁ ነበር። በነፍሱ፡ በፍቅር ስሜት ለመስራት እየሞከረ ነው። ያ አይሰራም። ጎዳናው ያ አይደለም። በእርግጠኝነት፡ ያ አይደለም።

85 ምናልባት በነፍሱ ስሜት (በምን?) በትዝታ ውስጥ፡ እየሰራ ሊሆን ይችላል። “ኦህ፡ ወንድም ጆን፡ እናትህ ድንቅ እናት ነበሩ። ከረጅም ጊዜ በፊት ሞቱ።” ትዝታ! አያችሁ? አትችሉም።

86 በነጻ የሞራል ምርጫ መስመር አልፎ መምጣት አለበት። የእግዚአብሔርን ቃል፡ ከአንተ፡ ከእራስህ ይሰራ... እናትህ ጥሩ ሴት ስለነበረች አንተ አትመጣም። ጥሩ ጎረቤት ስለሆንክ አትመጣም። እግዚአብሔር እንድትመጣ ስለጠራህ እና በቃሉ መሰረት ስለምትቀበለው ትመጣለህ። ቃል ሁሉም ነገር ነው። ቃል! ሁሉንም ነገር ከመንገድ አስወግደህ፡ ሕሊና ሁሉ፡ ስሜት ሁሉ አስወግደህ፡ ቃል እንዲገባ ብትፈቅድ፡ ቃል በትክክል ይሰራል።

87 በምን እንደተሸፈነ፡ እዚጋ ይታያችኋል? እንዲህ ትሉኝ ይሆናል፡ “ታዲያ፡ አሁን፡” እናንተ፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ታዲያ፡ እነዚህ፡ ስሜት እና ህሊና፡ እና ሌሎች፡ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውምን? ” በትክክል አላቸው፡ እንጂ። ነገር ግን ቃሉን ተቀብላችሁ፡ በሕሊና ከሸፈናችሁት፡ የተጣመመ ቃል ይሆናል እንጂ፡ አያድግም።

88 መሬት ላይ የተዘራች ጥሩ የበቆሎ እህል፡ በላይዋ ላይ እንጨት ነገር ወድቆባት አይታችሁ ታውቃላችሁ? ተጣምማ ታድጋለች። አዳጊ የሆነ፡ ምንም አይነት ተክል፡ ከልካይ ሲገጥመው፡ እንዲሁ ይሆንበታል።

89 እንግዲህ፡ ዛሬ የጴንጤቆስጤ እምነታችን ጉዳይም ያ ነው። የተማርነው እምነት፡ በእኛ ውስጥ እየኖረ ያለው መንፈስ ቅዱስን፡ ብዙ ነገሮችን እንዲያደናቅፉት ፈቅደናል። ሌላ ሰው በመመልከት፡ ብዙ ነገሮችን ፈቅደናል።

90 ዲያቢሎስም ሁል ጊዜ ከእውነተኛ እና ትክክለኛ ምስክርነት አርቆ፡ ወደ አንድ ሰው ውድቀት ሊጠቁማችሁ ይሞክራል። አንድ ጊዜ፡ ያልሆነውን ነገር፡ እንደሆነ አስመስሎ የወጣውን ግብዝ ሰው ያሳያችኋል። እሱ’ማ አስመሳይ ስለነበረ፡ አልቻለም። ከእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ምንጭ የመጣ ከሆነ ግን፡ “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።” እንዲህ መሆን አለበት።

አየሽ፡ እህት?

91 በአእምሮ ውስጥ ትቀበሉታላችሁ፡ ከዛ ብኋላ ልብ ውስጥ ይታመናል። ያኔ የእግዚአብሔር ቃል እውን ይሆናል፡ ያኔ የነፍስ እና የሥጋ ስሜቶች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ይታጠባሉ። ከዚያ ስለ እግዚአብሔር ያላችሁ ስሜት፡ ስለ እግዚአብሔር ያላችሁ ሕሊና፡ አምላካዊ የሆነው ሁሉ፡ በእናንተ ውስጥ መፍሰስ ይጀምራል። ጥርጣሬ አይኖርም። ሊነሳ የሚችል ነገር አይኖርም።

92 ትዝታ ላይ መጥቶ፡ እንዲህ ሊል የሚችል አንድም ነገር አይኖርም፡- “አስታውሳለሁ፡ ወይዘሮ ጆንስ እግዚአብሔርን ለማመን ትሞክር ነበር፡ ወይዘሮ

**እከሊት-እና-እከሊትም** እንዲሁ። አንድ ቀን፡ ወይዘሮ ዶኢ፡ አልሆነላትም እንጂ እግዚአብሔርን እንዲፈውሳት ለማመን ትሞክር ነበር።" አያችሁ?

93 ነገር ግን ያ አውታር ተጠርጎ ከተጸዳ፡ እና ከውስጡ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ፡ ሚስ ጆንስ ማንም ትሁን ምንም ታድርግ፡ በጭራሽ ትዝታ ውስጥ አይመጣም። አንተ እና እግዚአብሔር፡ ናችሁ፡ ከሁለታችሁ በቀር ሌላ አይኖርም። እውነቱ ይህ ነው። ውጊያችሁ ይህ ነው። ከጅምሩ ግደሉት። በመንገድ ሳለ ግደሉት። ውጊያው ምን ያህል ማዘግየታችሁ አይደለም። አሁኑኑ፡ አስቁሙት!

94 ትዝታዎቹን እና ሕሊናውን፡ የምትሏቸው ነገሮች እያሰባችሁ፡ በመጠበቅ፡ እና በማምጣት፡ "አይ፡ ልወድቅ እችላለሁ። ትክክል ላይሆን ይችላል።" በጭራሽ፡ እንዲህ አታድርጉ።

95 ሌላውን ሁሉ አስወግዳችሁ፡ አውታሩን ከፍታችሁ፡ እንዲህ በሉት፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ ቃልህ ለዘለአለም እውነተኛ ነው፡ የእኔም ነው። መላው ቤተ ክርስቲያን ቢወድቅ፡ ዓለም ሁሉ ቢወድቅ፡ እኔ ግን ቃልህን ይዣለሁና፡ አልወድቅም በሉ።" ውጊያው ይህ ነው። ነገሩ ያ ነው።

96 ሁሉን ቻዩ አምላክ ካንሰርን ከሴት ጡት፡ ያለ ጠባሳ እያስወገደ፡ ህጻን ልጅ ወድቆ እንዲሞት እንዴት ይፈቅዳል? ኖ፡ ሰር።

97 ቅርብ ጊዜ፡ አንዲት ሴት ከሁለተኛው ደረጃ ትምህርት ቤት፡ ወደዚህ መጣች። እናቷ ደወለችልኝና፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ልጄ ሆጅኪን በሽታ ተይዛለች፡" አለችኝ። እብጠቶችን የሚሰራ፡ ካንሰር ነው። ዶክተሮቹ በጉሮሮዋ ላይ ከወጣው ከአንዱ ቁራጭ ወስደው፡ ላኩት፡ እና በትክክል የሆጅኪን በሽታ ሆኖ ተገኘ።

98 ስለዚህም "ቀጣዩ የሚወጣው፡ ልቧ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ያ ሲወጣ፡ ትሞታለች፡" አላት። "ምንም አልቀራትም... እንደ አወጣጣቸው፡ ለመኖር፡ የቀራት ጊዜ፡ ምናልባት፡ የሦስት ወራት ጊዜ ይኖራታል፡" አለ።

99 እናትየውም "ምን ላድርግ? ትምህርት ቤት ልላካትን? " አለችው፡

100 "አዎን አካሄድዋ ድንገት ስለሚሆን፡ ትሂድ፡" አላት። "ተያት ትሂድ፡ የቻለችውን ያህል ነጻ ህይወት ትኑር። ስለ ጉዳዩ አትንገሯት፡" አላት።

እመቤቲቱም "ምን ላድርግ፡" ብላ ጠየቀችኝ?

101 "አምጧት እና በፀሎት መሰመር ውስጥ አስገቧት፡" አልኳት። የሆነ እንግዳ ስሜት ተሰማኝና፡ "አንቺም ከሷ ጋር ነይ፡" አልኳት።

102 ልጅቷ ስትመጣ፡ በዚያ ጠዋት፡ ከሜክ-አፕ የተነሣ፡ ከንፈሮቿ ሰማያዊ-ይመስላሉ፡ የትምህርት ቤት ነገር ታውቁታላችሁ። ምስኪኗ—መጣች። ማን እንደሆነች አላወቅኳትም፡ የተደዋወልነው በስልክ ብቻ ነበር። እጇን ያዝኳትና፡ "እንደምን አደርሽ፡ እህቴ፡" አልኳት። እሷ ነበረች። እሷ ናት። ከትንሽ ጊዜ በኋላ፡ እናቷን አየኋት እና ሁለቱም ያለ እግዚአብሔር፡ ያለ ክርስቶስ አየኋቸው። "በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ፈውስን እንዴት ትጠብቃላችሁ? ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችሁ ትቀበላላችሁን? " አልኳቸው፡ "ስለ ሐጥያቶቻችሁ ስርየትስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመጠመቅ ወደዚህ ገንዳ ለመግባት ፈቃደኞች ናችሁን? " አልኳቸው፡

እነሱም “ፈቃደኞች ነን፡” አሉኝ።

103 አቤት፡ የሆነውን ታውቁታላችሁ። ሴቲቱ ዛሬ ጠዋት በዚህ ቁጭ ብላ ትሆናለች። ብዙዎቻችሁ ጉዳዩን ታውቃላችሁ። እዚህ ካሉት ባለአደራዎች፡ አንዱ የሆነው ወንድም ማይክ ኢጋን፡ ጉዳዩን አይቶታል። ይህ የሆነው ከአራት ወይም ከአምስት ዓመታት በፊት ነው። ልጅቷ ወደ ሐኪም ተወሰደች፡ በውስጧ የሆጂን በሽታ ምልክቱ እንኳ አልተገኘባትም።

104 ምክንያቱ ምንነበር? አስቀድማችሁ፡ አውታሩን መክፈት አለባችሁ። የእግዚአብሔርን ቃል የሚቀበል፡ ወታደሩ፡ መንፈስ ቅዱስን፡ በጦር ግንባር ላይ እንዲሰለፍ መፍቀድ አለባችሁ። እርሱ ቃል ነውና። እሱ ሲቆም፡ የሚያስቆመው ነገር አይኖርም። ማንም አይችልም... ሌሎች አውታሮች በሙሉ ይወገዳሉ። ማስተንፈሻው የተደፈነ፡ የድሮ ቦይለር፡ እሳት ላይ ብትጥዱት፡ ዕቃዎቻችሁን ያፈነዳባችኋል። ብዙ የፈነዳዱ-ክርስቲያኖች ጉዳይም የሆነው ይህ ነው፡ የዚህ ሁሉ ምክንያት፡ ወደ ውስጥ ዘልቀው አውታሮቹን ስለማያጸዱ ነው። ህሊናን፣ ትዝታን፣ ሀሳቦችን፣ ሁሉ ወደ ጎን በመተው፡ በማይጠፋው በእግዚአብሔር ቃል፡ ከውስጥ ወደ ውጭ መውጣት አለበት፡ እውነቱ ይህ ነው።

105 ዛሬ **በዚህ** በኩል፡ አሰር ሺ ሰዎች፡ አምነው ቢሞቱ፡ ነገም **በዚያ** በኩል፡ አሰር ሺ ሰዎች፡ አምነው ቢሞቱ፡ ከኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ግለሰቡ እኔ ነኝ። እኔው ነኝ የማምነው። የማምነው እኔው ነኝ። ከዛ በኋላ፡ አውታራችንን ለመክፈት ስንፈልግ፡ ከቻልኩ ብለን ለማየት፡ ወደ ኋላ እንጎተታለን። **ይህንን** እና **ያኛው**፣ **ይሄኛው** እና **ያኛው**፣ በሺዎች የሚቆጠሩ፡ ሲመሰክሩ እናያለን።

106 ዲያቢሎስ ግን ወዲያውኑ ተመልሶ ሊመጣ ይሞክራል። ፍጹም፡ መግቢያ ካለ፡ ያያል፡ ከዛ ሰራዊትህን በሙሉ ያሸንፍብሃል።

107 ስሜቶችን ሁሉ፣ ማየት፣ መቅመስ፣ መዳሰስ፣ ማሽተት፣ እና መስማት፡ ቢኖሩ ችግር የለውም፡ ከቃሉ ጋር ካልተስማሙ ግን አትመኑአቸው። ሁሉም ጥሩ ናቸው፡ ከቃሉ ጋር ከተቃረኑ፡ ግን፡ አትስሟቸው። ምናብ፣ ሕሊና፣ ትዝታዎች፣ አመክንዮ እና ፍቅር፣ እነዚህም ሁሉ፡ ከቃሉ ጋር ከተስማሙ፡ ምንም ችግር የለውም። ፍቅራችሁ ከቃሉ ጋር ካልተስማማ ግን፡ አስወግዱት። ማስተንፈሻውን፡ ወዲያው ያፈነዳባችኋል። አያችሁ? አመክንዮአችሁ ከቃሉ ጋር ከተጻረረ፡ ከሱ ራቁ። እውነት ነው። ሞተሩ... ትዝታህ፣ ምናብህ፣ ህሊናህ፣ ምንም ይሁን፡ በውስጥ ካለው ጋር ካልተስማማ፡ አስወግዱት።

108 ከዚያስ ምን ታገኛላችሁ? ሶላር ሲስተምን አለ። ሃሌሉያ! እግዚአብሔር፡ ከዋክብትን በስርዓት አዘጋጅቶ “እስክጠራችሁ ድረስ እዚያ ቆዩ!” አላቸው። ማንም ሳይነቀንቃቸው፡ እነሆ ጸንተው ቆመዋል። አንድ ሰው ስሜቶች፣ ሕሊና፣ እና ሌላ ሌላ ነገሮች ሁሉ ጠራርጎ፡ በመንፈሱ ውስጥ፡ እግዚአብሔር ከጎኑ እስኪቆምለት ድረስ ከኋላው እስኪደግፈው ድረስ፡ እግዚአብሔር በእጁ ከያዘው፡ ጥርጣሬን ሊዘራበት የሚችል ሰይጣን በዓለም አይኖርም። ትክክል ነው።

ዙርያሽ ላይ መጥቶ “ምንም አልተሻለሽም፡” ይልሻል።

109 ህሊናሽ ግን፡ ወደዛ ተወስዷልና። ማስተንፈሻው ተጠራርጓልና፡ “ሃሌሉያ!” ብሎ ይጮኻል፡ ጭስ ማውጫው “ክብር ለእግዚአብሔር!” ይሁን ብሎ ይጮኻል፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ በትክክል እንዲሠራ፡ የእግዚአብሔር

ኃይል እንዲሠራበት፡ ንጹሕና ግልጽ ሆኖ ያበራል። አያችሁ? ዋናው ነገር ያ ነው።

110 የጦር አውድማችሁ ያ ነው። የጦር አውድማችሁ፡ መጀመርያው በነፍሳችሁ ውስጥ፡ በተከፈተው አእምሯችሁ ውስጥ ነው። አእምሮ––የነፍስ በር ናት፡ ማለቴ፡ የመንፈስ በር ናት። አእምሯችሁ ተከፍቶ መንፈስን ይቀበላል፡ ወይም መንፈስን ይቃወማል። ትንንሽ ሕሊናዎች፡ ትንንሽ ስሜታዊነቶች፡ እና ትንንሽ ስሜቶች፡ ሌላ ሌላ ነገሮች ሊኖሯችሁ ይችላሉ። ያ ግን ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ትንንሽ ስሜቶች እና ነገሮች ብቻ ናቸው። ወደ እውነታው ሲመጣ ግን፡ አእምሮህ ይከፍታል። አእምሮህ ይቀበላል ወይም ውድቅ ያደርገዋል። ያ ነው፡ ወዳጆቼ።

እግዚአብሔር ሆይ፡ አንዳቸውም ይህ እያምልጣቸው።

111 አያችሁ፡ በሩን የሚከፍተው ወይም የሚዘጋው፡ ሕሊናችሁን የሚያዳምጠው፣ ትዝታችሁን የሚያዳምጠው፣ ፍቅራችሁን የሚያዳምጠው፣ አእምሯችሁ ነው። ነገር ግን አእምሯችሁ እነዚህ ነገሮች ሲዘጋባቸው፡ እግዚአብሔርን፡ እና የቃሉን መንፈስ እንዲገባ፡ ሲፈቅድ፡ ሌሎች ኮተቶችን በሙሉ ይጠራርጋቸዋል። ጥርጣሬ ሁሉ ይወገዳል። ፍርኃት ሁሉ ይወገዳል። ስሜት እና ጥርጣሬ በሙሉ ይጠፋል። ስሜታዊነት ሁሉ ይጠፋል። ከእግዚአብሔር ቃል በቀር በዚያ መቆም የሚችል ሌላ የለም፡ ሰይጣንም ያንን ሊዋጋው አይችልም። ኖ፡ ሰር። ሊዋጋው አይችልም። አሁን፡ ያ እውነት እንደሆነ እናውቃለን።

112 እነዚህ በሰው አእምሮ ውስጥ ያሉ ጦርነቶች የተፋፋሙት፡ ከኤደን ገነት ዘመን ጀምሮ ነው። ጀማሪውም ሰይጣን ነው። ሄዋንን ሲያገኛት ምን አደረገ? የእግዚአብሄርን ቃል አልካደም፡ ነገር ግን ነጭ አለባበሰው። የሆነ ቦታ ላይ አንዳንድ ትናንሽ አውታሮችን ዘጋ። "በኑው እግዚአብሔር… " ዘፍጥረት 3:1። አያችሁ? ቃሉ እውነት እንደሆነ ያውቃል። "በውኑ፡ እግዚአብሔር፡ እነዚህ ቃ––ቃ––ቃል የገባቸው ነገሮች'ኮ… " ዘው ብሎ መጥቶ ነገሩን ማፍረጥ እንደሌለበት፡ መዘክዘክ እንደማይገባው ያውቃል፡ ነገር ግን––የስኳር-ቅብ–– አደረገው።

113 እናቴ መድኃኒት ስትሰጠን፡ የብርቱካን ጭማቂን በካስተር ዘይት ውስጥ ለማስገባት ትሞክራለች። አቤት፡ የካስተር ዘይቱን ያለ ብርቱካን ጭማቂ ብትወስዱት ይሻላል! ይህ ግብዝነት ነው! አያችሁ? ማታ መጥታ… ትቀሰቅሰናለች፡ ለክሩፕ ብላ፡ የድንጋይ ከሰል ዘይት ትሰጠን ነበር። የከሰሉን ዘይት አምጥታ፡ ስኳር ታደርግበታለች፡ አያችሁ፡ የተገበዘ ነገር ነው። ስኳሩ ከሄደ በኋላ ግን፡ ላንቃችሁን፡ እስኪነቅል ድረስ፡ ያቃጥላችኋል።

114 እንግዲህ፡ እንዲህ ነው ወዳጆች ሆይ። ሰይጣን ዳር ዳሩን––ሊገበዝ ይሞክራል። የተሻለ ነገር ቀላል መንገድ፣ የበለጠ ማስተዋል፣ የተሻለ ትርጉም ሰጪ እቅድ ሊያሳያችሁ ይሞክራል። ነገር ግን እግዚአብሔር በመጀመሪያ ካወጣው ቃሉ የተሻለ፡ ሌላ እቅድ የለም። ይህን ቃል ያዙ። ተጣበቁበት። እሱም በእናንተ ውስጥ ይጣበቅ። አብራችሁ ቆዩ። ቁም ነገሩ––ያ ነው።

115 ሔዋን አመክንዮዋን ለማዳመጥ አእምሮዋን በከፈተች ጊዜ፡ ውጊያው ተፋፋመ። ወደ ውስጥ ያስገባው ማስተንፈሻዋ ያ ነው። ወደ ውስጥ ያወረደው አውታሯ—አመክንዮዋ፡ ነው። እሷ ራሷ፡ በነፍሷ ውስጥ፡ አመካኘች።

116 አይኖቿ እይታ ሆኑ። እባቡን አየችው። ቆንጆ ነበር፡ ከባሏ ይልቅ እጅግ የተሻለ፡ ሸበላ ነበር። ከምድር አውሬዎች ሁሉ ይልቅ ብልህ ነበር፡ ምናልባትም ከባልዋ ይልቅ እጅግ የሚያምር ነበር። ከፊቷ የቆመ ግሩም ወንዳ ወንድ አውሬ ይመስላል። እንዴት ታላቅ ነበር! ታላላቅ ነገሮችን ሊነግራት እየሞከረ ነበር።

117 እና መጀመሪያ ያደረገችው ነገር፡ አእምሮዋን ከፈተች። በከፈተችው ጊዜ፡ ሰዋዊ አመክንዮ ገባበት። "ያ፡ ለምን ደስታ አይሆንም?

118 ዛሬ በሴት ላይ የሚያደርገውም ይህ ነው። ጨዋ ባል ያላቸው አንዳንድ ሴቶች፡ ታላቅ፡ ግሩም፡ ወንዳወንድ ሰው ያገኛችኋል። ይህ ሰው አመክንዮን ለመክፈት ይሞካክራል። አስታውሱ፡ ሰይጣን ነው። ዲያብሎስ ነው። ወይም፡ በተቃራኒው፡ ወንድ ለሴት፡ ሴትም ለወንድ፡ በማንኛውም መንገድ። ምን ምን ያደርጋል? በአመክንዮው ኃይል፡ ሕሊናው ወይም ሌላ ነገር፡ መንሸራተት ይጀምራል።

119 ለእግዚአብሔር ቃል ግን ቅድሚያ ሰጡ። አንድም ሰው ሊጠጋው አይችልም... ኃጢአት መሥራት አይችልም... ሃሌ ሉያ! እንካችሁ። ይህ አሁን የወረደ፡ ትኩስ ነው። ሰው አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ቃል ካልጣለ ኃጢአት መሥራት አይችልም። **ኃጢአት** አይሰራም ይህም፡ "አለማመን" ነው፡ አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ቃል፡ የእግዚአብሔርን መገኘት ካልካደ፡ ኃጢአት ሊሠራ አይችልም።

120 ሔዋን የእግዚአብሔርን ቃል ከመካዷ በፊት፡ የአመክንዮ አውታሯ ከነፍሷ ከፍታ፡ ማመካኘት እስክትጀምር ድረስ ኃጢአት አልሠራችም። "እንዴ፡ እውነት'ኮ ነው። ባሌ እነዚህ ነገሮች ነግሮኝ አያውቅም፡ በእውነት አንተ ግን... እሱ'ኮ እንዲህ አታድርጊ ብሎኛል፡ ታውቃለህ፡ አንተ ግን፡ ይገርምሃል በእውነት እና በግልጽ አብራርተኸዋል። ግልጽ ሰላደረግክልኝ፡ በጣም ጥሩ እንደሚሆን—አምናለሁ።" አያችሁ፡ የመጀመርያው ውጊያ ይህ ነበር። ከዚህ ውጊያ መነሻ፡ ሌሎች ውጊያዎች ሁሉ መጡ። የመጣው ደም መፋሰስ ሁሉ፡ መነሻው በኤደን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል አላመነችም።

121 እንግዲህ አንዲት ትንሽ የእግዚአብሔር ቃል ባለማመኗ፡ ይህን ሁሉ ችግሮች ከተፈጠሩ፡ እንዴት ቃሉን አላምንም ብለን፡ እንመለሳለን? አትችሉም። እነዚህን ሁሉ ነገሮች፡ ህሊናን፡ ትዝታን ሁሉ... አመክንዮዎች፡ እና እነዚህ ሁሉ፡ ሌሎች ነገሮች ዝጉት። "እመክንዮዎችን ጣሉ።" ፈጽመን፡ በጭራሽ፡ ምንም ምክንያት አንሰጥ።

122 ቃሉን የምንቀበለው "እግዚአብሔር ብሏል፡" በሚል መነሻነት ነው፡ ይህም በእናንተ እና በእግዚአብሔር መካከል ምንጭን ይከፍታል። ከዛ በኋላ፡ በእናንተ እና በእግዚአብሔር መካከል እያንዳንዱ አውታር ይከፋፈታል።

123 የመጀመርያው፡ የውጊያው አውድማ፡ ይህ ነበር። ባለ .22 ጠመንጃ አንጠቀም፡ አቶሚክ ቦምብ—እንታጠቅ፡ ሰራውን በትክክል እንስራ። የእግዚአብሔርን አቶሚክ ቦምብ እንያዝ፡ "እሱ ምንድን ነው ወንድም ብራንሃም? " ኤፍ-ኤ-አይ-ቲ-ኤች እምነት በቃሉ ላይ። የእግዚአብሔር አቶሚክ

ቦምብ ያ ነው። በቀኝና በግራ፡ ደዌንና ሰይጣንን ይመታል። ፈጽሞ—ያጠፋቸዋል። ይቆራርጣል... ኦህ፡ በቃ... ይደመሰሳል። አምላካዊ ያልሆነውን ሁሉ ያፈርሳል። የእግዚአብሔር ቃል ከኋላው ሆኖ፡ ያንን የእምነት ቦምብ ወደዚያ ሲጣል፡ ሰይጣንን ሁሉ፣ ደዌን ሁሉ፣ እና በሽታን ሁሉ ይበታትናል።

124 "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ በውኑ እንዲያ ነውን? ታዲያ ለምን፡ በአንዳንዶች ላይ ይሰራል፡ በሌሎች ግን ለምን አይሰራም? " ትላላችሁ፡

125 በአውታሩ ምክንያት ነው። እዩትና ፈትሹት። ነገር ግን **እዚሁ** አቅጣጫ፡ **ወደዚህ፡** የሚመለከት መሆን አለበት። **ከዚያ** ከውጭ፡ ወደ ውስጥ አይደለም፡ ከውስጥ ወደ ውጭ መመልከት አለባችሁ። አያችሁ? በአመክንዮ ማለፍ አትችሉም። በሌሎቹ ነገሮች መምጣት አትችሉም። በቀጥታ ወደ ነፍስ፡ ወደ እግዚአብሔር አውታር እለፉ። እንዴት ነው የምታደርጉት? የመጨረሻው አውታር ማን ነበር?

126 ከዚያ ወድያው... ማመካኘት ይጀምራል። ስሜት፡ ብላችኋል አይደል፡ "ኦህ፡ እንዲህ—ይሰማኛል። አዎን፡ ይህ ነው። አህ-ሃህ። ኦህ፡ ሊሽተኝ—ይችላል፡ ወዘተረፈ። እንዲህ እንዲያ አለኝ። አዎን።" ቀጥላችሁም፡ ታመካኛላችሁ፡ "አቤት፡ ይህ ሰው የሚናገረውን የሚያውቅ ይመስላል። ዶክተሩ አትድኚም ብሎኛል። ሳይሆን አይቀርም።" አያችሁ፡ ስህተታችሁ—እዚህ ጋር ነው። በፊታችሁ የቆመው ዲያብሎስ ነው። እነዚህ ወደ እናንተ ለመጨመር የሚጣጣረው ዲያብሎስ ነው። አትመኑት።

127 "ሃሌ ሉያ! የእግዚአብሔር ቃል እኔ አደርገዋለሁ ብሏልና... 'ከሁሉም በላይ፣ በጤና እሰጣችኋለሁ' ብሎናል። ትክክል ነው።" ኃያል ሰራዊት መሆን የምትችሉት እንዴት ነው? አያችሁ፡ "'በጤና የበለጸጋችሁ እንድትሆኑ እመኛለሁ።'"

128 እዚህ ላይ ነው፡ እነዚህ፡ እነዚያ አውታሮች፡ አምጥታችሁ፡ ክፈቷቸው። አትለፏቸው...

129 ሕሊና እና ሌሎች ነገሮች ተጠቅሞ፡ ሰይጣን መግባት ሲፈልግ፡ ዝም ትሉታላችሁ፡ እነዚህ ሁሉ አልፎ ወደ ነፍስ በር ድረስ፡ ወደ አእምሮ ይመጣል። እንግዲህ፡ ከያዛችሁ... መጀመሪያ **እዚህ** እንዲገባ እስካላደረጋችሁት ድረስ መቼም—መቼም ቢሆን እነዚህ አታዩም። እንዲገባ ታደርጉታላችሁ እንጂ። ከዛ በኋላ ገብቶ፡ ይቆጣጠራችኋል። ከዚያስ ምን ያደርጋል? ህሊናን መጠቀም ይጀምራል። **ይህንን** መጠቀም ይጀምራል። **ያንን** መረብ መጠቀም ይጀምራል። የትኛውን? ማየት፣ መቅመስ፣ መዳሰስ፣ ማሽተት፣ መስማት፣ ምናብ፣ ሕሊና፣ ትዝታ፣ አመክንዮ፣ ፍቅር። ከገባ ብኋላ፡ **እዚህ** ካለው ከትንሹ በበለጠ፡ እነዚህን የተለያዩ አውታሮችን መጠቀም ይጀምራል። አስቀድሞ ግን፡ ወደ አእምሮአችሁ ይገባል፡ እናንተም ትቀበሉታላችሁ። ሊሆን የሚችለው... ይሄውላችሁ። ሊታገላችሁ ይችላል፡ ነገር ግን እስካልተቀበላችሁት ድረስ ሊቆጣጠራችሁ አይችልም።

130 ሰይጣንም ወደ ሔዋን በቀረበ ጊዜ፡ "ታውቃላችሁ፡ ፍሬው ደስ የሚል ነው፡" ሲላት፡ ለአፍታ ቆም አለች። ኦህ፡ የተሳሳተችው፡ ያኔ ለአፍታ ስታቆም ነው።

131 በከንቱ አትቁሙ። መልእክቱን ይዛችኋልና። ኢየሱስ ህያው ነውና። እግዚአብሔር መድኃኒት ነው። መልእክቱም ይህ ነው። በከንቱ አትቁሙ፡ አታመካኙ፡ ሌላ ሌላ አትበሉ።

132 እሷ ግን ለአፍታ ቆመች። ሰይጣን ወደ አእምሮዋ የገባው ያኔ ነው። “ነገሩ፡ ምክንያታዊ ይመስላል፡” አለች። ኦህ፡ እንዲህ አታድርጉ። እግዚአብሔር የተናገረውን ብቻ ውሰዱ።

133 አብርሃም፡ ከሣራ ልጅ እንደሚወልድ ሲነግረው፡ በአመክንዮ ቢቆም ኖሮስ፡ እርሰዋ ስድሳ-አምስት እርሱ ሰባ-አምስት ነበሩና? እሱ መቶ፡ እርሰዋም—እርሰዋም ዘጠና በነበሩ ጊዜም፡ አሁንም፡ በጽናት፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን አ—አ—አመነ። ያልነበሩትንም፡ እንዳሉ አርድርጎ፡ ቆጥሯልና። አያችሁ? ተሰፋን... እንኳ ሳይቀር፡ ተሰፋስ ነበረ ወይ? ጭራሽ ተሰፋን አልተጠቀመም።

134 “ስሙኝ፡” አንዳንዴ፡ “ይሻለኛል ተሰፋ አለኝ። ደህና እንደምሆን ተሰፋ አደርጋለሁ። መንፈስ ቅዱስ እንደምሞላ ተሰፋ አደርጋለሁ ትላላችሁ። ክርስቲያን እንደሆንኩ ተሰፋ አደርጋለሁ። **ይህን** እንደማደርግ ተሰፋ አደርጋለሁ።” ይህ አያስፈልጋችሁም።

135 አብርሃም ያንን አይቶት እንኳን አያውቅም። አሜን። “ተሰፋን አሰወግዶ፡ እምነቱን በእግዚአብሔር ቃል ላይ አደረገ።” እምነት ከተሰፋ በላይ ነው። እምነት የሚመጣው፡ **ከዚህ** ከውስጥ ነው። እምነት የሚመጣው **ከዚህ** ነው።

136 እንዴት ይገባል? በዚህ አእምሮ፡ በዚህ—በር፡ የጦር ግንባሩ እዛው ይዘጋጃል።

137 አሁን፡ ውጊያው ተደራጅቶ መፋጠጥ ሲጀመር! አሁን ዲያብሎስ፡ ዛሬ ጠዋት፡ በእያንዳንዱ ሰው ልብ ተቀምጧል። በዚች ህጻን ልጅ ልብ ቁጭ ብሏል። በልቦቻችሁ ውስጥ ተደላድሏል። በዙርያው ሁሉ አለ። “ኧረ፡ ከዚህ በፊትም ስትሞክሪ አይቼሻለሁ። ከዚህ በፊትም ሰምቼሻለሁ፡” እያላችሁ ነው።

138 ገሰጻችሁ አሰወጡት። በቃ። አሰወጡት። መጽሐፍ ቅዱስ፡ ጽሑፋችን ምን ይላል? “አሰወጡት።” ትክክል። “አሰወጡት።” ስልጠና ተሰጥቶናል።

139 ሳሰበው፡ “እኛ ሰባኪዎች ችግራችን ምንድነው? ” የወሰድነው ስልጠና ያሰገርመኛል።

140 እግዚአብሔር ለዚህ ታላቅ ውጊያ ስልጠና እየሰጠ ነውና። በማቴዎስ 24 ላይ፡ እና ዳንኤል 12 ላይ፡ ተናግሯል፡ “በምድር ላይ፡ ከዚህ ቀደም ሆኖ የማያውቅ መከራ ይሆናል።” እኛም አሁን እየኖርንበት ያለነውን ዘመን፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ በባህል፣ በትምህርት፣ እና በሌላ ሌላ ነገር ተሸፍኖ፡ ወደ ምክንያት እና ልዩ ልዩ ነገሮች ተገብቷል። ውጊያው አሁን ነው። የሚጸና ማን ነው? ሃሌሉያ! ውጊያው ለመጀመር በተጠንቀቅ ላይ ነው። አሁን ተፋጣለች። ማዶ ላይ እንዴት ያለ ተገዳዳሪ እንዳለን ተመልከቱ።

141 እንደ ዳዊት የሚሆን ማን ነው? ማን እንዲህ ይላል፡ “ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ የእግዚአብሔርን ሰራዊት ሲሳለቅ ዝም ትሉታላችሁን? እኔ ወርጄ እዋጋዋለሁ።” አሜን። ዛሬ ጠዋት እግዚአብሄር “እንደቃሉ አደርጋለሁ፡” የሚሉ ወንዶች እና ሴቶች እንዲነሱ ይፈልጋል። አሜን። **ይህም** ያም የትም

ይሂዱ፡ **ሌላውም** ምንም ያድርግ፡ **ምንምም** ይውረድ። ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም። እናንተ ሳኦሎች፡ እና ሌሎች ሆይ፡ ከፈራችሁ፡ ወደ ሰፍራችሁ ተመለሱ። የእግዚአብሔር ሰራዊት ግን ወደ ፊት እየገሰገሰ ነው፡ አሜን፡ ብርቱዎች፡ የ-የ-የእምነት አርበኞች፡ ኃያላኖች፡ አሰተዋዮች እየገሰገሱ ነው። ብልጥ መሆን አይጠበቅባቸውም። የተማሩ መሆን አያስፈልጋቸውም። አውታር ብቻ ይሁኑ። እግዚአብሄር ታናናሽ አውታሮች ያሰወግዳል።

142 ሄዋን ሰለ አመክንዮ፡ ለአፍታ ቆም አለችና፡ "እንግዲህ፡ አሁን፡ እሰኪ እንየው፡" አለች። እንዲህ፡ ቢሆንስ፡ እንደ...

143 ይህች እመቤት፡ ዛሬ ጠዋት፡ ሞት አፋፍ ላይ ናት ብሎ፡ ዶክተሩ እንደነገራት አያጠራጥርም፡ "ምንም ማድረግ አንችልም" ብሏታል። እንግዲህ፡ ያ፡ ዶክተሩ ነው። አልኮንነውም። ሰውዬው የሳይንስ ሰው ነው። በሽታው የልጅቷን ሰውነት በልቶ አይቷል። ከአቅም በላይ ነው። በሽታውን ማሰቆም የሚቻልበት መድኃኒት የለውም።

144 ካንሰሩ ሴቲቱን ያሸንፋታልን፡ አዎን፡ ሞት ህጻኗን ያሸንፋታልን፡ ይሁን እንጂ የዚህ ታላቅ ሰራዊት፡ አዛዥ ፡ ሃሌሉያ፡ ትንሣኤና ሕይወት ራሱ ነው። እሱ በማንም አይሸነፍም። ሃሌሉያ!

145 የሰራዊቱ ሁሉ አእምሮ፡ ወይም እውቀታቸው የሚቀመጠው አዛዦች ላይ ነው። በጀርመን፡ የጀርመን አእምሮ፡ ሮሜል ነበረ፡ ሂትለር አይደለም። ሮሜል ነው! እውነት ነው። ኤሲንሃወር! ፓተን! የጦር አበጋዞች ናቸው! ግንባር ላይ የተሰልውፉ ሰዎች፡ መመርያው የሚሰጡበት መንገድ ወሳኝ ነው። ትክክለኛ ጀነራል ከሆነ፡ አዛዦችሁን ተከተሉት። ትክክለኛ ከሆነ፡ ባለ አራት-ኮከብ ጀነራል ከሆነ፡ የተረጋገጠ ከሆነ፡ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጫ ካላችሁ፡ ተከተሉት። አንዳንዴ፡ ትክክል ሆኖ ባይሰማችሁም፡ ወደ ግንባር ዝመቱ። ያዘዛችሁን ፈጽሙ።

146 J-e-s-u-s የሚሉ ኮከቦች ያሉት፡ f-a-i-t-h በተባሉ አምስት ከዋክብት ባለ መዓርጎች ያደረገን፡ ባለ አምሰት-ኮከብ ጀነራል አለን፡ ሃሌሉያ! በጦርነት ተሸንፎ አያውቅም። ሃሌ ሉያ! ሞትን፡ ሲኦልን፡ እና መቃብርን ድል ነሰቷል። ዲያብሎሰን ሁሉ ከፊቱ ጠራርጓቸዋል። ታላቅ አዛዥ ነው። ዲያብሎስ፡ በዚህ ሰዕል ላይ ፈጽሞ ሊቆጠር አይችልም።

147 የውጊያዎች ሁሉ አውራው ውጊያ፡ አሁን ተዘጋጅቷል። አዎን፡ ዝግጁ ነው። ኦህ፡ ሃሌሉያ!

148 ሳሰበው! ቆሜ እሱ የሚያደርጋቸው ነገሮች አይቻለሁ፡ ነግሮችን ሲገልጥ፡ ነገሮችን ሲከፍት፡ "**በዚህ** እና **በዚያ** ይሆናል፡" ሲል ተመልክቻለሁ፡ ይኸው ሆኗል! ኦህ፡ **ወደዚህ** ተመልሳችሁ እያያችሁ፡ "ይህ ታላቅ አዛዥ ማን ነው፡" ትላላችሁ? ኦህ፡ እኔ እንደሆነ፡ ዶክተር **እከሌ-እና-እከሌ** ነው ብዬ፡ አልዞርም። አዛዡ የሚለውን እመለከታለሁ። "የመዳናችን ራሰ እሱ ነውና።" ሃሌሉያ! መዳን ምንድነው? ነጻ መውጣት! ክብር ይሁን! "ነጻ የመውጣታችን ራሰ እሱ ነው።"

149 ታላቁ የሰልፍ ሰዓት ደርሷል። ሃሌሉያ! ተዋጊዎች፡ እሰከነ አብረቅራቂው ትጥቃቸው፡ እሰከነሚውለበለብ ቀለሞቻቸው! ዛሬ ጠዋት፡ በዚህ ጉባኤ፡ እምነት እና ጥርጣሬ፡ ተፋጣችኋል፡ በአንዱ ወገን ጥርጣሬ፡ በሁለተኛው ወገን

እምነት። ተዋጊዎች ሆይ፡ የንጋት ኮከቡ፡ አዛዣችን፡ እየመራ ነውና። ሃሌሉያ! ምሽጋችሁን ጠብቁ። በፍጹም ወደ ኋላ አይልም። ማፈግፈግ የሚሉት ቃል (በጭራሽ) አያውቀውም። አዎን። አያፈገፍግም። አሜን።

150 የውጊያዎች ሁሉ አውራው ውጊያ፡ አሁን እዚሁ እየተካሄደ ይገኛል፡ የሰ፡ ስር፡ ውጊያው በሞት እና በህይወት መካከል፡ በጤና በህመም መካከል፡ በእምነት እና በጥርጣሬ መካከል፡ ኦህ፡ ማይ፡ በባርነት እና በነጻነት መካከል ነው። ውጊያው ተጀምሯል! ተዋጊዎች ሆይ፡ ጦራችሁን አዘጋጁ። ትጥቃችሁን ወልውሉ። እግዚአብሔር ተዋጊዎች እያዘጋጀ ነውና። እግዚአብሔር ሰራዊቱን ቀብቷልና። አሜን።

151 አሜሪካውያን ወታደሮቻቸውን ማልበስ በሚችሉት ሁሉና በሚያገኙት፡ በበለጠ ትጥቅ፡ በብረት ራስ ቁር፡ በታጠቁ ታንኮች፡ ሊያገኙት በሚችሉት ትጥቅ ሁሉ፡ ያስታጥቃሉ።

152 እግዚአብሔር ሰራዊቱን አስታጥቋል። ሃሌሉያ! ምን አይነት ትጥቅ እንጠቀማለን? የሰይፉ መንፈስ፡ የእግዚአብሄር ቃል! አሜን! “የእግዚአብሔር ቃል ሁለት-አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፡” ዕብራውያን 4፡ “ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፡ እስከ አጥንት—መቅኔ ድረስ፡ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል።” የእግዚአብሔር ቃል! ቃሉን ማመን፡ እግዚአብሔር የሚያስታጥቅበት መንገድ ነው።

153 ሔዋን እንድትታጠቅ የሰጣት ያ ነው። ትጥቋን ሰበረች። እንዴት አርጋ ሰበረችው? አእምሮዋን ለአመክንዮ ሰለከፈተች። እናንተ ግን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ምክንያት አታብዙ። ሰበብ የለውም። የእግዚአብሔር ቃል ነው... አለቀ። መቼም—መቼም ቢሆን አያጠራጥርም። አመክንዮ የለበትም። የእግዚአብሔር ቃል ነውና። አለቀ። ደቀቀ። ለዘለአለም እራት ነጥቡ ይህ ነው።

154 ምን እንደፈለግኩ አየሽ፡ እናት? [ሴቲቱም “አሜን፡” አለች።—አርታዒ።] እግዚአብሔር ቃል ገባ። እግዚአብሔር ተናገረ። የእግዚአብሔር ቃል ነው።

155 አብርሃምን፡ “ልጅ እንደምትወልድ እንዴት ታውቃለህ” አሉት?

“እግዚአብሔር ተናግሯል።” አለቀ።

“ታዲያ፡ ለምን አልወለድክም? ”

156 “እግዚአብሔር ተናግሯልና፡ እወልዳለሁ። መቼ እንደምወልድ አላውቅም። ይህ ምንም አያሰቆመኝም።” የጠራኝ-...

157 “ለምን ወደ መጣህበት ቤትህ፡ አትመለሰም? ”

158 “በዚህች ምድር እንግዳና መጻተኛ እሆናለሁ።” አሜን!... ? ... “የተሰፋው ቃል የሰጠኝ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ራሱ በላከኝ ምድር ውስጥ ልጅ ይሰጠኛል።” ሃሌሉያ!

159 እግዚአብሔር እናንተን በላከበት በዚህ በመንፈስ ቅዱስ ድባብ ውስጥ በትክክል ይፈውሳችኋል። እግዚአብሔር ይሰጣችኋል። እመን ብቻ። አሜን። የነፍስ እና የሥጋ፣ የስሜት፣ እና የሕሊና ማስተንፈሻዎችን ክፈቷቸው፡ የእግዚአብሄር ቃል ዘልቆ እንዲገባ፡ አእምሮን ቀድሞ እንዲቆጣጠር ፍቀዱለት። የጦር አውድማው ነውና።

160 “እንግዲህ፡ የእግዚአብሔር ክብር ሲወርድብኝ ከተሰማኝ፡ ስሜቱ ከነካኝ! ኦህ!” አትበሉ። ይህ ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም፡ በምንም።

161 ያንን አእምሮ ክፈቱት። የጦር አውድማው ያ ነውና። ጦርነቱ የሚፋፋምበት ቦታ፡ እዚሁ አእምሮአችሁ ፊት ለፊት፡ ላይ ነው። ክፈቱትና፡ “ጥርጣሬን... በሙሉ፡ ጥርጣሬዬን ጠረጠርኩት፡” በሉት። አሜን። “አሁን ጥርጣሬዬን ጠረጠርኩት። ሰይጣን ሆይ፡ መጣሁብህ። የእግዚአብሔርን ቃል አምኛለሁና።” የሆነ ነገር ይሆናል። በእውነት፡ ይሆናል። የሰ፡ ሰር።

162 አገልጋዮቹን በመንፈሱ ይቀባል። መላዕክትን ይልካቸዋል። አንዳንዴ፡ ሰዎች ያንንም ያፌዙበታል፡ “መላእክት።” ለአፍታ ያክል—አብረን የሆነ ነገር እንድንከፍት፡ ፍቀዱልኝ። ለአፍታ ያህል፡ ዕብራውያንን አብረን እንከፍታለን። ዕብራውያን 4ኛ ምዕራፍ፡ 4ኛ ምዕራፍ፡ ማለቴ... ዕብራውያን 1ኛ ምዕራፍ፡ 14ኛው ቁጥር እንከፍታለን።

> **ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው፡ ለማገዝ** የሚላኩ... **የሚያገለግሉም፡ መናፍስት** አይደሉምን?
>
> ... **ከመላእክትስ**... **በቀኜ ተቀመጥ** ከቶ ለማን ብሎአል... ?
>
> **... የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ...**

163 አሁን እዚህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ መጥቶ እዚህ ጋር፡ እግዚአብሔር መላእክትን እንደሚልክ ይነግረናል። ክብር ይሁን! ምንድን ናቸው? “የሚያገለግሉ መናፍስት ናቸው።” ክብር ይሁን! የሚያገለግሉ መናፍስት፡ (ከየት) ይልካቸዋል? ከእግዚአብሔር መገኘት። ምን ሊያደርጉ? ቃሉን እንዲያገለግሉ። አሜን! የአንዳንድ የእምነት ተቋም ኅራ አንዳንድ ሥነ መለኮትን ለማገልገል ሳይሆን፡ ቃሉን ለማገልገል ነው። አለቀ። “የሚያገለግሉ መናፍስት፡ ተልከዋል።”

164 መሆናቸውን እንዴት እናውቃለን? መጽሐፍ ቅዱስ “የጌታ ቃል ወደ ነቢያት ይመጣል፡” ብሏል። ልክ ነው? እነዚህ መላእክት በመንፈሱ በኩል፡ ቃሉን ያገለግላሉ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ቃሉን ያገለግላሉ። መንፈስና ቃልም ወደ ነቢያት ይመጣል፡ ነብያትም የእግዚአብሔር ቃል ነበራቸው። ያደረጓቸውን ተአምራት ሊያደርጉ የቻሉት በዚህ ምክንያት ነው። በሰውየው ውስጥ የነበረ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው እንጂ፡ ከሰውየው አይደለም፣ በሰውየው ውስጥ የነበረ የክርስቶስ መንፈስ ነው። ምክንያቱ... የእግዚአብሔር ቃል ምን ስላደረገ? አውታሮቹ ሁሉ ጠራረገ። እግዚአብሔር መርጦታልና፣ በመንፈስ ቅዱስም ተቀባ። ስለዚህ ከሱ አይደለም። በራእይ ካላየ በቀር ምንም ማድረግ አይችልም። ኤልያስም በቀርሜሎስ ተራራ፡ “ይህን ሁሉ ያደረግሁት በትእዛዝህ ነው። አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ አምላክ እንደ ሆንህ ይታወቅ፡” አለ። አቤት፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

165 የእግዚአብሔር መንፈስ በአንድ ቦታ ሲወርድ፡ ያኑኑ ቦታም፡ በቅብዓቱ ስር ሲሆን ብዙ ጊዜ አይቻለሁ! ዛሬ ጠዋት ይህ እዚህ ያለ ትንሽ ቡድን፡ ጥርጣሬዎችን በሙሉ፡ ከዚህ አእምሮ ማስወገድ ብቻ ቢችል! ሙታን—ሙታን ተነሥተው፣ አንካሶች ሲሄዱ፣ ዕውሮች ሲያዩ፣ ደንቆሮዎችም ሲሰሙ እያያችሁ፣ ወደ ፊት እንዴት ትጠራጠራላችሁ?

166 የጌታ መልአክ ሥዕሉ ሳይቀር፡ ሳይንስ ያተመበት፡ በየስፍራው፡ ግድግዳ ላይ ተሰቅሏል። እናንተ ከቃሉ ጋር ጽኑ። አሜን! ምን ያደርጋል? ዲያብሎስን በሙሉ ይቆራርጠዋል። አዎን፡ ይቆራርጠዋል። ምንድነው? "ከእግዚአብሔር ፊት የተላኩ፡ የሚያገለግሉ መናፍስት፣" ከቃሉ ጋር የሚጸኑ፡ የቃሉ ተናጋሪዎች ይቀባሉ። ምልክቶችን በማስከተል ቃሉን እያጸና፣ ኢየሱስን ትናንትና፣ ዛሬ፣ እና ለዘላለም ያው ያደርገዋል። እነሆ እሱ።

167 እሱ በሳይንሳዊ፣ በቁሳዊ፣ በመንፈሳዊ፣ ሊረጋገጥ በሚችልበት መንገድ ሁሉ፡ **እዚህ** ሲረጋገጥ፡ እንዴት እንጠራጠራለን?

168 ምንድነው ችግሩ? በአእምሯችን ውስጥ ነው። ለነገሩ አእምሯችንን ከፍተን፡ እንዲህ እንላለን፦ "እስኪ፡ አሁን፡ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል አላውቅም። ምናልባት፡ ነገ ከተሻለኝ እንላለን።" ኧረ፡ ይሄም ከሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

169 ብዙ ጊዜ እንዳልኩት፡ ሣራ የሴትነት ዕድሜዋ—ያለፈባት ነበረችና... አብርሃም ተናግሯታል ብዬ አስባለሁ። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገብቷችኋል፡ ህይወት ያማፍራት ጊዜዋ፡ ሃያ-ሰምንት ቀናትዋ። አሁን፡ የስድሳ-አምስት ዓመት ሆናለች። ምናልባት፡ አሰራ አምስት፡ እና ሃያ አመታት አልፈውባታል። ምናልባት፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ እየመጣ፡ "ውዴ፡ የተለየ ስሜት የለሽም፡" ብሎ ይጠይቃታል?

"ምንም አዲስ ነገር የለም።"

170 "ለነገሩ፡ ከሱ ጋር ምንም አይገናኝም። ወደዛ እያመራን ነንና። መቼም፡ አሁን፡ እንደገና ወደ—ወጣትነት ሴት መመለስ ከጀምርሽ፡ ከሕይወት ደም፡ ማወቃችን አይቀርም፡ ስለዚህ፡ ያኔ፡ ህጻኑን ለመጸነስ መዘጋጀትሽን፡ እና ነገሩ ሁሉ ትክክል እንደሚሆን እናውቃለን። አሁንስ፡ ዛሬ የተሰማሽ አዲስ ስሜት አለ? ቃል ከገባልኝ አንድ ወር ሆኖታል። ውዴ፡ ልዩ ስሜት አለሽ'ዴ? "

171 "ምንም የለም፡ አብራሃም። ምንም የምንም ምልክት የለም። አይ— አሁንም ላለፉት ጥቂት አመታት እንደነበርኩኝ—አሁንም ያው እንደዛው ነኝ። የተለየ ነገር ምንም የለም።"

"ለማንኛውም፡ መውለዳችን አይቀርም። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!"

172 "አብራሃም ሆይ፡ እሺ... እየህ፡ ቃል ከገባልህ'ኮ፡ በእውነት **በዚህ** መልኩ፡ ምልክት ሊሰጠን ይገባል። በእርግጥ ምልክትን ይሰጠናል።" ሆ! ሃሌ ሉያ!

173 "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይሻል።" ትክክል። ምልክት ነበረው። ምልክቱ ምን ነበር? የእግዚአብሔር ቃል። ምልክቱ እሱ ነበር።

174 እግዚአብሔር ይህን ልጅ እንዴት ይፈውሰዋል? ስሜት ተሰማኝም፡ አልተሰማኝም፡ የእግዚአብሔር ቃል ስለተናገረ ይፈወሳል። እንደው... ምንም ቢፈጠር፡ እግዚአብሔር ከተናገረ፡ ሆነ ነው።

175 "ሻርፕሽን እና ሌላ ሌላ ነገሮችሽን ሁሉ ሸክፊ፡ ወደ ምድሪቱ እንሄዳለን፡" አለ አብራሃም።

"ወዴት እየሄድክ ነው? "

176 “እኔ አላውቀውም።” አሜን። “ለማንኛውም ግን፡ እንሄዳለን። መሄዳችን ነው!” ሁሉንም አሻሽጎ እየሄደ ነው። ሃሌ ሉያ! እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። በፊቱ ያለው ስሕበት ምን ነበር? “ሄደን እንወርሳታለን።” የሚል የእግዚአብሔር ተሰፋ ቃል፣ የእግዚአብሔር ቃል።

177 “አብርሃም ሆይ ከሕዝብህ መካከል ተለይ። ዋናው ነገራቸው፡ ተጠራጣሪዎች፡ እና የማያምኑ መሆናቸው ነው። አንተንም በተመሳሳይ ወጥመድ ያጠምዱሃል። ውጣ። እራስህን ለይተህ፡ ኑርልኝ።” ምንድነው? “ሕሊናህን እና ስሜቶችህን በሙሉ፡ እንዲህ ጣላቸው። አእምሮህን ክፈተው፡ እኔ ነኝ፡ አስታውስ። ና፡ ከእኔ ጋር ኑር።” አሜን።

178 እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘር ሁሉ፡ ዛሬ ጠዋት ወደዚያው ዓይነት ሕይወት እየጠራ ነው። አሁን፡ በመላው ዓለም ታላቅ ውጊያ አለ። እግዚአብሔር ልጆቹ ከምን እንዲለዩ ይፈልጋቸዋል? ከማየት፣ ከመቅመስ፣ ከመዳሰስ፣ ከማሽተት፣ ከመስማት፣ ከምናብ፣ ከሕሊና፣ ከትዝታ፣ ከአመክንዮ፣ ከሰሜታዊ ፍቅር፡ ከሁሉ። አእምሯቸውን ይከፍታሉ የእግዚአብሔር ቃል እንዲሰርጽ ይፈቅዳሉ፡ ከዛ በኋላ ከቃሉ ጋር ይዘምታሉ። እውነተኛ ወታደር ማለት ይህ ነው።

179 ከዋክብት የጸኑት በዚህ ነው። ሶላር ሲስተሙ፡ ዞዲያክ እስከ አሁን አልተቀየረም። የንጋት ኮከብ ምድር በተፈጠረች ጊዜ እንዳስቀመጠው፡ በየማለዳው በተጠራበት ጥሪ ላይ ይወጣል። የምሽት ኮከብ፡ ኮከቦች ሁሉ ሰፍራውን ይተካሉ። ትንሹ ዲፐር፡ ወቅቱን ጠብቆ፡ መገኘት ባለበት ሰፍራ ይታያል። የሰሜን ኮከብ ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ ይጸናል። ሃሌ ሉያ! የሰሜን ኮከብ በምድር መሃል ስለሚገኝ፡ ነገሮች በሙሉ፡ በዙርያው ይዞራሉ።

180 ያ ማለት ክርስቶስ ነው። አሜን። ቆሞ፡ ሠራዊቱን እንደ ብርቱ አዛዥ ያዛቸዋል።

181 ሙሴም እስራኤልም መንገዳቸውን ለማስከፈት ሲዋጉ፡ በተራራው ላይ፡ እጆቹን ወደላይ እንደዘረጋ፡ እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ ቆሟል። ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ ቆሞ ዋለ። እጆቹን ደግፈውለት ነበር። ይህ ሙሴ ነበር።

182 እርሱ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። እጆቹ ወደ ላይ እንደሚሰቀሉ ያሳይ ነበር፡ ማለት በምሰቀል ላይ ተቸነከሩ። ሃሌ ሉያ! እናም ዛሬም፡ በደም በተለወሰ ልብሱ በእግዚአብሔር ፊት፡ ወደ ክብር ግንብ፡ ወደ ግርማው ቀኝ ወጥቷል። ስለዚህ መንገዱን ለማስከፈት፡ ለሚዋጋ ሰራዊት ሁሉ፡ ይከፍትለታል። ምንም ቢገጥማቸው አይገደኝም፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ግን፡ የነጻነታቸው መንገድ ያስከፍታሉ። አሜን።

183 ለምሳሌ እንቁላል ውስጥ ያለ ጫጩት፡ መፈልፈልን ቢፈራስ? እንቁላሉን መቆፈር ቢፈራስ? በእንቁላል ውስጥ ያለው ጫጩት፡ ወይም ትንሽ ወፍ፡ የእንቁላሉን ቅርፊት መምታት ቢፈራስ? ከውጭ የሚሰማው ድምጽ፡ “ቅርፊቱን አትምታ፡ ራስህን ትጎዳለህ፡” ሲለው ቢሰማስ? ተፈጥሮ ግን፡ በወፏ ውስጥ፡ “ቆፍረው! ምታውና ቀዳዳ ክፈት፡” ትለዋለች።

184 ያረጁ ድርጅቶች ሁሉ፡ “የተአምራት ዘመን አልፎዋል። እራስህን ትጎዳለህ። አክራሪ ትሆናለህ” ቢሉህም።

185 አንተ ግን ባለ በሌለህ ኃይልህ፡ ቅርፊቱን ምታው። ሃሌ ሉያ! “ሰይጣን ሆይ ራቅ! ከዚህ እየወጣሁ ነው።” አለቀ። “ከእንግዲህ፡ ወድቄ ተኝቼ አልኖርም። ከእንግዲህ፡ ቁጭ ብዬ አልኖርም። ያረጀው ሰይጣን እውድማ ሰፍራዬ አይደለም። ዛሬ ጠዋት፡ መንገዴን ለመቅደድ እቆፍራለሁ። አሜን። እኔ ንሰር ነኝ።” አሜን! ሃሌ ሉያ!

186 ትንሹ ንሰር ግን፡ ከውስጥ ያለው አንገተ ሞደሻ ግን፡ ቅርፊቱን ይደበድባል። ቅርፊቱ ምንም ያህል ቢጠነክርም፡ ዝም ብሎ በሰቶ ይወጣል። እንደምታውቁት፡ ያኔ የሚሆነው፡ የመጀመርያው ነገር፡ ክንፎቹን በሰሱ ያራግባል። አሁን ደህና ነው።

187 መውጫህን ቅደድ። አዎን። እንዴት ታደርገዋለህ? **“የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡”** በሚል ቅደደው። በመጨረሻም፡ ንጹህ አየር ማሸተት ትጀምራለህ። **“የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።”** ጭንቅላትህ ወደ ውጭ ብቅ ይላል። **“የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።”** አሁን በኃይል ግፋው፡ አሁን ወጥተሃል!

188 ከዛ በኋላ ነፃ ነው። እንደገና ወደ ቅርፊቱ አይመለሰም። አሜን። ኦህ፡ ማይ! ያ ቃል ከሰሜቶች እና ከሕሊናዎች ሌላ ነገር አልፎ፡ እዚህ አርፎ ለመደላደል፡ አንዴ **እዚህ** ገብቶ ከተቀመጠ፡ አእምሮም ከፍቶ ያስገባዋልን። አምላክ ሆይ፡ ማረን! ዳግመኛ የሚያሰርህ ነገር አይኖርም። ነፃ ነህ። ልጁ ነጻ ያደረገው ሁሉ ከቅርፊት ውጪ ነውና። የሐይማኖት ተቋምህ ተመለሰ አይሉህም። ከዛ በኋላ ዲያብሎሰ፡ ማልቀሰ እና ማንቋረር ይችላል። ምንም ሊያደርግብህ ግን አይችልም።

189 አንተ በአውራው ጎዳና፡ በኃይለኛ ፍጥነት መሮጥ ጀምረሃል፡ ኦህ፡ ማይ፡ በንጉሱ አውራ ጎዳና፡ የተቀባ የመሰቀሉ ሰራዊት ሆንነህ ሩጫ ላይ ነህ። እናንተ ንሰሮች ሆይ፡ ኢየሱሰን የዓለም ብርሃን እንደሆነ፡ በእምነት አውጁ፡ በንጉሱ አውራ ጎዳና ሩጡ። አዎን። የሰ፡ ሰር!

190 አገልጋይዮች ለመሆን፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩ “የሚያገለግሉ መናፍሰት አሉ፡” (ምን) ለማገልገል? ቃሉን፤ ሥነ መለኮትን ሳይሆን፡ የእግዚአብሔርን ቃል። እንዲያገለግሉ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩ፡ አገልጋይ መናፍሰት ናቸው። አገልጋይ መናፍሰት! ኦህ! እሰታውሱ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ትተው፡ ሌላ ነገር ካገለገሉ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደሉም። ምክንያቱ፡ “ቃል ሁል ጊዜ በሰማይ የተረጋገጠ ነው።” እግዚአብሔር፡ ቃሉን፡ በሰማይ-... ሁል ጊዜ፡ ይጠብቀዋል። ከቃሉ ውጭ የሆነን ነገር የሚያገለግል መንፈሰ በፍጹም አይልክም።

191 ከታላቅ ፒኤችዲ፣ እና ዲ ዲ ዲ፣ አንገትጌ ጀርባው ላይ ያዞረ መንፈሰን፡ እና የመሳሰሉ ነገሮች፡ “ኧይ፡ ተው ባክህ፡ የተአምራት ዘመን አልፏል። ሁላችንም እናውቀዋለን፡” የሚሉትን፡ በጭራሽ አይልክም። አይልክም፡ አይልክም። ያ ከእግዚአብሔር የመጣ አይደለም። ከቃሉ ጋር ተቃራኒ ነው። አሜን።

192 የቃሉን መንፈሰ የሚያገለግሉትን ይልካል። አሜን።

193 ኦህ፡ አራት ወይም አምስት ተጨማሪ ነገሮች ነበሩኝ፣ ግን በዚህ ጊዜ እተወዋለሁ፣ በሚቀጥለው እሁድ አነሣቸዋለሁ። እሺ።

ሰይጣንና አጋንንቱም የተቀቡ ናቸው።

194 እነዚህ መልአክ መናፍስት ቃሉን እንዲያመጡላችሁ፡ ቃሉን እንድታምኑ የተቀቡ ከሆኑ፡ ነብይ ሆኖ የእግዚአብሄርን ቃል የሚክድ፡ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ነብይ፡ አይታችሁ ታውቃላችሁን? [ጉባኤው "አላየንም፡" አሉ።—አርታዒ።] ኖ፡ ሰር። በየዘመናቸው የነበሩት ተቋማት እየተነሱ፡ "እርሱ ተሳስቷል" ሲሏቸው፡ ምን ይፈጠር ነበር? አንዱ ብቻውን ይጸናል፡ ብቻዉን ይቆማል። "ትክክል ነው፡" ይላል።

195 የይምላ ልጅ ሚክያስን፡ ያ ሆሊ-ሮለር፡ ያኔ ያደረገውን፡ ተመልከቱት። የተቀቡ ናቸው የሚባሉት፡ አራት መቶ፡ የተቀቡ ነቢያት በዚያ ቆመው ነበር፡ ሁሉም በደንብ የበሉ፡ በደንብ የሰለጠኑ፡ ሁሉም በትልልቅ ዲግሪ የተመረቁ፡ ከፍተኛ ትምህርት የተማሩ እና የተመራመሩ ምሁራን ነበሩ። ሁሉም፡ "ንጉስ ሆይ፡ ሂድና ተከናወን። ጌታ ከአንተ ጋር ይሁን። የኛ ናት። ኢያሱ የሰጠን ርስታችን ናት። ወርደህ ውረሳት። ይህ እውነት ነው። ወርደህ ውረሳት። ወዘተ… " "እየህ፡ ኢዮሳፍጥ-… " አለው፡

196 ኢዮሳፍጥ፡ ምን እንዳለ ታውቃላችሁ፡ እንግዲህ አራት መቶዎቹ በፊቱ እያሉ፡ "ከሌላ ቦታ፡ ሌላ የለምን? " አላቸው። አራት መቶዎቹን ለምን አላመንካቸውም? "ይሁን፡ በእርግጥ፡ ሌላ ቦታ የቀረ፡ አንድ መኖር አለበት፡" አለው።

197 እንዲህ አለው፡- "እ—እ… አዎን፡ አንድ አለ። ሌላ አንድ አለ፡ ግን፡ ኦህ፡ እጠላዋለሁ።" ሆ! አያችሁ?

198 "እኔ፡ መስማት የምፈልገው፡ እሱን—ነው።" "እሱን አምጡት። ምን እንደሚለን እንስማው፡" አላቸው።

199 እነርሱም ሄደው፡ እንዲህ አሉት፡ "አሁን፡ ሰማ። ዛሬ ስብከትህን በትክክል አዘጋጅ፡ ዛሬ ጠዋት፡ የምትሰብከው ንጉሱን ነው። እየህ፡ የምትሰብካቸው… እነ **እከሌ-እና-እከሌ** የተባሉትን፡ የፍልሰጤም—የአገልጋዮች ማኅበር በሙሉ፡ መላው የአገልጋዮች ማኅበርን ነው። አሁን፡ አስተውል፡ እነሱ ያሉት እንዲህ እና እንዲህ ነው። አንተም ተመሳሳይ ነገር ተናገር። አብረሃቸው እመን።" ይህ ምስኪን…

200 ከባድ ሰው—ገጠመው። ያ ሰው ከዚህ አሮጌ አስተሳሰብ የራቀ ነው። አያችሁ፡ ጭስ ማውጫዎቹን ህሊናውን ሁሉ፡ አጽድቷል።

201 "አንተም፡ አሁን፡ እየህ፡ ምን እንደሚያደርጉልህ ታውቃለህ? ተመሳሳይ ነገር ከተናገርክ፡ የወረዳው ቄስ ያደርጉሃል ብዬ እሰባለሁ። ሳያደርጉህ አይቀሩም። አንተም—ከእነርሱ ጋር ከተሰማማህ፡ እዚህ ላሉት አጥቢያዎች ሊቀ ካህን—ያደርጉሃል።" እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው አልነበረም።

202 ለምን፡ የጭስ ማውጫው ተጠራርጓል፡ ሕሊናው ሁሉ እና ሁሉም ነገር ንጹሕ ሆኗል። አእምሮው ለእግዚአብሔር ቃል ተከፍቷል። የሚያምነው፡ የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ነው። አገልጋይ መናፍስት ነው። አገልጋይ መንፈስ ያ ነው።

203 እንዲህ አላቸው፦ “አሁን ምን ማለት እንዳለብን አላውቅም። እኔ አንዲት ነገር እናገራለሁ፡ ይህም፡ እግዚአብሔር ተናገር ያለኝ ብቻ እናገራለሁ።”

ሌሊቱን በሙሉ ጠበቁት። እና ራዕይ አየ።

204 በሚቀጥለው ቀን ጠዋት፡ ሚክያስ መጽሐፍ ቅዱሱን ሲያጠና፡ ሲናገር ይታየኛል፡ “አሁን፡ እንመርምረው እስኪ። ከራእዩ ጋር... ሰዎቹ ሁሉ፡ በሆነ መልኩ ችግር አለባቸው፡ ነገሩ፡ ይሆናል ካሉት በተቃራኒኒ ነው። እሺ፡ የተባለውስ ምን ነበር? በነብዩ በኤልያስ፡ ቀድሞ የተባለው እንመርምር፡ ነብይ እንደነበረ ሁላችንም እናውቃለንና። አያችሁ... አዎን። የጌታ ቃል ወደ ኤልያስ መጣ። ምን አለው? ‘ኤልዛቤል፡ ውሾች ይበሏታል። ውሾች ደምሽን ይልሳሉ። ይህም በጻድቁ አክዓብ... ማለቴ በጻድቁ በናቦቴ ምክንያት ነው።’” ወድያውም... ያን ባየ ጊዜ እንዲህ አለ፡ ራእዩ ከእግዚአብሔር ቃል ቀጥተኛ መሆኑን፡ አስተዋለ፡ ሽማግሌው አክዓብም ወደ እርሱ መጣ።

205 ፊት ለፊት ሄዶ፡ ተናገረው፡ “አንተ ሂድ ተከናወን። እስራኤልን ግን አይቼዋለሁ... ” አያችሁ፡ ያኔ ቃሉ ከጌታ ዘንድ ስለሆነ፡ ራእዩን ለመናገር አልተሸማቀቀም። ያንን ነገር በትክክል መውሰድ እንደሚችል አውቋል። ምንድነው? ልቡን፣ አእምሮውን፣ ለእግዚአብሔር ቃል ከፍቷል፣ የእግዚአብሔር ቃልም ተመልሶ ተገለጠለት፡ ስለዚህም ፍጹም የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አወቀ።

206 አሁን፡ “ኦህ፡ እኔስ ሚኪያስ መሆን በቻልኩ!” ያላችሁ ሰዎች፡ መሆን ትችላላችሁ። እንዲሁም ናችሁ። አንቺም፡ ነሽ፡ ማር። አንቺም፡ ነቢዩ ሚክያስ ነሽ። ምን ማድረግ ትችያለሽ? አእምሮሽን ክፈቺ። ዛሬ ጠዋት ምን እየነገርኳችሁ ነው? የጌታ ቃል። አያችሁ? አእምሮአችሁን ክፈቱት፣ “አሁን፡ መዳን እንደምችል፡ አሁን እምናለሁ፡” በሉ። ታዲያ፡ ይህ ምንድነው? የጌታ ቃል ነውን? በእርግጥ ነው፡ የጌታ ቃል ነው።

207 እና **ይህ** ሰው፡ እንዲህ ይላችኋል፦ “የተአምራት ዘመን አልፏል። **ይህን** ማድረግ አትችልም። አንተ... ” እርሱት ናቁት። እግዚአብሔርን አሰቀድሙ።

208 እነሆ የጌታ ቃል ወደ እርሱ መጣ፡ እርሱም ተናገረ፡ እንዲሁም ሆነ።

209 ከዛስ፡ ሰይጣን ምን አደረገ? ሰይጣን ሌሎች የተቀቡ ነበሩት። እንግዲህ፡ ሰይጣንም አገልጋዮቹን ይቀባል። ኦህ፡ በትክክል። አህ-ሃህ። በትክክል። አገልጋዮቹን ይቀባል። በምን ይቀባቸዋል? በአለማመን ይቀባቸዋል። ሰይጣንና አጋንንቱ የእግዚአብሔርን ቃል ላለማመን የሰውን ልጆች ይቀባሉ።

210 አሁን፡ ያንን ማረጋገጥ ከፈለጋችሁ፡ ዘፍጥረት 3:4 እንክፈት። እስቲ ወደዚያ ተመልሰን ይህንን፣ ለአንድ ደቂቃ ያህል እናዳምጥ፡ እና ያ የመጀመሪያ ስልቱ ይሁን አይሁን እንይ። መጀመሪያ ያደረገው ይህ ነው። ተመሳሳይ ስልቱን አይተወውም። ደጋግሞ ያደርገዋል። አሁንም፡ ያ እንደሆነ ብቻ እንየው—ያ ነው። እሱ ቃሉን አልተቃወመም። ታውቃላችሁ፡ በሰሱ እድታጣምመው ብቻ አደረጋት፡ እሱ እንዲሰማ በሚፈልገው መንገድ እንዲሰማት አደረጋት፡ ሙሉውን ቃል እንዳትቀበል አደረጋት። አሁን፡ ዘፍጥረት፡ እዚህጋ፡ ዘፍጥረት 3:4 ይዣለሁ። የተባለው እንደዚያ ከሆነ እንመርምር፡ አሁን።

**እባቡም ሴቲቱን፡ በእውነት ሞትን አትሞቱም፡**

211 “በእውነት ሞትን አትሞቱም።” እንዴት እርጎ ዙርያውን እንደጠቀሰላት አያችሁ? “ኦህ፡ የተአምራት ዘመን ማለፋን እናምናለን። ሰዎች በጰንጠቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስን እንደሚቀበሉ አይነት ነገር አለ ብለን እናምንም። ኦህ፡ በማንኛውም መንገድ ተጠመቅ፡ ምንም ለውጥ አያመጣም።” ሰይጣንን አያችሁት? ስልቶቹን አያችሁ? “በቃ፡ ዶክተሩ አትድኚም ካለሽ፡ አለቀ።”

212 አሁን፡ ዶክተሩን ማንቋሸሼ፣ እሱን አለማመን አይደለም። ዶክተሩ በሳይንሳዊ መስክ እየሰራ ነው። ዶክተሩ የግለሰቡን ህይወት ለማዳን የተቻለውን ሁሉ አድርጓል፡ መዳን አይችልም፡ ከዚህ በላይ ሊያደርግላት የሚቻለው ነገር የለውም። የእውቀቱን ጥግ ላይ ደርሷል። ሰውየው ቅን ነው። አሁን፡ የእውቀት ዛፍም፡ ምንም ችግር የለውም፡ ነገር ግን መጓዝ እስከሚችለው ርቀት ከተጓዘ በኋላ፡ ወደ ህይወት ዛፍ ውረድና መንገድህን ቀጥል። አሜን። አለቀ። እስካሁን ድረስ ይሰራል። አዎን።

213 አሁን የሰይጣን ዘዴ፡ ምን እና ምን ያደርጋል? እዚህጋ ምን አለ? አሁን 1 እና—2ኛ ቁጥር ተመልከቱ። አሁን—ከ1ኛ ቁጥር ጀምሬ፡ እስከ 3 ድረስ ላንብበው።

> **እባቡም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አራዊት** ሁሉ ይልቅ፡ **ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፡** በውኑ፡ **እግዚአብሔር፡ ከገነት ዛፍ ሁሉ... እንዳትበሉ፡ አዝዞአልን አላት?**

214 ምን ያህል አሰቀያሚ እንደሆነ፡ እና—ቃሉን ምን ያህል እንደቀባባው፡ አሁን ሰሙት። አያችሁት? ምን ማድረግ... ፈልጎ ነው? ወደ አእምሮዋ ለመግባት። አያችሁ? ቃሉ እዚያ ውስጥ ከመሸገ በኋላ፡ መጥቶ እያነጋገራት ነው።

215 ሰይጣን መጥቶ፡ ምንም አይነት ምሽግ እንዲሰራባችሁ አትፍቀዱለት። አያችሁ? የእግዚአብሔር ቃል ብቻ በልባችሁ ውስጥ ይመሽግ። አያችሁ? እናንተም፡ ሚኪያሶች ሆይ። እናንተም እንዲሁ አድርጉ።

> **... ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፡ በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፡** ነገር ግን...
>
> **በገነት መካከል** (አያችሁ፡ በመካከል) **ካለው ከዛፉ ፍሬ ግን፡ እግዚአብሔር... አለ፡ እንዳትሞቱ፡** ከእርሱ **አትብሉ አትንኩትም።**

216 አያችሁ፡ ይህም፡ ቃሉ ነው። ቃሉን መልሳ እየጠቀሰችለት ነው። አሁን ተከታተሉ።

> **እባብም ለሴቲቱ አላት፡ በእውነት ሞትን አትሞቱም፡**

217 ዘዴዉን አያችሁት? ምን ለማድረግ እየሞከረ ነው? አያችሁት? ከሰው ዘር መካከል፡ የመጀመርያዋ፡ የእግዚአብሔር ሴት ልጅ፡ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስክዳት ቅባት ሊቀባት እየሞከረ ነው። እሷ እንድታደርገው የሚፈልጋት ነገር ያ ነበረ።

218 ማር፡ አንቺም እንድታደርጊው የሚፈልግሽ ያንን ነው። እናንተንም ቀብቶ፡ ሁላችሁም፡ እንድታደርጉት የሚፈልጋችሁ ይህ ነው። አሁን እናንተ ማድረግ የምትችሉት ብቸኛው ነገር... ነጻ የሞራል ምርጫ ስላላችሁ። ከፈለጋችሁት

ተቀበሉት። እናንተ ግን አባርሩት። ሄዋን፡ እሱን ለመስማት ባትቆም ይሻላት ነበር! ለተራ ነገር አትቁሙ። አትቁሙ።

219 ኤልያስ—ጊያዝን፡ እንዲህ ባለው ጊዜ፡ “በትሬን ወስደህ፡ በሞተው ህጻን ላይ አኑረው። ማንም ቢያናግርህ፡ አትመልስ። ማንም ሊያሰቆምህ ቢሞክር፡ ዝም ብለህ ቀጥል አለው።”

220 ሴትየዋ ሎሌዋን ስትጠራው ተመልከቱ። “በቅሎ ኮርቻ አድርግና ወደ ፊት ሂድ፡ እኔ ካላዘዝኩህ፡ አትቁም።” አለቀ።

221 መልእክቱን በተቀበላችሁ ጊዜ፡ ቀጥሉ። አሜን። “መራመድ አልችልም። አዎን አሁን፡ ችያለሁ! ኑህ፡ እየደከመኝ ነው።” ሌላውን ሁሉ ጥለህ፡ ዝም ብለህ ቆፍር። ቀጥል፡ አታቁም፡ ወንድሜ፡ ሰይፉን በእጅህ ይዘሃልና፡ ዝም ብለህ ቁረጠው።

222 አንድ ጊዜ፡ ሰብከት ለመሰበክ፡ ወደ እግር ኳስ ስታዲየም ገባሁ። እና በሩ ላይ ቆሜ፡ ወደላይ አየሁ። እንዲህ ይላል፡ “ውጊያው የሚያሸንፈው የውሻው መጠን ሳይሆን። በውሻው ውስጥ የውጊያው መጠን ነው።” ውጊያውን የሚያሸንፈው ያ ነው። አያችሁ?

223 “እንግዲህ፡ ተመልከት። ታላላቅ ቸርቾች ሁሉ ይሄን ይቃወሙታል፡” ትሉኛ ይሆናል።

224 ምንም ያህል ግዙፋን ይሁኑ አይገደኝም። ዋናው ነገር፡ በውሻው ውስጥ ያለው የውጊያው መጠን ነው። በግለሰቡ ውስጥ ያለው እምነት ነው። ፈሪ ከሆንክ ወደ እልፍኝህ ተመለስ። አንተ ግን፡ ወንድሜ፡ ወታደር ከሆንክ፡ ጸንተህ ቁም። ውጊያ እየተካሄደ ነው። እውነት እና ስሕተት ተፋጠዋል። እንዋጋ።

225 ልክ እንደ ፒተር ካርትራይት፡ ወደ ከተማ ገባና፡ “ጌታ እዚህ ገብተህ—ሪቫይቫል አድርግ ብሎኛል፡” አለ። አንድ አሮጌ መጋዘን ተከራይቶ፡ እዚያ ገብቶ ማጽዳት ጀመረ።

226 እና ትልቅ የከተማው ጉልበተኛ፡ ጎኑ ላይ ሽጉጥ አንጠልጥሎ፡ ወደ ታች ይወርዳል። በሮች ተከፍቷል… አንዳንዶችም አሉ፦ “ሰውየው እዚያ ምን እያደረገ ነው? ”

227 “እኔ ሰባኪ ነኝ። ሰብሰባ አደርጋለሁ፡ ብሏል፡” አሉት።

228 እንዲህ አላቸው፡ “ነው’ዴ፡” “ሄጄ ወደ መንገድ እወረውረዋለሁ፡ ከዚህ አባርረዋለሁ። በቃ። በአከባቢያችን ምንም አይነት ሰብሰባዎች አያስፈልጉንም።”

229 ወደዚያ ወርዶ፡ በሩን ረገጠው። እና ፒተር ካርትራይት ኮቱን ለብሶ ነበር፣ ታውቃላችሁ፣ እና መስኮቶቹን እና ግድግዳውን እያጠበ ነበር። አጠር ያለ ወንድም ነው፡ ታውቃላችሁ።

230 እንደምታውቁት፡ ዛሬ ዛሬ የማይደረግ አይደለምና፡ ዶሮ በእጅ ስለ መብላቱ፡ ሽማግሌው ሰባኪ ሳቀበት፡ ታውቃላችሁ።

231 ስለዚህ ዙርያውን ሁሉ እያስተካከለ መስኮቶቹን እያጠበ ነበር። ጉልበተኛው፡ ሽጉጥ ጎኑ ላይ አንጠልጥሏል፡ ሄደና ኮቱን ጎትቶ፡ “እዚህ ምን ታደርጋለህ፡” አለው?

232 “ኦህ፡” አይ፡ “መስኮቶቹን እያጠብኩ ነው” አለውና። ዝም ብሎ፡ መስኮቶቹን ማጠብ ቀጠለ። አላማው አንድ ናት። እግዚአብሔር ሪቫይቫል አድርግ ብሎታልና። መስኮቶችን ወደ ታች፡ ያጥባል።

“እዚህ አካባቢ ሪቫይቫሎችን አንፈቅድም፡” አለው።

233 “ኦህ፡ ጌታ ግን—ይህን ሪቫይቫል እንዳደርግ አዞኛል፡” አለው። አያችሁ? መስራቱን፡ ቀጠለ። አያችሁ? አያችሁ?

234 “ስማ፡” አለው፡ “አንድ ነገር—ማወቅ አለብህ።” “ከተማዋን የምመራት እኔ ነኝ፡” አለው።

235 “ኦህ፡ አንተ ትመራታለህ? ” አለውና፡ እንዲሁ፡ መስኮቶቹን ማጠብ ቀጠለ።

236 “ሪቫይቫል ከማድረግህ በፊት፡ እኔን ከዚህ ማስወገድ ይጠበቅብሃል፡” አለው።

“ኦህ፡ ይጠበቅብኛል’ዴ? እሺ፡ ቀጣይ ስራዬ እሱ ይሆናል፡” አለው።

237 ኮቱን ብቻ አወለቀ። ወደዚያ ሄዶ፡ አንገትጌውን ያዘውና፡ ወለሉ ላይ ዘረረው፡ ከዛ በላዩ ላይ ዘሎ ወጣበት። “ጌታ ሆይ፡ ለመንገስ፡ መታገል አለብኝና፡ ድፍረትን ጨምርልኝ፡” አለና። ወጥ በወጥ አረገው።

“አሁንስ ይበቃሃል? ” አለው፡

238 “አዎን፡” በቃኝ አለው። ተነስቶ እጁን ጨበጠው። ያን ቀን ማታ ላይ፡ ቸርች ውስጥ ጌታን ተቀበለ።

239 እንዲያ ነው። አያችሁ? የእግዚአብሔርን ቃል አንሱና ጥርጣሬዎችን ሁሉ ቁረጡ። አያችሁት? አዎን፡ ይህ ነው። ቀጣይ ስራችን ያ ነው፡ እንጨርሰው። ልክ ነው። ቀጣዩ ስራዬ ጥርጣሬን ማስወገድ፡ መቁረጥ ነው። ቀጣይ ስራዬ፡ ዉጣ ውረዶችን ማስወገድ ነው። ስሜቶቼ፡ “መጥፎ ስሜት፡ እየተሰማህ ነው፡” ብለው ከነገሩኝ፡ ቀጣዩ ነገሬ ያንን መቁረጥ ነው። ትክክል።

240 “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ስለ’ኔ... እንግዲህ፡ እንዲህ ነህ ይሉኛል... ታውቃለህ፡ ሕሊናዬም... እንዲህ ይለኛል... ” ካላችሁ፡ ምናልባት፡ ያ ነገርም መቁረጥ ይኖርባችሁ ይሆናል። ከዚያ ተጉዛችሁ ብዙም ርቃችሁ አትሄዱም። ቀጣይ ስራችሁን ፈጽሙ። ኮታችሁን አውልቃችሁ ግቡበት። ዝም ብላችሁ ቀጥሉ። ግባችሁ አንድ እሱም “አሸንፋለሁ ይሁን፡” አሜን። “አሸንፋለሁ እንጂ፡ አልሸነፍም።” ይሁን። አሜን።

241 አያችሁ? ሰይጣንም ይቀባል። የመጀመርያው ስልቱ ምንድነው? መጀመርያ መግባት የሚፈልገው ሰፍራ ምንድነው? አእምሮ። እሷ የሚናገራትን ለመስማት ለአፍታ ቆመች። “ተው እንጂ፡ አትለኛም? ”

242 ብዙ እንስቶች ስህተት የሰሩበት እዚያ ላይ ነው፡ ብዙ ወንዶችም የተሳሳቱት እዚህ ላይ ነው፡ ትክክል፡ ለአፍታ ቆም አለች፡ በቃ ለአፍታ ቆመች። በዚህ ላይ፡ እንዲህ አይነት ነገሮች ላይ ስንት ጊዜ የፍቺ ጉዳዮችን አይቻለሁ።

243 “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ልንገርህ፡ እውነት እልሃለሁ፡ ‘ዊት-ዊው’ አርጎ፡ አፏጨብኝ፡ ከዛ በኋላ፡ እኔም፡ ቆምኩኝ፡ እውነት እልሃለሁ እኔ—ፈልጌው አይደለም።” አህ-ሃህ። ይሄው ነው።

244 “ኦህ፡ ትንሽ ራቅ ብዬ፡ አጠገቧ ካለው ወንበር ተቀምጬ ነበር። አይኖቿ—በጣም ያማምራሉ!” አየህ? አህ-ሃህ። አያችሁ? በቃ።

245 ዲያብሎስ ስራው ተመሳሳይ ነው። “ኦህ፡ ዶክተሩ አይሻልህም ብሎኛል፡ ስለዚህ... ” ይሄውላችሁ፡ ተመልከቱ፡ የውጊያዎች ሁሉ አውራው ውጊያ፡ ይህ ነው።

246 “እንዲህ ብለው፡ ነግረውኛል... **እከሌ-እና-እከሊት** መንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ ሲሉ ሰምቻለሁ።” አዎን፡ አንዳንድ ግብዞችን አየተሃል። በትክክል ስለተሞሉትስ ምን ትላለህ? አህ-ሃህ። አዎን። ዲያቢሎስ አንዳንድ የቁራዎች ወጥመድ ይጠቁምሃል፡ እውነተኛውን እርግብ ግን አያሳይህም። አህ-ሃህ። ትክክል ነው። አያሳይህም፡ ያንን ግን ከአይኖችህ ሰውሮ ያቆይብሃል።

247 ኦህ፡ እሱም፡ ተዋጊ ነው፡ ይህን አትርሳ። የኛ ግን ከሱ ይበልጣል... “በዓለም ካለው ይልቅ፡ በእናንተ ዘንድ ያለው ይበልጣል።” እናንተ እዚህ ያላችሁ የሰራዊት አዛዦች ሆይ፡ የእግዚአብሔርን ቃል አጽንታችሁ ያዙ፡ እመኑት። ወንድሜ፡ ምሽግን አጽና። አዎን፡ ጥሪአችሁን አጽኑ።

248 አንድ ጊዜ፡ አንድ ምስኪን ሴት፡ ገጠመችኝ። ምናልባት ዛሬ እዚህ ልትኖር ትችላለች። ስሟ ኔሊ ሳንደርስ ትባላለች። ለመጀመሪያ ጊዜ ሰይጣን ሲወጣ ያየሁት ያኔ ነው። አሁን፡ ካስታወስኩት፡ የነበርነው፡ ከመካነ መቃብር ተሻግሮ፡ ሶስት ጎዳናዎች አለፍ ብሎ ነበር። ገና ሰባኪነት የጀመርኩ ጊዜ ነውና፡ እዚህ ጥግ ላይ፡ ድንኳን ጥየ እየሰበኩ ነበር።

249 እና ይህች ሴት ከምርጥ ዳንሰኞች አንዷ ነበረች። እሷ እና ሊ ሆርን፡ ሃይስኩል የተማሩት እዚህ ነው። ከተማ ውስጥ ያላችሁ ብዙዎቻችሁ ሊ ሆርን ታውቃላችሁ፡ የመዋኛ ገንዳ ክፍል ሐላፊ ሆኖ ይሰራል። ሁለቱ፡ እሷ እና ሊ ሆርን፡ በአገሪቱ ውስጥ ካሉ ምርጥ ዳንሰኞች ነበሩ። እሱ ራሱ፡ ካቶሊክ ነው። እርግጥ ነው፡ ሃይማኖት ለእነርሱ... ለኔሊ እና ለሌሎቹ፡ ምንም ማለት አይደለም። ብቻ ታላቅ ዳንሰኛ ነበረች፡ እሱም፡ እንዲሁ ነበር። እና እዚህ አካባቢ “ብላክ ቦተም፡” እና “ጂተርበግስ፡” እና ሌላ ሌላ የሚሉት ዳንስ ነበራቸው። ያኔ እሷ... ሁለቱም በአገሪቱ ውስጥ አሉ የተባሉ ዳንሰኞች ነበሩ።

250 አንድ ቀን፡ እዚህ፡ አንድ ምሽት፡ ወደ ጉባኤው ገባች። እና ምስኪኗ ኔሊ፡ በመሠዊያው ላይ ወደቀች። ልቧ ብሩክ ይሁን። መሰውያው ስር ወደቀች። ከዛ ጭንቅላቷን ቀና አደረገች። አለቀሰች፣ እንባውም በጉንጯ ላይ ይወርዳል። “ቢሊ... ” አለችኝ፡ ታውቀኛለች። “በጣም፡ መዳን እፈልጋለሁ፡” አለችኝ።

251 እኔም አልኳት፦ “ኔሊ፡ መዳን ትችያለሽ። ኢየሱስ አስቀድሞ አድኖሻል፡ እመቤት። እንደ ቃሉ መሰረት አሁን መቀበል ይገባሻል።”

252 ባለችበት ቆመች። አለቀሰችና፡ ጸለየች፡ ዳግመኛም የዓለምን ነገር እንደማትሰማ ለእግዚአብሔር ነገረችው። ድንገት፡ በአንድ ጊዜ ደስ የሚል ጣፋጭ ሰላም በነፍሷ ላይ ወረደ። እና እግዚአብሔርን እያመሰገነች፡ እየጮኸች፡ ከዚያ ተነሣች።

253 እና ከዚያ በኋላ ከሰድስት ወይም ከሰምንት ወር ገደማ በኋላ፡ አንድ ምሽት፡ ወደ ስፕሪንግ ስትሪት ትወርድ ነበር።

254 ያኔ፡ ገና ወጣት ልጅ ነች፡ ገና በአሥራዎቹ ዕድሜዋ፡ የአሥራ ሰምንት ዓመት ልጅ ነበረች። ወደ'ኔ መጣችና፡ "እንደ ሆፕ… " በሆንኩ አለችኝ፡ ሆፕ የቀድሞ ሚስቴ ናት፡ አሁን እርፏለች። "እንደ ሆፕ እና እንደ አይሪን ብመስል እመኛለሁ፡" አለችኝ። "ታውቃለህ፣ እነሱ'ኮ ዓለምን ፈጽመው አያውቁትም፡" አለችኝ። "ዓለም ጠባሳ ትተውልሃለች፡" አለችኝ። "እኔም ፊቴ ተጠብሷል፡" አለችኝ። እንዲህ አለች፡ "አሁን፡ ሜክ-አፕ እና አሸንክታብ ትቻለሁ፡ ፊቴ ግን ጠባሳ ነው። ፊቴ ሳይቀር፡ ተላልጧል፡" አለችኝ። "አላምርም።" "እነሱ ግን መልከ መልካም እና ለሰላሳ ናቸው፡" አለች። "ያንን ፈጽሞ ባላደርገው ደስታዬ ነበር፡" አለች።

255 "ኔሊ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል፡ ማርዬ። ቀጥይ እመኚው፡" አልኳት።

256 ዌይን ብሌሶ፣ ብዙዎቻችሁ ታውቁታላችሁ፣ የብዙ ዓመታት፡ ውድ ጓደኛዬ ነው። እና ሰካራም ነበር። እናም ከወንድሜ ኤድዋርድ ጋር፡ ወደዚህ መጣ። እና ጎዳናው ላይ ሰክሮ፡ ፖሊሶች ሊወስዱት ሲሉ፡ ሄጄ አነሣሁት። እና ወደዚህ አመጣሁት። እና እኔ ሰባኪ ነበርኩ እና እዚህ፡ ገና ከማግባቴ በፊት፡ ከእናቴ እና ከአባቴ ጋር እኖር ነበር። ወሰጄው እዚያ አልጋ ላይ አስተኛሁት። እና ታጣፊ አልጋ… ላይ ተኛሁ። ብራንሃሞች ብዙ ቤተሰብ ነን፣ ታውቃላችሁ፣ አሥር ነበርን። እና ሰለዚህ አራት ያህል ክፍሎች ነበሩን፡ እና ትንሽ፡ ታጣፊ ማድረግ ነበረብን። ስለዚህ፡ የምተኛበት የድሮ ታጣፊ ነበረኝ። **እንዲህ** ሰቤ አወጣሁትና፡ እና—እና ዌኒን ከእኔ ጋር አስተኛሁት። ሰክሯል፡ ተሸክሜ ቤት ውስጥ ማስገባት ነበረብኝ።

257 እና እንዲህ ተኝቼ ነበር። "ዌይን፡ እንዲህ ስትሆን፡ ትንሽ አታፍርም ወይ? " አልኩት፡

258 እርሱም።"ኧረ፡ ባክህ ቢሊ፡ እንደዛ አትበለኝ፡" አለኝ።

እጄን ዘረጋሁና። "ዌኒ፡ እግዚአብሔር ይባርክህ። አሁን እጸልይልሃለሁ፡" አልኩት። እኔም ገና ከዳንኩ፡ ምናልባት፡ አንድ አመት አካባቢ ይሆነኛል።

259 እና፡ ድንገት፡ ፖሊሰ—መሣይ፡ የሆነ ሰው፡ በሩን ከውጭ መታውና፡ በኃይል ማንኳኳት ጀመረ። "ወንድም ቢል! ወንድም ቢል!" [ወንድም ብራንሃም መድረኩን አንኳኳ—አርታዒ።]

260 "ወይ ጉድ፡ የሆነ ሰው፡ ሳይሞት አይቀርም፡" ብዬ አሰብኩ። ተነሳሁ፡ ወደ በር ዘለልኩ፡ ያረጀውን ጨርቅ ያዝኩና፡ **እንዲህ**፡ ፒጃማዬ ላይ ጣል አድርጌ፡ ዌኒን አለበሰኩትና፡ ወደ በሩ ሮጥኩ።

261 ሴት ትመሰላለች። በሩን ከፈትኩት፡ እና ይህች ሴት በሩ ላይ ቆማለች። "ኦህ፡ ልግባ? " አለችኝ።

መብራቱን አበራሁትና፡ "ግቢ፡" አልኳት።

262 ዝም ብላ ታለቅሳለች፡ "ወይኔ፡ ቢሊ፡ በቃ—በቃ—በቃ ጉድ ሆንኩ! ጉድ ሆኛለሁ!" ብቻ ትላለች፡

263 "ምን ገጠመሽ ኔሊ? ምንድነው—የልብ ድካም አጋጠመሽ? " አልኳት፡

264 “አልገጠመኝም፡” አለች። እና እንዲህ አለች፡ “ወንድም ቢል፡ ከሰፕሪንግ እየተመለኩ ነበር።” “እውነት እልሃለሁ፡ ወንድም ቢል! የእውነት፡ ወንድም ቢል፡ በክፋት አልነበረም። ክፋ አሰቤ አልነበረም፡” አለችኝ።

265 “ምን ሆንሽ? ” አልኳት፡ “አሁን ምን አደርጋታለሁ? ” ብዬ አሰብኩ፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። እኔ፡ ገና ምንም የሌለኝ ወጣት ነኝ። እና...

266 “ኦህ፡ ወንድም ቢል፡” አለችኝ። “እንጃልኝ—እንጃልኝ—እንጃልኝ ብቻ ተዋርጃለሁ፡” አለችኝ።

“አሁን ተረጋጊና እህት። ስለ ጉዳዩ ሁሉ ንገሪኝ፡” አልኳት።

267 እርሰዋም፡- “እሺ፣” አለችና፡ “በሬድማን አዳራሽ አጠገብ፡ በመንገድ ላይ እየመጣሁ ነበር... ” በዚያም የቅዳሜ ማታ ጭፈራ እያደረጉ ነበር። እና እንዲህ አለች፡- “ለራሴ የምለብሰው ልብሰ የምሰራበት ዕቃ ይዤ፡ እያለፍኩ ነበር።” “እና ሙዚቃ ሰማሁ፡” አለች። “ታውቃለህ፡” አለች። “ለአፍታ ብቻ ቆም አልኩኝ፡” አለች። “እየጣፈጠኝ መጣ። እና አንድ አሳብ አሰብኩ፡ ‘እዚህ ብቆም፡ ምን ችግር አለው፡’” አልኩኝ አለች።

268 የሳተችው እዚያው ነው፡ ለአፍታ መቆሟ። በቃ ማዳመጧ ነው።

269 እንዲህ አለች፡ “እሺ፡ እስኪ ላሰብ፡” አለች። “ጌታ ሆይ፡ እንደምወድህ፡ ታውቀዋለህ።” አለችም፡ “ጌታ ሆይ፡ እንደምወድህ ታውቀዋለህ። ግን እኔ እና ሊን—ዋንጫዎቹን፡ እና ሌላውን ሁሉ ያሸነፍንበትን ጊዜ ትዝ ይለኛል።” “አቤት፡ ያ ዘፈን እጅግ ሲመሰጠኝ አስታውሳለሁ። አሁን ግን አይሰበኝም።” አለች።

270 ኡ-ሆ፡ ኡ-ሆ! ፈጽማችሁ አታሰቡት። ወዲያውኑ፡ እዛው አጥምዷችኋል። እዛው፡ እሱ የሚፈልገው ያ ነው። አያችሁ?

271 ኔሊ ሳንድረሰን ሰንቶች ታውቋታላችሁ? አዎን፡ ሁላችሁም ይመስለኛል። በትክክል። አዎን። ያኔ እነሱ—እንዲያ—ነበሩ...

272 እና፡ እንዲህ አለች፡ “እንዴ፡ ታውቃለህ? ” “ምናልባት’ኮ ወደ ደረጃዎቹ ጠጋ ካልኩ፡” “ምናልባት የምመሰክርለት አንድ ሰው አላጣም፡” አልኩኝ፡ አለች።

273 አቤት! አያችሁ፡ በዲያብሎስ አውድማ ገብታችኋል። ውጡ ከዛ። “የክፉን ፊት ጥረጉት።”

274 እሷ ግን፡ ወደ ደረጃዎቹ ወጣች፡ እና ጥቂት ደቂቃዎችን ቆም አለች። ከዛ በኋላ ግን፡ ወለሉ ላይ ከአንድ ወጠምሻ ክንድ ሰር፡ ራሷን አገኘች።

275 ከዛ ወደ ራሷ ተመለሰች። እና ቆማ ቀረች፡ ማልቀስ ጀመረች፡ እና “አይ... ከእንግዲህ፡ በቃ፡ ላልመለስ ጠፍቻለሁ፡” አለች።

276 እና እንዲህ አሰበች፡ “እኔ፡ መጽሐፍ ቅዱስን አላውቅም፡ ኢየሱስ ግን፡ ‘በሰሜ አጋንንትን ታወጣላችሁ’ ብሎ እንደተናገረ አምናለሁ።” እ...

277 እና ዌኒ በሰሱ ነቅቷል፡ ቁጭ ብሎ፡ ማየት፡ ጀምሯል። አያችሁ? እና አልኩ፡ “አሁን፡ አንተ ዲያብሎስ፡ ማን እንደሆንክ እኔ አላውቅህም፡ እኔ ግን አሁን እልሃለሁ፡ እቺ እህቴ ናት፡ እሷን የምትይዝበት ምንም ምክንያት

የለህም። ለአፍታ ብቻ ቆመች እንጂ። ሆን ብላ አላደረገችውምና።" ጥፋትዋ፡ ያ ቢሆንም። "አሁን ግን ከሷ ትወጣለህ። ሰማህ? " አልኩት፡

278 ጌታ ሆይ፡ አቤቱ፡ አሁንስ፡ በፍርድ ወንበር ፊት እርዳኝ። ከዚያ የመስታወት በር፡ በራሱ፡ መዝጋት እና መክፈት ጀመረ። "ገርበብ፡ ገርበብ፡" እዛ በበሩጋ። "ገጭ፡ ገጭ-ቋ፡ ገጭ-ቋ።" አሳሰበኝ።

እና እንዲህ አለች፡ "ቢል፡ እየው። እየው።"

"አዎን። ምንድነው? " አልኳት፡

"እንጃ፡" አለችኝ።

"እኔም አላወቅኩትም፡" አልኳት።

279 በሩ አሁንም "ገርበብ-ገጭ፡ ሰጢጥ-ገጭ" ብሎ ተዘጋ። "ምን ተፈጠረ? ምንድነው? " አልኩኝ፡

280 በድጋሚ፡ **እንዲህ** አየሁና፡ "ልቀቃት፡ አንተ ሰይጣን! ውጣ፡ በኢየሱስ ስም!" አልኩት፡

281 ልክ እንዳዘዝኩት፡ ቁመቱ **ይሄን** የሚያክል፡ የሌሊት ወፍ የሚመስል፡ ከጀርባዋ በኩል ብድግ አለ፡ ከዊጉ ረጅም ጸጉር ወደታች የወረደ፡ **እንዲህ** ሆኖ፡ እግሩ ድረስ ወርዷል። "ኡኡውውውው፡" እያለ ተነሳ። እና በተቻለው ፍጥነት፡ ወደኔ መምጣት ጀመረ።

282 "ጌታ አምላክ ሆይ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከዚህ ይጋርደኝ፡" አልኩኝ።

283 ዊጊ ከአልጋው ላይ ዘሎ ተነሳና፡ አየ። እንደ ትልቅ ክብ ጥላ፡ ይመስላል፡ እየተሽከረከረ ሄደ፡ እና ከአልጋው ኋላ ገባ። ዊጊም በተቻለው ፍጥነት፡ ከአልጋው ወርዶ፡ ወደ ሁለተኛው ክፍል ገባ። ከዛ...

284 ኔሊን ይዤ ወደ ቤትዋ ወሰድኳት። እና ተመልሼ መጣሁ፡ አልቻልኩም...

285 እናቴ መጥታ አልጋውን እና ዙርያውን ፈተሸች። አልጋው ውስጥ ምንም አልነበረም። ምን ሆነ? ዲያብሎስ ከውስጥዋ ወጣ። ለምን? ለአፍታ ስለቆመች። ይኸው ነው።

286 ፈጽማችሁ፡ አትቁሙ። እግዚአብሔር ቃሉን በልባችሁ ውስጥ ሲያስርጽ፡ ያንን ሰይፍ ያዙና መክተፍ እና መቁረጥ ጀምሩ። ሃሌሉያ!

287 "ሌላ ለመጠበቅ ጊዜ የለኝም። ኢየሱስ ከፊቴ ቀድሞኛል፡ ጊዜ የለኝም፡ የማርፍበት ጊዜ የለኝም።"

288 እንዲህ አለው፡ "ሂድና፡ ብትሬን ወሰደህ ልጁ ላይ አድርገው። መንገድ ላይ ማንም ቢያናግርህ፡ ፈጽመህ አትመልስላቸው።"

289 ዲያብሎስ እንዲህ ሲልህ፡ "አንተ፡ ምን እየተሰማህ እንዳለ ታውቃለህ አይደል? " መልስ አትመልስለት። መንገድህን ቀጥል።

290 ዲያብሎስ፡ ታውቃላችሁ፡ እላችኋል፦ "ለመሆኑ ምን እንደሆነ ግን ታውቃለህ? **እከሌ-እና-እከሊት**፡ መንፈስ ቅዱስ ከተቀበሉ በኋላ፡ ምን እንደሆኑ ታውቃለህ፡ አእምሮአቸውን እንደሳቱ—አትርሳ እንጂ።" መልስ እንኳን አትመልሱለት። ዝም ብላችሁ ቀጥሉ። ስለ **እከሌ-እና-እከሊት** እናንተ አታውቁም።

291 አንተ እና እግዚአብሔር ብቻ ናችሁ። እውነት ነው። እግዚአብሔርን ጠብቁት። ባርያዎቹን ይቀባል። አሁን መፍጠን አለብኝ። እግዚአብሔር ባርያዎቹን ይቀባልና። እያችሁ?

292 እዚጋ ጥቂት ማስታወሻዎችን እልፋቸዋለሁ፡ ይሄን ማለት ግን እፈልጋለሁ። አሁን፡ እዚህጋ፡ በደንብ ስሙኝ።

293 አንቺ ታናሽ ሴትም፡ በደንብ ስሚኝ።

294 እዚጋ የዲያብሎስን ዘዴዎች እንይ። እንዴት አርገን? አሁን፡ ወደ ነብያት እና በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉ ሰዎች፡ ወደነሱ የመጣበት፡ ያደረገውም ተመሳሳይ ዘዴ፡ ብዙ ቃላት ይዣለሁ። የዘወትር ዘዴው ይህ ነው፡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳያምኑ ማድረግ ነው። እናንተ የመስቀሉ ሰራዊት ሆይ፡ አድምጡኝ። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን አንድ ቃል ከካዳችሁ፡ ትጥቃችሁን ፈትታችኋል።

295 ማር፡ ታምኛለሽ?

296 ትጥቃችሁን ፈትታችኋል። አንተ ጂሊፊሽ፡ ተማርካሃልና። የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልበስ። አሜን። ሰልፍ ላይ ነንና። እግዚአብሔር ያለውም እውነት ነው። እያችሁ? "የሰው ሁሉ ቃል ውሸት ነው።" ነገር ግን… እናንተን አንዲት ነገር እንድትሰሙ ካደረጋችሁ፡ ዘዴው ያ ነው፡ ትጥቃችሁን ፈትታችኋል።

297 ሄዋን ስንት ነገር በመስማት ትጥቋን ፈታች? አንድ ነገር ብቻ። ወድያውኑ ትጥቅ ፈታች። ዲያብሎስ ያደረገው ምን ነበር? ወደ አእምሮዋ ዘልቆ ገባ፡ ወደ መንፈስዋ ገባ፡ ያኔ ተታለለች። ልክ ነው አይደል? ትጥቅ እንደፈታች፡ የእግዚአብሔርን ቃል አላምንም እንዳለች፡ ወድያውኑ ተታለለች። በጣም ጥሩ። ዘዴዎቹን አይተናቸዋል።

298 የእግዚአብሔር ሰራዊት ሆይ "የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሱ፡" ተብለዋል። ልክ ነው አይደል? አሁን፡ ቃሉን መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ በኤፌሶን 6:10 እና 13 ያዙ። እያችሁ? ቀደም ብለን አንብበነዋል፡ ቃላችን ነው። በጣም ጥሩ። አስተውሉ። "የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልበሱ።" እንዲህ እናድርግ… ጥቂት ጊዜ ይኖራችኋል? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።-አርታዒ።] እስኪ ለአፍታ ወደ ኋላ መለስ እንበልና። ሙሉ የእግዚአብሔ ዕቃ ጦር ምን እንደሆነ እንመልከት። እሺ። ከቁጥር 10 እንጀምራለን። አሁን፡ በደንብ ተከታተሉኝ። ሙሉውን የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር እንየው። "በቀረውስ ወንድሞች ሆይ… " አውቄአለሁ፡ ይገባኛ… እንደው…

299 አሁን፡ ሀያ ጉዳይ፡ ለአስራ ሁለት፡ ሊሆን ነው። ዛሬ፡ ረጅም ትምህርት ላስተምራችሁ አል—አል… ፈልግኩም፡ ለክረምት ጉዞ እስክጨርስ ድረስ፡ ምናልባት ከአንድ ሌላ ተጨማሪ መልዕክት ውጪ ሌላ ላይኖረኝ—ይችላል፡ እያችሁ።

300 ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ለምን ይሄን እንደማደርግ ታውቃላችሁ? እነግራችኋለሁ። በቀደምለት ሕልም አየሁ። አሁን ለመናገር አላሰብኩትም ነበር፡ ልቤ ውስጥ ግን አለ። ጌታ ትርጉሙን ከሰጠኝ በኋላም፡ ምናልባት እነግራችኋለሁ።

301 ለወንጌል ሰራ፡ ታላቅ ወንዝ እየተሻገርኩ አየሁና። እና፡ መጀመርያ፡ ከሚስቴ ጋር ነበርኩ…

302 እዚህ ከተማ ውስጥ ጆርጅ ስሚዝን፡ ሲክስ-ሰከንድ ስሚዝን፡ የምታውቁት ሰንቶች ናችሁ? የጆርጅ ስሚዝ፡ ወንድ ልጁ እዚህ የፖሊስ አባል ነው። ምስኪን ጆርጅ፡ አሁን የአልኮል ሱሰኛ ሆኖአል። ድሮ ግን ከዋናዎቹ ተፋላሚዎች አንዱ ነበረ። እኔንም ያሰለጠነኝ እሱ ነበር፡ ወደ Y.M.C.A. እና ወደ ሌሎቹ የሄድኩት በሱ ነበር። አሰልጣኛችን ነበር። ፈጣን፡ በጣም ፈጣን ነበረ። የአንድ መቶ-አርባ-አምስት ፓውንድ፡ ዋልተርወይት ነበረ። ያሰለጠነኝም እሱ ነው። እዛጋ ይቆምና፡ ቡጢውን፡ **እንዲህ** ጨብጦ፡ ሆዼ ላይ ይመታኛል፡ አንሰቶኝ ግድዳው ላይ ያጋጨኛል፡ አያችሁ፡ ግን፡ ምንም አያስጨንቀኝም ነበር። እያሰለጠነኝ ነው፡ ስልጠና እንጂ ሌላ ነገር አልነበረምና።

303 በቀደም፡ ማታ ላይ—ህልም አየሁና፡ ሲክስ-ሰከንድ ስሚዝን አየሁት። በርግጥ፡ ራእይ አልነበረም። ህልም ነው። እና አንድ ወጣት ሰው፡ ሲክስ-ሰከንድ ስሚዝ ጋር፡ ነጻ ትግል ሊገጥመው ይመጣል። እና፡ ሽማግሌው፡ ምናልባት፡ አሁን፡ ይመስለኛል... እኔ ኃምሳ-ሁለት ነኝ። እሱ ኃምሳ-ሰምንት፡ ሰድሣ ይሆናል። ከወጣቶቹ አንዳቸውም በምንም ቢሆን፡ ጫፉን አይነኩም ነበር። በክንዱ እንዲህ ይቆልፋቸዋል፡ ከዛ ወለል ላይ **እንዲህ** ይጥላቸውና፡ በእጁ ይደግፋቸው ነበር።

304 “ይገርማል፡” ብዬ አሰብኩ። ሚስቴም ከእኔ ጋር ነበረች፡ እና “ይገርማል፡” አልኳት። “ምን እንደሆነ፡ ታውቂአለሽ ሜዳ? እሱ’ኮ አሰልጣኜ ነበረ፡” አልኳት።

“አዎን ከዚህ በፊት ነግረኸኛል፡ አ—አስታውሳለሁ፡” አለችኝ።

305 እንዲህ አልኳት፦ “የስ፡ ሰር። በውጤታማ ስልጠናው፡ አስራ አምስት የሚያህሉ ፕሮፌሽናል ተፋላሚዎችን አሸንፌአለሁ፡ እሱን ስራ—አቁሜ፡ ወንጌል ሰባኪ ሆንኩ።”

306 ወድያውኑ ተቀየረና፡ ውኃ ዘንድ—እየተሻገርኩ ነበር። ሰሄድ ግን፡ በሞተር ጀልባ ነበር የምቀዝፈው። ዙርያዬን አየሁና፡ ከጓደኞቼ ሁለቱ፡ ለመሄድ ተዘጋጅተው፡ ከእኔ ጋር በታንኳ ለመሄድ፡ ቁጭ ብለዋል። እንዲህ አልኳቸው፡ “እንዲህ አታድርጉ፡ ወንድሞች ሆይ፡ ለብቻዬ መሄድ አለብኝ። አሀ-ሃሀ።”

307 መርከበኛው መጣና፡ እውነተኛ ነጭ የፕላስቲክ ጀልባን “እንካ ይህን ጀልባ ውሰድ፡” አለኝ።

“አይ። አሀ-ሃሀ። ይህ አይሆንም፡” አልኩት።

308 “አየህ፡ ይሄን ይዘህ **በዚ** በኩል፡ በሰዓት ኃምሳ ማይልስ መቅዘፍ ትችላለህ፡” አለኝ።

አያችሁ? እንዲህ አልኩት፡ “እኔ መሻገር የምፈልገው ግን **በዚያ** በኩል ነው።”

“እሺ፡” እንዲህ አለኝ፡ “**ከነዚህ** ሰዎች ጋር አብረሃቸው ሂድ።”

309 እንዲህ አልኩት፦ “እነሱ መርከበኞች አይደሉም። ያን ያህል እውቀት የላቸውም። ደስ ስላላቸው ብቻ እንጂ። መቅዘፍ አይችሉም። ሁለቱም እዚያው ይሰምጣሉ። በቃ አይችሉም።”

እና እንዲህ አለኝ፡ “ለመሆኑ... ትተማመናለህ ግን... ? ”

310 እንዲህ አልኩት፡ “ሰማ፡ ስለ ጀልባ ከእነሱ ይልቅ—እኔ የተሻለ አውቃለሁ፡ እና በዚህ ዓይነት መሳርያ እየቀዘፍሁ፡ ይሄን መሻገር አላሰበውም” “ይሄን ለመሻገር የሞተር ጀልባ መሆን አለበት፡” አልኩት። “ከዚያ የተሻለ ነገር እጠቀማለሁ፡” አልኩት።

311 እና ከወንድሞች መካከል፡ አንደኛውን አይቶ፡ “መርከበኛ ነህ? ” ብሎ ሲጠይቀው አየሁት፡

እነዚያ ወንድሞችም “አዎን፡” አሉ። አያችሁ?

እኔም “ስህተት ነው፡” አልኩት።

312 መርከበኛው መጣና። “ምን ማድረግ እንዳለብህ እነግርሃለሁ፡” አለኝ። አለኝም፡ “ይወዱሃል። ያምኑሃል። ግን፡” “አንተ በሞተር ጀልባ ስትሻገር፡ እነሱም በታንኳው ይከተሉሃል። ሁለቱም ይሞታሉ፡ አየህ።” አለኝ፡ “ሊከተሉህ አይችሉም፡” አለኝ።

“ታዲያ ምን ላድርግ? ” አልኩት፡

313 ዳርቻ ላይ የነበረ መርከበኛውም፡ እንዲህ አለኝ፡ “**ወደዚያ** ተመለስ።” “በዚህች አገር ውስጥ አንድ መጋዘን ብቻ አለች፡ አንድ አነስተኛ መጋዘን ብቻ አለች። አንተም በቂ አስቤዛ አድርግላቸው እና አስቀምጥላቸው፡” አለኛም፦ “እዚህ ይቆያሉ። አንተ በሄድክ ጊዜ—ከአንተ በኋላ—እዚህ ይቆያሉ።” አንተ ግን፡ “በቂ አስቤዛ አቅርብላቸው፡” አለኝ።

314 ከዛ በኋላ እኔም ልዩ ልዩ ጥቅል ጎመኖች፡ እና ተርኒፖች፡ ቀይስር፡ እና ሌሎች፡ ሰብስቤ ጫንኩላቸው። ከዛ ነቃሁ።

315 እኔ ምን እንደነበረ አላወቅኩም ነበር፡ አሁን ግን አውቄአለሁ። አያችሁ፡ ወንድሞች ሆይ፡ አሁን እኛ ሁላችን አስቤዛው ፊት ቀርበናል። ይህም ብቻችሁን የምትጓዙት ህይወት ነው።

316 ሊዮ፡ መጀመርያ ወደዚህ በመጣህ ጊዜ፡ ያየኸውን ህልም ታስታውሳለህ አይደል? [ወንድም ሊዮ ሜርሴር “አሜን” አለ—እርታዒ።] ስለ ፒራሚዱ፡ አንተም ፒራሚዱ ላይ እወጣለሁ ብለህ አሰበህ ነበር። እኔም አልኩህ፡ “ሊዮ፡ እግዚአብሔር ካላወጣው በቀር። አንድ ሰው መውጣት አይችልም። ሰው ሊደርስባቸው የሚቻሉትን ሰጋዊ እድማሶች ሁሉ ደርሰህባቸዋል።” እንዲህ አልኩህ፡ “ሊዮ፡ ወደዚህ መምጣት አትችልም። አየህ? ሂድ ውረድ። ከእግዚአብሔር የመጣ እንደሆነ ለሰዎቹ ንገራቸው።” አየህ? አየህ?

317 ምንም መልካም ወንድሞች—እና እህቶች፡ እና ቤተክርስትያኔ ብትሆኑም፡ በሁሉም ስፍራ እንደሚገኙ ቸርቾች እና ወንድሞች፡ ምንም ያህል መልካሞች ብትሆኑም፡ በዚያ ሁሉ፡ መደገፍ የማትችሉት ነገር ነው።

318 አሁን፣ እዚያ ካለችው ቤተ ክርስቲያን መራቅ አልችልም። አንድ ሰው እንዲህ አለኝ፡ “ከነዚያ ሰዎች ጋር ለምን ትሆናለህ፡ እነሱ የሥላሴ አማኞች ናቸው፡ **እንዲህ፡ እንዲያ፡ ሌላ** ናቸውና፡ ዋንነስ፣ ኦንሊ ጂሰስ፣ እና ሌሎች ሁሉ ለምን ትተባበራለህ? ለመሆኑስ፡ ከነዚህ ጋራ ህብረት ለምን ታደርጋለህ? ” የእኔ ናቸው። ምንም ቢሰሩ፡ የእኔ ናቸው። ፑልፒቴ ናቸው።

319 እግዚአብሔር ሙሴን፡ እንዲህ ብሎ እስኪናገረው ድረስ፡ እስራኤል ክፉ አደረጉ፡ “እራስህን ለይ። ከአንተ—አዲስ ህዝብ ከአንተ አወጣለሁ።”

320 ሙሴ ግን ራሱን መንገድ ላይ ጥሎ፡ “እነሱን ከመግደልህ በፊት፡ እኔን ግደለኝ፡” አለው።

321 ምንም ያህል ቢበድሉም፡ እኔ የተላክሁት ለእነሱ ነው። እርሱ ብርሃንን ላከ፡ ብርሃን ባለበት እንዲያበራ አይደለም። ጨለማ ባለበት ቦታ፣ የብርሃን መገኛ ያ ነውና። ስለዚህ ከህዝቡ ጋር መጓዝ አለብህ። ምንም ያህል፡ በደል ይኑራቸው፡ በምትሄድበት ሁሉ፡ አብረሃቸው መቆም አለብህ።

322 እራኤላውያን እጅግ በደል አበዙ። እግዚአብሔር ተሰፋ እስኪቆርጥባቸው ድረስ በደሉ። ሙሴ ግን፡ እጅግ ይገርመኛል፡ እንዴት መጣለት፡ የክርስቶስ መንፈስ በሙሴ ነው። አያችሁ?

323 አያችሁ፡ ሁላችንም በድለናል። በበደላችን ሳለን ስለሁላችንም ቆመ።

324 የቱንም ያህል የተሳሳቱ ቢሆኑም፡ ራሳችንን ከምንም ነገር እናላቅቅ ወይም አንለያይ። ነፍስን ማሸነፍ እስከቻልን ድረስ ዘልቀን እንግባ “እንደ እባብ ብልህ፣ እንደ ርግብ የዋህ፡” አያችሁ፡ የቻልነውን ያህል ነፍሳትን እንማርክ።

325 አሁን፡ ዛሬ ጠዋት የምላችሁ ነገር፡ ምግብ ስለማከማቸት ነው። ምግብ ማከማቸት፡ የምትመገቡት ነገር እንዲኖራችሁ፡ የምትበሉት ነገር እንድትይዙ ነው። በቴፖቻችሁ ውስጥ ይኑር። በምቹ ክፍላችሁ ውስጥ አብጁት። ምናልባት፡ ሩቅ መንገድ ስሄድ፡ እነዚህ ነገሮች እውነት መሆናቸውን ያኔም ታስታውሳላችሁ። ክፍላችሁ ውስጥ አዘጋጅታችሁ አዳምጡ። አያችሁ?? ስለዚህ ይህ ነገር፡ በመጋዘን የሚቀመጥ፡ ምግብ ነው። ጉዞዬ ወዴት እንደሆነ አላውቅም፡ የትም ቢሆን ግን፡ ወዴት እንደሚመራኝ፡ እሱ ያውቃል፡ ዝም ብዬ እከተላለሁ፡ አላውቅም።

326 አሁን፡ እዚህ ምን ተናገረ? በጥሞና አድምጡ።

> **በቀረውስ፡ ወንድሞቼ፡ በጌታ እና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።**
>
> **... በኃይሉ ችሎት... በርቱ።**
>
> **የዲያብሎስን ሽንገላ** ትቃወሙ **ዘንድ እንዲቻላችሁ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።**
>
> **ከሥጋና ከደም ጋር አንታገልምና፡...**

አያችሁ፡ ጥይት መተኳኮስ እና በቢላ መቆራረጥ፡ አይደለም።

> **... ነገር ግን በአለቆች ላይ፣ በሥልጣናት ላይ፣ በገዢዎች ላይ... የዚህ ጨለማው ዓለም፡...**

327 “የጨለማ ገዥዎች።” ዓለምን የሚገዛው ማነው? ዲያብሎስ። በእርግጠኝነት። እነዚህ ነገሮች የሚፈጸሙት፣ እነዚህ ሁሉ ኃጢአቶች፣ በዚህ አካባቢ የሚፈጸሙት፡ የመንግስት ነገሮች፡ እና ሌላ ሌላ ነገሮች፡ የሚፈጸሙት እንዴት ነው? ሁሉም ዲያብሎስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ይላልና። ዩናይትድ ስቴትስ የሚቆጣጠር ዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ጀርመንን ተቆጣጥሯል። ዲያብሎስ በዓለም ላይ ያለውን ሕዝብ ሁሉ ተቆጣጥሯል። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ እመለስበታለሁ፡ መሆኑን አለመሆኑን፡ በግልጽ እናውቀዋለን። ወደድን ጠላን... እግዚአብሔር መንግሥቱን እስኪያጸና ድረስ፡

የድሮ መንግሥታት እና ወደፊትም የሚኖሩ ሁሉ፣ በዲያብሎስ ቁጥጥር ስር ናቸው።

328 እንግዲህ፡ በዚያ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ ዲያብሎስ ናቸው አላልኩም። በመንግስት መሰርያ ቤቶች—ውስጥ ብዙ መልካም ሰዎች አሉና።

329 በጥቂት ምሽቶች ውስጥ አንዱ እዚህ ይመጣል፡ እዚሁ፡ እዚህ ቦታ ላይ ከወንድም አርጋንብራይት ጋር ፎቶ ለማሣየት ይመጣል። ለአምስት የተለያዩ ፕሬዚዳንቶች ዲፕሎማት ሆኖ ሰርቷል፡ ወንድም ሮው ይባላል። በሚያዝያ ወር ሁለተኛ ሳምንት ገደማ ይመሰለኛል፡ እዚህ... ከእኛ ጋር ይገኛል። ማስታወቂያውን ወንድም ኔቪል ይነግረናል። በጣም ድንቅ ሰው ነው።

330 ይመስለኛል፡ በሰምንት የተለያዩ ቋንቋዎች መናገር እንደሚችል ተናግሯል። መንፈስ ቅዱስን በተቀበለ ጊዜ ግን፣ ከጌታ ጋር የሚነጋገርበት ቋንቋ አጣ፣ ስለዚህ ጌታ አንድ ሰጠው፡ ስለዚህም ከእሱ ጋር፡ በዚያች እነጋገራለሁ አለ። ፈጽሞ ያልተለማመደውን አዲስ ሰጠው። በጣም ጥሩ።

**... በሰማያዊ ስፍራ ካለው መንፈሳዊ ክፋት ጋራ።**

**ስለዚህ...**

331 አሁን እናንተ ሰራዊት በሙሉ፡ አሁን የጸሎቱን መሰመር ከመጀመራችን በፊት፡ ሰሙኝ።

**ስለዚህ... የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ** (ሁ-ሉ) (ጥቂቱን አይደለም)... **እንነሡ፡ በክፉው ቀን ለመቋቋም እንድትችሉ፡...**

አሁን እየኖርንበት ላለን ቀን ነው።

**... ሁሉንም ፈጽማችሁ፡ ለመቆም እንድትችሉ።**

**መቆም...**

332 አሜን። ገብቶሻል? አየሽ፡ ማር? መቆም የሚያስችል ነገር ሁሉ፡ ካደረጋችሁ በኋላ፡ ቁሙ። አትንቀሳቀሱ።

**እንግዲህ፡ ወገባችሁ ታጥቃችሁ ቁሙ...**

333 ምን እንደሆነ፡ ይህን ሰሙት፡ አዳምጡት። "ወገባችሁን።" **እዚህ** ጋር ያለው፡ መካከለኛው አካል፡ እያችሁ።

**... በእውነት ታጥቃችሁ፡...**

334 እውነት ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ቃል። ትክክል ነው። "ቃልህ እውነት ነው።" እሺ።

**... የጽድቅን ጥሩር ለብሳችሁ፡**

335 ይህ ማለት "ቅን የሆነውን ፈጽሙ።" ትክክል የሆነውን እያደረጋችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ያዙ። "የጽድቅን ጥሩር።"

**በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤**

336 በየትኛውም ቦታ፣ በማንኛውም ቦታ፣ በማንኛውም ጊዜ፣ እግሮች በወንጌል ተጫምተው ይሂዱ። እያችሁ? እና ተመልከቱ፡

**ከምንም** በላይ፡ **የእምነትን ጋሻ አንሡ፡...**

337 ዳርቶቹን የሚዘርረው ያ ነው፡ አያችሁ፡ “የእምነት ጋሻ።”

**... የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን.**

**የመዳንንም ራስ ቁር ያዙ፡...**

338 ያም ነፍስን ነው... አእምሮ—አእምሮን፡ **እዚህ**፡ ጭንቅላት፡ ከጭንቅላቱ በሙሉ ይሸፍናል።

**... የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ—እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡**

339 ይህን የራስ ቁር እንዴት ትጠቀሙበታላችሁ፡ ምንስ ያደርጋል? መከላከያ ነው። የራስ ቁር ከምን የተሠራ ነው? ከናስ። ናስ ቶሎ አይቀጠቀጥም፡ ከብረት ይልቅ፡ ጠንካራ ነው። የናስ ራስ ቁር፣ (ምን? ) መዳን፣ ይህን የማወቅ እውቀት፣ “ፈውሴም ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። መዳኔ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ልምምዴ ከቃሉ ጋር የሚሰማማ እንጂ፡ የአብያተ ክርስቲያናት ሃሳብ አይደለም፡ ቃል ነው!” አሜን። እነሆ። በራስ ቁር መዳን፡ እና በነጻ መውጣት፡ መከላከያ ጋር፡ ተሸፍናችኋል። ያንን ይዛችሁ፡ ወደፊት ገስግሱ። ኦህ፡ አሁን፡ ማድረግ ያለብን፡ ይህ ነውና። የሰይጣን ሰራዊትም...

340 አሁን ተከታተሉኝ፡ አሁን፡ እኛም... መፍጠን አለብኝና፡ ይሄን ግን—እንድትረዱት ማድረግ አለብኝ።

341 የሰይጣን ሠራዊት በሽታዎችን ያመጣል። ሰይጣን ይህ ነው፡ አጥፊ ነው። ሰይጣን፡ መላው የሰይጣን መንግሥት፡ ሕመም፣ ሞት፣ እና ሀዘን፣ እና ጭንቀት፣ ግራመጋባት፣ ሁሉም ከሰይጣን ነው።

እግዚአብሔር ሕይወት፣ እምነት፣ ደስታ፣ ሰላም፣ **ይህ** ነው። አያችሁ?

342 አሁን፡ እየተሳሳቡ ያሉት ሁለቱ ታላላቅ ኃይሎች እነዚህ ናቸው። እየተዋጉ ነው። አሁን እዚህ ሕንፃ ውስጥ እየተዋጉ ነው። ኃይላት ሁሉ፡ በየቀኑ፡ አንተን፡ ይዋጉሃል።

343 ሰይጣን፡ ያ ታላቅ፣ ትልቅ፣ ንጉሳዊ ካህን ጎልያድ ተመስሎ፡ እየተከታተለህ፡ ጉበትህን በፍርሃት ለሞምላት ይጥራል። ትክክል ነው፡ በእግዚአብሔር ግን...

344 ወገብህን በእውነት ቃል፡ አሜን፡ ዙርያህ በወንጌል፡ ታጥቀሃል። ክብር ይሁን! ሰባኪ ሆይ፡ እንዲሁ ነውና። የመዳን የራስ ቁር፣ የእምነት ጋሻ፣ ሰይፉም በእጅህ እወዛውዘው! “ሰይጣን ሆይ፡ አንተን ለመግጠም ተነስቻለሁ። በሳይንስ ስም ትገጥመኛለህ። በባህል ስም—ትገጥመኛለህ። አንተ በድርጅት ስም ትመጣብኛለህ። **በዚህ፣ በዚያ** ወይም **በሌላ** ስም ትመጣብኛለህ። እኔ ግን በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ። እመጣብሃለሁ። መንገዱን ልቀቅ!” ሞት እንኳን ከፊቴ አይቆምም። መውጫ ቀዳዳውን ቆፍሩ። ትክክል።

345 የሰይጣን ሠራዊት በሽታዎችን ያመጣል፡ የእግዚአብሔር ሠራዊት እነሱን እንዲያወጣ ተልእኮ ተሰጥቶታል። አሜን። ይኸውላችሁ። ሰይጣን በእናንተ ላይ፡ ማንኛውንም ነገር በወረወረ ቁጥር፡ የእግዚአብሔር ሰራዊት ይገሰጸዋል። አሜን። ይገሰጸዋል!

346 እግዚአብሔር የተጠቀመበት ዘዴ ይህ ነው። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል ላለማመን፡ የጥፋት ሠራዊትን ተጠቅሟል፡ ከሚካኤልም የተሻለች መንግሥት አቆመ፡ እግዚአብሔር ግን አባረረው።

347 የእግዚአብሔር ዘዴ፡ ክፋውን መጣል ነው። የአመክንዮ ችሎታን ጣሉት። አጉል እምነቶችን አስወግዱ። ጭንቀትን ያስወግዱ። በሽታዎችን ያስወግዱ። ኃጢአትን አስወግዱ። አሜን። በክርስቶስ ኢየሱስ ከሞት ተነስታችሁ፡ በሰማያዊ ሰፍራ፣ ሰይጣን ሁሉ ከእግራችሁ በታች ሆኖ፣ ከሱ በላይ ናችሁ። እዚያ ውስጥ ጭንቅላቱን ማጣበቅ ከጀመረ፡ ምን...

348 ታውቃላችሁ፡ ሞታችኋል። ህይወታችሁ ተሰውራለች። **ሞት** ምንድነው? ስለ ስሜቶቻችሁ ሞታችኋል። ስለ ህሊናችሁ ሞታችኋል። ሰብዕናህ "አዎን፡ እኔ እንደሚመስለኝ..." ማለት ይጀምራል፡ አንተ ግን ስለ አመክንዮችህ ሙት። ስለ እነዚያ ነገሮች ሙታን ናችሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተቀብራችኋል፡ ከእርሱም ጋር ተነስታችኋል። እሱ ባለበት ቦታ ሁሉ፡ እናንተም ትሆናላችሁ።

349 ከተጠራጣሪዎች አንዱ፡ በገነት በመጣ ጊዜ፡ ምን ሆነ? እግዚአብሔር አባረረው። በክርስቶስ ለተነሱት ሰራዊቶቹስ ምን ብሏቸዋል? "ሰይጣን በመንገዳችሁ ሲመጣ፡ አባርሩት። ገሰጹት።" ኢየሱስ ሠራዊቱን ባሰለጠነ ጊዜ፣ እና እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ባዘዛቸው ጊዜ፣ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡ ያላመነ ይፈረድበታል። አማኝ ሰራዊቴም፡ እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል። በሰሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋዎች ይናገራሉ፡ እባቦችን ይይዛሉ፡ ወይም ገዳይ ነገሮችን ቢጠጡ፡ አይጎዳቸውም፡ እጆቻቸው በበሽተኞች ላይ ቢጭኑ፡ ይፈወሳሉ።"

> ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት!
> ወደ ሰልፍ እየዘመተ፡
> የኢየሱስ መሰቀል
> ከፊት ፊቱ ሄደ።

350 "እኔ ከእርሱ ጋር ተሰቅያለሁ፡ ኑሮዬ፡ በእኔ የሚኖረው እርሱ ነው እንጂ፡ እኔ ሕያው አይደለሁም።" ቃሉ፡ ከፊት እየቀደመ ይሄዳል፡ እግዚአብሄርም፡ ሁለት-አፍ ባለው ሰይፍ ይቆራርጣል።

351 ሰለዚህ፡ ግራንት ሪችሞንድን በያዛት ጊዜ፡ አይደንቅም፡ ያቺ ምስኪን የደቡብ ሴት ግራንት ሲመጣ አይታ፡ የመንፈስ መነቃቃት ወረደባት። እና እንዲህ አለች፦

> ዓይኖቼ የጌታን መምጣት ክብር አይተዋል፡
> ወይኑ በቁጣ የተከማቸበትን የወይኑን እህል እየረገጠ ነው፡
> በአስፈሪው ፈጣን ሰይፉ አደገኛውን መብረቅ ፈታው፡
> ሰራዊቱም እየገሰገሰ ነው።

352 አሜን። ግራንት ሪችመንድን እንዴት ተቆጣጠራት? ልክ እንደተጠጋት። አሜን። ሪችመንድን የተቆጣጠራት በዚህ መንገድ ነው።

353 የእግዚአብሔር ሰራዊትም ኃጢአትን፣ በሽታን፣ የሚቆጣጠሩት፡ በተጠጉ ቁጥር ነው። አሜን። ጥርጣሬያቸውን፡ ፍርሃታቸውን፡ እና ነገሮችን የሚያሸንፉበት መንገድ ይህ ነው። አንዱ ሲነሳ፡ ይቆርጡታል። “መንገድ ልቀቅ!” ኦህ፡ ማይ! አለቀ። እግዚአብሔር በገነት እንዳደረገ፡ ያባርራቸዋል። ታላቅ አዛዥ አለቃችን እንዴት እንደሚደረግ አሳይቶናል። አሜን።

354 ሮይ ሮበርሰን እና ወንድም ፋንክ፣ እዚህ ያላችሁ ብዙ የቀድሞ አርበኞች፣ እውነተኛ አዛዥ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ።

355 አንድ ጊዜ እኔ... ይህ ትንሽ የጄፈርሰንቪል የእሳት አደጋ መከላከያ ክፍል እዚህ አለ። የፋው ቦታ በእሳት ተቃጠለ። እና እዚህ የጄፈርሰንቪል የእሳት አደጋ መከላከያ ክፍል ቆሟል፡ እና አዛዡ እየተዘዋወረ፡ እንዲህ ይላቸዋል፦ “ትንሽ ውሃ **ወደዚህ** አፍስሱ።” “ቲፍ-ቲፍ-ቲፍ-ቲፍ፡” ትንሽ ቱቦ ወደዚህ። ክላርክስቪል መጣ፡ “ትንሽ ውሃ **ወደዚህ** አፍስሱ።” “ቲፍ-ቲፍ-ቲፍ።” የፋው ተቃጥሎ ወደቀ።

356 ወደ ሉዊስቪልን ደወሉ። የሰለጠኑ ሰዎች መጡ። አቤት፡ ሳይረናቸው እንዴት እንደሚጮህ!

357 እና የእሳት አደጋ ክፍል ዋና አዛዦች ቆሟል፣ እንዲህ ይላሉ፡ “ትንሽ ውሃ **ወደዚህ** አፍስሱ። ትንሽ ውሃ **ወደዚህ** አፍስሱ።” ያልሰለጠኑ ሰዎች።

358 ወንድሜ፡ ሞተሩ እንደቆመ፣ መሰላሉ ራስ ላይ ማን ወጣ? አዛዡ። መሰላሉ ወደላይ ሲወጣ፡ እርሱም አብሮ ወጣ። መሰኮቱን መታው፡ ገና መሰኮት አላገኘም ነበርና። መጥረቢያውን ይዞ በመሰኮት በኩል ወረወረው እና እንዲህ አለ፡ “እናንተ ልጆች፡ ኑ።” እና እሳቱ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ጠፋ። አዛዥ!

359 “ትንሽ ውሃ **ወደዚህ** አፍስሱ። ትንሽ ውሃ **ወደዚህ** አፍስሱ።” ያለው አዛዡ አልነበረም።

360 ግን “ኑ፡ ልጆች!” አሜን። መንገዱን መራቸው። እንዴት እንደሚደረግ አሳይቶናል።

361 “እሳቱን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አጠፋ፡ ያ በደንብ የሰለጠነ የእሳት አደጋ መከላከያ ክፍል ነው፡” አልኩኝ። ለምን? የሚሠራውን የሚያውቅ አዛዥ ስለነበራቸው።

362 ወንድሜ፡ ስለምትፈልገው ሰለ ነገረ መለኮትህ ሁሉ ተናገር። ከሰው-ሰራሽ የእምነት ተቋሞቻችሁ፡ ድርጅቶቻችሁ ጋር፡ ተጫወቱ።

እኔ ግን እንዴት ማድረግ እንዳለብኝ የሚያሳየኝ ዋና አዛዥ አለኝ።

“ቆይ እስኪ፡ ከሽተተኝ፡ ከተሰማኝ፡” ትላላችሁ። አቤት፡ ከንቱነት!

363 ዋና አዛዥ ይሆናል ያለው መንገድ **ይህ** ነው፡በሉቃስ ምዕራፍ 4። ለማንበብ ጊዜ የለኝም። እራሳችሁ አንብቡት። ጥሩ። የሉቃስ ወንጌል፡ ምዕራፍ 4፡ ከ1ኛው ቁጥር ይጀምራል።

364 እሱ በጭራሽ እንዲህ አላለም፦ “አሁን እላችኋለሁ እዚህ እና **እዚያ** ሄዳችሁ። ትልቅ ድርጅት መሰርቱ። ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ እና፡ ካርዲናሎች፣ ቢሾፖች፡ ሹሙልኝ፡ **ይሄን**፡ አድርጉልኝ አላለም።” ከቶ አላለም።

365 ሰይጣን ባገኘው ጊዜ፡ “አሁን ተርበሃል። እነዚህን ድንጋዮች ወደ ዳቦ ለውጣቸው፡” አለው፣

እርሱም “ተጽፏል... ” አለው፡

366 “እዚህ ላይ፡ ወደ ላይ እናወጣሃለን አንድ ነገር እናሳይሃለን፡” አለው።

“ግን ተጽፏል... ”

“**ይህን** ካደረግክ፡ እኔ እንዲህ አደርጋለሁ።”

“ተጽፏል... ”

367 ዋና አዛዡ እንደተፈጸመ የተናገረው በዚህ መንገድ ነው። እንዴት ነው፡ እህት? “‘በታመሙ ሰዎች ላይ፡ እጃቸውን ከጫኑ፡ ይድናሉ፡’ ተብሎ ተጽፏል።” “‘በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡’ ተብሎ ተጽፏል።” አሜን። ምንድነው ይሄ? “ተጽፏል!” ይህ የአዛዡ ትዕዛዝ ነው። “‘ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፡ ተብሎ ተጽፏል።’ ተጽፏል! ተጽፏል! ተጽፏል!” ያ ነው።—ትእዛዞቹ ናቸው። ወታደሩ ያ ነው። መንገዱ ይህ ነው። ወደ ላይ ከፍ የምናደርገው መድፍ ይህ ነው።

368 ምን አደረገ? እዚያው፡ ወደ ጎልያድ ወረደ። አሳያቸው... እንዴት እንደሚደረግ ዳዊት እንዴት አሳያቸው? እንዴት እንደሚደረግ ዳዊት ለእስራኤል ያሳያቸው እንዴት ነበር? **ዳዊት** ትርጉሙ “ተወዳጅ፡ አዳኝ፡” ማለት ነው። አያችሁ? ዳዊት እንዴት አደረገ? “የተደረገው መንገድ ይኸውና፡ በጌታ ቃል ታመኑ።” አላቸው።

369 ጎልያድም ወደዚያ መጣና፡ እንዲህ አለው፡ “ታውቃለህ? በዚህ ጦር ጫፍ ላይ ወግቼ አነሳሃለሁ፡ ወፎች እንዲመገቡህ እሰጥሃለሁ።”

370 እርሱም እንዲህ አለው “አንተ በድርጅትህ ስም መጥተህብኛል። እንደ ዘመናዊ ሳይንቲስት መጥተህብኛል። በታላቅ አስራ አራት-ጫማ ሰይፍህ መጥተህብኛል። በናስ ራስ ቁር፣ እና ከመሬት ላይ ማንሳት እንኳ የማልችለውን ጋሻ ይዘህ መጥተሃል። የሰለጠነ ተዋጊ ሆነህ መጣህብኝ። በፒኤች.ዲ፡ እና ኤል.ኤል.ዲ.፡ እና በድርብ-ኤል.ዲ.፡ በእነዚህ ሁሉ ነገሮች ውስጥ መጥተሃል። እኔ ግን በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ፡ ዛሬም ራስህን ከትከሻህ እቆርጣለሁ።” አሜን። ያ ትንሽ ደቃቅ ነገር ያንን ግዙፍ ሊወጋ ወጣ፡ ሰፍራውን በትክክክል ያውቅ ነበርና።

እስራኤል፡ ማዶ ላይ እየተንቀጠቀጠ ነው፡ “ኦህ፡ ምስኪን ብላቴና።”

ጎልያድም አላቸው፡ “ምን እንደምሰራ አሳያችኋለሁ።” እነሆም መጣ።

371 አምስት ጠጠሮች፡ አምስት ድንጋዮች፡ እነሣ። እያችሁ፡ f-a-i-t-h i-n J-e-s-u-s፡ ለመጀመር ያክል፡ አንዲት ድንጋይ አነሣ። ወንጭፉን አሽከረከረ፡ በውስጥ ያለውን ድንጋይን መንፈስ ቅዱስ ራሱ ይዞታል፡ እና ወረወረው። ጎልያድ ወደ መሬት ወረደ። አደራረጉ ይህ ነው።

372 ኢየሱስ የተናገረው፡ በዚህ መንገድ ነው። “አሁን፣ እናንተ ወደ መስክ የምትወጡ ወንድሞች፣ ዲያብሎሶች እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ አደራረጉን አሳያችኋለሁ።”

373 ሰይጣንም፡ ጎልያድም እንዲህ አለ፡ “አገኝሃለሁ።” “ማድረግ የምችለውን አሳይሃለሁ። አንተ ተርበሃል። አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ፡ እገዳደርሃለሁ። አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ትላለህ። እፈታተንሃለሁ። አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እነዚህን ድንጋዮች ወደ ዳቦ ቀይር። ተርበሃልና፡ ብላ። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ፡ ይህን ለማድረግ ስልጣን አለህ።”

374 “ግን ‘ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡ ተብሎ ተጽፏል፡’” አለው። ኦህ፡ ዋናው አዛዥ ያደረገው በዚህ መንገድ ነው።

በቤተ መቅደሱ ጫፍ ላይ ወሰደው። “ራስህን ብትጥል፣” ብሎ በተናገረው ጊዜ፡ “እንዲህም ደግሞ እንደተጻፈ ታውቃለህ፡” ብሎ መለሰለት…

375 እርሱም፡ “አዎን።” አለው፡ “‘እምላክህን እግዚአብሔርን አትፈታተን፡’ ተብሎ ደግሞ ተጽፏል፡” አለው። ራሱን የጠራውን አይታችኋል? “ጌታ አምላክህን።” አህ-ሃህ። “‘ጌታ አምላክህን አትፈታተነው፡’ ደግሞ ተብሎ ተጽፏል።” አያችሁ? ኦህ፡ ማይ!

376 ምን አደረገ? በእግዚአብሔር ቃል፡ አሸነፈው። የዲያብሎስ ዘዴ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳታምኑ ማድረግ ነው። ዋናው አዛዡም እንዲህ አለ፦ “የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብላችሁ ሰሩ። በሰሜ አጋንንትን ታወጣላችሁ።”

377 አቤት፡ ሰይጣን፡ አለቃቸውም፡ አቤት፡ አዎ፡ ታውቁታላችሁ፡ አንዳንድ የሐይማኖት ተቋማት ባለ ሰንጥቅ ሰኮና ነው፣ ባለ ሰንጥቅ ጅራት ነው፡ እና ብዙ ነገሮች በማለት፡ ሊያሳምኗችሁ ይሞክራሉ። እንዳታምኑት። እንደዛ አይደለም። አይደለም፡ ወዳጄ፡ ወንድሜ። እሱ ምሰጥ ነው። እነዚያን ነግሮች አለው ብላችሁ አትመኑ። ሊያሸብሯችሁ ብቻ ነው የሚነግሯችሁ። ዲያብሎስ እንደዛ አይደለም። ሲጀመር፡ ዲያብሎስ ሰኮና የለውም፡ በጣም ውሸት ነው። መንፈስ ብቻ ነው። ዲያብሎስ መንፈስ ነው። እንደሚመስላችሁ፡ ሰንጥቅ ሰኮና እና ወዘተረፈ የለውም። የለውም፡ ኧረ የለውም።

378 ነገር ግን፡ ጥበበኛ ነው። ወንድሜ ሆይ፡ እጅግ ጥበበኛ ሰው ነው፣ እስከ እናቱ ድረስ የተማረ፣ ሁልጊዜም፡ በዓለማዊ ጥበብ የኖረ ነው። ኧረ፡ አዎን። በጣም ቆንጅዬ ነው። ወንድሜ፡ ቃላት—መናገር እስከማትችል ድረስ፡ ሠራዊቱን፡ በዓለማዊ ጥበብ ያደራጃል። “የተአምራት ዘመን አልፏል፡” የሚሉትን ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹን ስታገኛቸው፡ የምታወራውን የምታውቅ ብትሆን ይሻልሃል። በጭራሽ፡ የለውም—ሰንጥቅ ሰኮና የለውም። ቀጥታ፡ ከሰሚናሪ፡ የ—የ—የወጣ ሰው ነው። በጣም አዋቂ ነው፡ ወንድሜ። ማለቴ፡ ብልህ ነው፡ ባለ Ph.D.፡ L.L.D.፡ Q.U.S.T.፡ እና ሌላው ሁሉ ምሩቅ ነው። አያችሁ? ሁሉም በውስጡ፡ በተቻለው አቅም ሁሉ ብልህ ነው። ጥበበኛ ነው፣ አዎን፣ ከሁሉም ይልቅ፡ ሰላቢ እባብ ነው። ወንድሜ፡ ጸጉሩን ለጥ አርጎ አስተኝቶ፡ እና፡ ኮቱ ላይ ነጥብ ሳይኖርበት፡ በደንብ፡ የለበሰ ነው። ብልህ፡ መሆን የቻለውን ያህል ሁሉ ጥበበኛ እና ቆቅ ነው። ትክክል።

379 የምትናገረውን እስካላወቅክ ድረስ ከእርሱ ጋር አትቀላለድ። ትክክል ነው። አቤት፡ እኛ ግን ያረጀ—ያፈጀ ዘዴውን በደንብ አውቀነዋል። ለማድረግ እየሞከረ ያለውን እናውቃለን፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳናምን ለማድረግ ነው።

380 ስንጥቅ ሰኮናም የለውም። ኖ፡ ኖ፡ ኖ። አሁን፡ ስንጥቅ ሰኮና እንደሌለው ካወቅን፡ ሌላ ነገር መሆን እንዳለበት የታወቀ ነው። ሰላቢ ነው። ጥበበኛ፣ የተማረ፣ የተደራጀ ነው። ወንድሜ፡ የራሱ ሰራዊትም አሉት።

381 ተመልከትቱ፣ አንድ ጊዜ፣ በሰዊዘርላንድ። እንዴት ማቆም እንዳለብኝ ጠፋብኝ ወገኖቼ። በ—ሰ... በሰዊዘርላንድ ውስጥ፣ የጀርመን ጦር እየዘመተ መጣ፡... ከውጭ ከሚገቡት ጋር መጣ። የጡብ ግድግዳ ይመስላሉ፡ የሰለጠኑ ብቻ ናቸው፡ አፈ ሙዛቸው፡ ሰምንት ወይም አሥር ጫማ ወደፊት፡ **እንዲህ** ተወድሯል። እና ወደ ምሰኪኗ ትንሿ ሰዊዝ መጡ፡ ምን ይዘው መጡ? ትጥቃቸው ከ—ማጭዶቻቸው የተሰሩ ሰለቶች፡ ዱላዎች እና ድንጋዮች፡ ይዘው ቆመዋል። ቤቶቻቸው ከገደሉ ማዶ ነውና። እና በደንብ የደገፏቸው። የሰዊዘርላንድ ጦር ሊጋፈጧቸው ወጡ። ምንም ሳይበድሏቸው። እንዲሁ ገብተው መሬታቸውን ወሰደውባችኋል።

382 ይህች ህጻን ልጅ፡ እሰኪ እንደው እንደው ሰለ እግዚአብሔር ምን የበደለች ህጻን ናት? ሰይጣን፡ ከቻለ፡ ህይወቷን ይወስዳል። አዎን፡ ይኸው ነው፡ ያለጊዜው። አያችሁ?

383 ሰዊዘርላንድ ምንም አላደረጉም። ጥሩ ሰዎች ነበሩ። ቤቶቻቸውን እየጠበቁ ነበር፡ ለመጠበቅ ግን ጸንተዋል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ አርኖልድ ዎን ዊንኬርድ የተባለ አንድ ሰው ነበር። ሰራዊቱ ደርሶባቸዋል። ሁሉም ተከበው ነበር። "ምን እናድርግ? " አለ፡

384 በየቦታው፡ በደንብ-የሰለጠኑ ወንዶች፡ ባህር ሆኗል። የሰይጣን አሰራር ያ ነውና። በደንብ-የሰለጠነ፣ ጦሩን እያመለከተ፣ እያንዳንዱ ሰው ደረጃ በደረጃ አንድ፡ ሁለት፣ አንድ፡ ሁለት፣ ወደ ትንሹ ሠራዊት መግባት ጀምሯል። ዝም ብለው—መንገዳቸውን ቀጠሉ፡ ማድረግ የነበረባቸው ይህ ብቻ ነበርና፡ ሁሉንም፡ በሰይፍ፡ ቀሏቸው። ጦሩ ሰዎቹን እየበሳ አለፈ። ባይሆን ግን የሰዊሰ ሰራዊት ማለቂያ ይሆን ነበር። ያበቃላቸው ነበር። ልክ ከተራራው በላይ ቤታቸው እና ወዳጅ ዘመዶቻቸው ነበሩ። ሴቶቻቸው በተደፈሩ እና በተጎዱ ነበር፣ እና ወጣት ሴት ልጆቻቸው እና ልጆቻቸው በተገደሉ ነበር። ቤቶች በተቃጠሉ፡ ምግብ፡ ከብት፡ ንብረት ሁሉ፡ በተወሰደ ነበር። ቆመው ነበር።

385 ምን ሆነ? የመንፈሰ መነቃቃት አርኖልድ ዎን ዊንኬርድ የተባለውን አንዱን ሰው አሥነሳው። እንዲህ አለ፦ "የሰዊዘርላንድ ሰዎች ሆይ፡ በዚህ ቀን ለሰዊዘርላንድ እሞትላታለሁ።" አሜን። "በዚህ ቀን ለሰዊዘርላንድ እሞትላታለሁ።"

"ምን ታደርጋለህ፡" አሉት?

386 "ተከተሉኝና፡ ባላችሁ አቅም ሁሉ ተዋጉ፡" አላቸው። እዚያ ቆመና፡ ጦሩን ወርውሮ፣ በእጁ የያዘውን ትንሽ ዱላ፡ **እንዲህ** ይዟል። እና እጆቹን ወደ ላይ **እንዲህ** ዘርግቶ፡ እየጮኸ ወደዚያ ሮጠ፡ "ለነፃነት መንገድ ጥረጉ!" እያለ ጮኸ፡ የቻለውን ያህል ጠንክሮ፡ ወደ ሰራዊቱ ሮጠ። እና፡ እንዲሁ ባደረገ ጊዜ፡ የቻለውን ጦር ሁሉ ቀለበ፡ ወዲያውም **እንዲህ** ወደ ደረቱ ተሰካክተው ሞተ።

387 ከመሄዱ በፊት፡ ነግሯቸዋል። "ማዶ ላይ አንዲት ትንሽ ቤት አለችኝ፡ ሚስት እና ህጻናት ትቻለሁ፡ የገዛኋት ትንሽ ቤትም አለችኝ፡" አላቸው። እንዲህም አለ፡ "እ—እወዳቸዋለሁ፡ ዛሬ፡ ግን፡ ለሰዊዘርላንድ እሞታለሁ። ህይወቱን ሰጠ... "

“ሀገርን ለማዳን ነው ህይወቴን እሰጣለሁ፡” አለ። እና ያ ጀግና ነበር። ከዛ ጀምሮ ጦርነት አላጋጠማቸውም። ያ፡ አበቃለት።

388 እሱ እስኪሞት ድረስ፡ በተጋደለው ተጋድሎ፡ ያንን ሰራዊት አሸንፏል... ያ—ያ ሰራዊት እጅግ ተዳንጦ ነበርና። ሰዊዞች በእነርሱ ላይ ድንጋዮችን እንከባለው፡ ከአገር ውጭ አባረሯቸው፡ እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተመልሰው አያውቁም። ይህ የሆነው ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ነው። አያችሁ? ለምን? ያ ታላቅ ስራ ነው።

389 ግን፣ ኦህ፣ ወንድሜ፣ አንድ ቀን፣ አለማወቅ፣ አጉል እምነት፣ ጥርጣሬ፣ መወዛወዝ እና ፍርሃት፡ የእግዚአብሔር ሕዝብን ወደ ጥጉ በመለሰው ጊዜ፡ ሰሙ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚባል አንድ ነበረ “ዛሬ ለዚህ ህዝብ እሞታለሁ አለ።” ትክክል ነው።

390 ለሠራዊቱ ምን አላቸው? “ተከተሉኝ እና ባገኛችሁት ሁሉ ተዋጉ። ሰንጢ ካገኛችሁ፡ በሰንጢ ተዋጉ። አትፍሩ። ዱላ ካገኛችሁ፡ በዱላ ተዋጉ። ድንጋይ ካገኛችሁ፡ በድንጋይ ተዋጉ፡ ባገኛችሁት ሁሉ ተዋጉ።”

391 የእኛ አዛዥ ዛሬ የሚለውም ይህንኑ ነው። “የእግዚአብሔርን ቃል ይዤ፡ ዲያብሎስን እና ኃይሉን አሸንፌአለሁ።” እሱ በዚያ ቃል፡ እንደ ሪባን ቆራርጦታልና፡ አሜን። አሁን፡ በያዝከው ነገር ሁሉ፡ አንድ ቃል ብቻ ከያዝክም፡ “የሚፈውስህ አምላክህ እግዚአብሔር፡” ይቆርጠዋል። ተከተሉ። አሜን። አዛዡን ተከተሉ። የሰ፡ ሰር። እሱ ራሱ ይቆራርጠዋል።

392 ሰይጣን፡ በትልቁ፡ በሚያማምሩ መንግሥቶቹ፡ እና በበለጠ ውበቱ፡ እና ሁሉም ነገር፡ ከሁሉም-ሰልጣኔዎቹ-ጋር። ከእኛ ጋር ምንም ጉዳይ የለውም። በትክክል። ከሜዳ አራዊት ሁሉ ይልቅ በጣም ተንኮለኛ ነው። የሰ፡ ሰር። ኢየሱስ የዚህ ዓለም ልጆች ከእግዚአብሔር መንግሥት ልጆች ይልቅ ጥበበኞች እንደሆኑ ተናግሯል።

393 አሁን፡ እነዚህ ሁለት ታላላቅ ግጭቶች። አሁን እንዘጋለን... መዝጋት እንዳለብን... ተረድቻለሁ። እነዚህ ሁለት ታላላቅ ግጭቶች አሁን አንድ ላይ እየመጡ ነው። በአሁኑ ጊዜ የሕክምና ሳይንስ እና ሌላው ሁሉ እስኪደናቀፍ ድረስ፡ ዓለም በበሽታ እና፡ በሌሎች ነገሮች የምትጠቃበት ዘመን ነው። ከባድ ነው፡ እኛም—እኛ... ሠራዊቱ፡ ትንሹ የእግዚአብሔር ሰራዊት፡ ወደ መጣበብ ወደ አንድ ጥግ የሚታጨቅበት ጊዜ ነው። ወንድሜ፡ የሌላ ዳግማዊ አርኖልድ ዎን ዊንኬርድ ጊዜ ነው። ሌላ የእግዚአብሔር ሰው የሚቆምበት፡ ጊዜ ነው። ኤልያስ የሚታይበት ጊዜ ነው። የሆነ ነገር የሚሆንበት ጊዜ ነው።

394 የእግዚአብሔር ሠራዊት ሆይ፡ አእምሮህን ድፈነው። ዲያቢሎስ በስሜት ህዋሳት የሚያቀርብልህን ማንኛውንም ነገር ለማሰብ ለአፍታ አትቁም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል፡ ፈጽሞ እንደማይወድቅ አስታውስ።

395 እነዚህ ሁለት ታላላቅ ሠራዊቶች! ጠላት ዛሬ እንደመጣው ዓይነት፡ እንደ ጎርፍ ሲመጣ፡ እግዚአብሔር ምን አደርጋለሁ አለ? “የእግዚአብሔር መንፈስ ልኩን ያበጅለታል።” አንተም ከነርሱ አንዱ ነህን? የሰ፡ ሰር።

396 በያዕቆብ 4:7 ተምረነዋል፣ ለማንበብ ጊዜ የለኝም፣ ያዕቆብ 4:7፡ “ዲያብሎስን ተቃወሙት፡ እና፡” አይሄድም፡ ብቻ አይደለም፡ “ይሸሻል፡” እንጂ።

“ሰይጣንን ተቃወሙት።” ዲያብሎስን እንዴት ትቃወሙታላችሁ? ዋናው አዛዥ እንድናደርገው በነገረን በተመሳሳይ መንገድ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ውሰዱ። እንደዚህ ነው ዲያብሎስን የምትቃወሙት፡ በእግዚአብሔር ቃል ነው። ዋና አዛዥ እንዴት እንደተደረገ ነግሮናል። በጣም ጥሩ።

397 አሁን፡ በመዝጊያ ላይ፡ ይህን ማለት እፈልጋለሁ። አሮጌው ሰይጣን፡ አሁን፡ ደርቋል የምትሉት። ልጅን ያጠቃል ብላችሁ ታስባላችሁ ወይ? አዎን ማንኛውንም ነገር ያጠቃል። ኢየሱስ ክርስቶስን አጥቅቷል። በሦስት ክፉ ጥቃቶች፡ መጣበት። ይህን ታውቃላችሁ? ሰይጣን አንድ ጊዜ ብቻ አላጠቃውም። በበሽታ ያጠቃችኋል፡ ከዛ በኋላም ተመልሶ መጥቶ ያጠቃችኋል፡ እንዲህ ይላችኋል፡ “የተአምራት ቀናት አልፈዋል። አንቺ’ኮ አልተፈወስሽም። ምንም ነገር አላገኘሽም።” እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ?

398 ኢየሱስን ሦስት ጊዜ አጥቅቶታል። በአምላክ ቃል ላይ ባለው አለማመን ጋር፡ ሦስት ክፉ ጥቃቶችን፡ በኢየሱስ ላይ አደረገ። ኢየሱስ ቃል ነበር። በትክክል፡ እሱ ግን አላመነበትም፡ “ከሆንክ... ከሆንክ... ” ዛሬም አንዳንዴ ጠላት እንደሚያደርገው ዓይነት፡ በክፉ ጥቃቶች፡ እንደገና መጣ። ሁሉም መጡበትና፡ “የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፡ ተአምር አሳየኝ። ሲደረግ ልየው፡” አሉት። ወንድሜ፡ ሶስት ክፉ ጥቃቶችን ወረወረ፡ “አንተ ከሆንክ... ከሆንክ... ”

399 አሁን፡ ኢየሱስ ምን አደረገ? ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል ነበር። እሱ ቃል ነበር። ቃልንም አጠቃው። ክብር ይሁን! እውነት—እላችኋለሁ... እየተከፈተልኝ ነው፡ ለመሰበክ፡ ጥሩ ስሜት እየተሰማኝ ነው። እውነት ነው። ኢየሱስ ቃል ነው። “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃልም ማደርያው ውስጥ ገባ፡ ሥጋ ሆነ፡ አደረ... ” ኢየሱስ ያ ቃል ነበረ። ምን አደረገ? እንደ ሪባን ቆረጠው። ኦህ፡ ማይ! አሁን አቆማለሁ። ኢየሱስ ምን አደረገ? እርሱ ቃል ነበር። ስለዚህ፡ በቃሉ፡ በከባድ ጥቃት ሰይጣንን ቆራረጠው። ልክ እንደ ፓራዎች-፡ አውሎ-ነፋሶች፡ ወይም ሌላ እንደዚህ ያለ ነገር ወደሱ በረረ፣ ቃል በሆነው፡ በኢየሱስ ላይ፡ አንዣበበ። ኢየሱስም፡ ያን ቃል አንሥቶ ከታተፈው። ሃሌ ሉያ! አዎን፡ በቃሉ ቆራርጦ፡ አሸንፎታል።

400 ጥቃቱን አይታችኋል? መዝጊያ ነው፡ ተከታተሉ፡ አዳምጡ። ጥቃቱ ምንድነው? ጥቃቱ፡ የእግዚአብሔርን ቃል አትመኑ ነው። በዚህ ውስጥ፡ የውጊያዎች ሁሉ አውራው ውጊያ አያችሁትን? ሁለት ኃይላት ብቻ ናቸው፡ ሰይጣን እና እግዚአብሔር። በእናንተ ላይ የሰይጣን ዘዴ ምንድን ነው? ትጥቃችሁን እንዳታምኑ ለማድረግ መሞከር ነው። ትጥቅ ያስፈታል። አሁን— በትክክል በጽሞና እናዳምጥ። አዳምጡ። ትጥቃችሁ ውጤታማ እንዳልሆነ እናንተን ማሳመን ከቻለም፡ ትጥቃችሁን እንዳታምኑ ከማድረግ ጋር እኩል ነው፡ ትጥቃችሁን አስፈትቷችኋል።

401 ወንድም ኔቪል ሆይ፡ ያንን በፍጹም እንዳናምን፡ ተስፋ አደርጋለሁ።

402 ተመልከቱ፡ ትጥቃችሁ እንዳታምኑ ካስደረጋችሁ አስፈትቷችኋል። ያንን ካራገፋችሁ በኋላ፡ ውጊያችሁ ያበቃለታል፡ አለቀላችሁ። ትይቃችሁን ያዙ፡ አትፍቱ። አለማመንኑን እናያለን። በቃ...

አሁን በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ መናገር የምፈልገው አንድ ተጨማሪ ነገር።

403 ሩስያ። ይህን ማለት የምፈልገው ለነባር አርበኞች፡ እና ሌሎች፡ እዚህ ለተገኛችሁ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችም ጥቅም ነው። ስለ ሩስያ የሚያጨንቃችሁ እና የሚያነታርካችሁ ምንድነው? ሆ! የቦምብ መከላከያ ምሽግ ስሩ ሰላችሁ አልሰማችሁኝም፡ አይደለም እንዴ? ስለ ሩስያ ለምን ትጨነቃላችሁ? ሩሲያ ምንም አይደለችም። አንድም ጦርነት አያሸንፉም። አለምን አያንበረክክም። ኮሚኒዝም ዓለምን አያንበረክክም። ሰዎች ችግራቸው ምንድነው? የእግዚአብሔር ቃል ሊወድቅ ይችላልን?

404 ሰሙኝ፡ ይህ አሁን ቴፕ ላይ ነው፡ ለአለም እናገራለሁ፡ ወይም፡ እነዚህ ካሴቶች ለሚሄዱበት ሁሉ እላለሁ። እዚህ ላላችሁ ሰዎችም፡ በእኔ ላይ ምንም አይነት ነገር ቢደርስብኝም፡ ይህን እመኑት።

405 ሩሲያ፡ ኮሙኒዝም፡ ምንም ነገር አያንበረክክም። የእግዚአብሔር ቃል አይወድቅም። ዓለምን የሚያንበረክክ ሮማኒዝም ነው።

406 የዳንኤልን ራዕይ እንውሰድ። ያ የእግዚአብሔር ቃል ነው። “አንተ፡ ዳንኤል ሆይ... ” “ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ፡ ይህ የወርቅ ራስ፡ አንተ ነህ።” ባቢሎን። “ሌላ መንግሥት ይተካሃል፡ እርሱም ብር ነው።” እያችሁ፡ ይህም ሜዶ-ና-ፋርስ ነበር። ሌላው ግሪክ ነበር፡ ታላቁ አሌክሳንደር። በመቀጠል ሮም ገባ። እና ስለ ኮሙኒዝም ምንም የተባለ ነገር የለም። ሮም ዓለምን ታንበረክካለች።

407 ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በሮም ዘመነ መንግሥት ነው፡ ሰደት ደርሶበታል፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣው፡ በሮም ዘመነ መንግሥት ነው። በሁለተኛው ምጽአቱም፡ አሁን ይመጣልና፡ መልእክቱ በሮማውያን የሐይማኖት ተቋማት፡ የሁሉም እናት በሆነችው ይሰደዳል። ሲመለሰም፡ የሮምን መንግሥት ለማጥፋት ተመልሶ ይመጣል፡ የአይሁዶች መሻትም መጥቶ የሮምን መንግሥት ያጠፋላቸው ዘንድ ነውና።

408 በዓለም ላይ ካሉ ከሌሎች ሐይማኖት ተቋማት ጋር የካቶሊክ የሰልጣን ተዋረድ፣ አሁን እንደ ድርጅት አንድ ላይ እየተሰበሰበ ይገኛል፡ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በአንድነት ተደራጅተዋል። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።** ሩሲያ አይደለም። ሮም ነው። አዎን። ኮሚኒዝም ይሁን ሌላ፡ ከሮም ውጪ ገዢ የሚሆን ሌላ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አሳዩኝ።

409 ሜዶን-ና-ፋርሰ ናቡከደነፆርን ተክቶ ነበር? በእርግጠኝነት። ግሪክ እነሱን ተክታለች? አዎ። ከዚያስ፡ ሮም አልተቀበለቻቸውምን? አሁን እንዳየነው በአሰር የኦቶማን ኃይሎች ተከፋፍሎ የለምን?

410 **አይዘንሃወር**፡ ትርጓሜውም፡ “ብረት፡” እና **ክሩሽቼቭ** ትርጓሜውም፡ “ሸክላ፡” ሁለቱ እዚህጋ ሰብሰባ አላካሄዱምን? ከዛ በኋላ ክሩሼቭ ጫማውን አወለቀ፡ [ወንድም ብራንሃም ቹልፒቱ ላይ አንኳኳ—አርታዒ።] ህዝቡን በግልጽ ለማሳየት፡ ለማብራራት፡ ነገሩን ለማስረዳት፡ **እንዲህ** አርጎ፡ ጠረጴዛውን ደበደበው። [ወንድም ብራንሃም ቹልፒቱ ላይ ደበደበ።]

411 እንዴ፡ ዛሬ ሰው ምን ነካው? እምነት ወዴት ገባ? የእግዚአብሔርን ቃል እውነት እንደ ሆነ፡ ለምን አታምኑም? **ነገርየው** የለም’ኮ። የዛሬ ሰባኪዎች ምን ነካቸው? “ኮሙኒዝም!” ሰባኪ ሁሉ ኮሙኒዝምን ይታገላል። ኮሙኒዝም፡ ተራ ነገር ነው።

412 ዲያብሎስ፡ ነገሩን አፍንጫችሁ ስር እያወዛወዘው ይገኛል፡ እናንተ ግን ሮማኒዝም፡ ሐያማኖታዊ ተቋማዊነት፡ እንደሆነ አታውቁትም። ሮም የሐይማኖት ተቋማት ሁሉ እናት ናት። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በእግዚአብሔር ላይ፡ እና በቃሉ ላይ ያመጸች "ጋለሞታ ናት፡ ልጆችዋም አመንዝራዎች ናቸው፡" ይላቸዋል።

413 ሰራዊት ሆይ፡ ቃሉን አንሡ። የምሕረት መላእክት ሆይ፡ ቃሉን ጸንታችሁ ያዙ። እኔ አንድ ቀን እጠፋለሁ፡ ይህ ቃል ግን አይጠፋም። እናንተም ወጣቶች ሆይ፡ በዘመኔ ካልሆነ፡ እናንተ ታዩታላችሁ። ነገሩ ይሆናል።

414 የዛሬ ጠዋት ዜና ሰምታችኋል? ወይዘሮ ኬኔዲ፡ ጳጳሱን ለማየት ሄዳለች፡ ጳጳሱ ምን ተናገረ? እያችሁ፡ የዓለም ሐይማኖቶች በሙሉ! ኦህ! ምናልባት፡ በሚቀጥለው እሁድ በበለጠ እናየዋለን።

415 እያችሁ፡ ስለ ሩሲያ አትጨነቁ። ሩሲያ በባሕር ዳር እንዳለች አነስተኛ ደሴት ናት። ስለ ኮሙኒዝም አትጨነቁ። ሮማኒዝም ከአብያተ ክርስትያናት ጋር አንድነት ሲፈጥር ግን ተጠንቀቁ። ኮሙኒዝም ዓለምን ይመራል የሚል ጽሑፍ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ የለም።

416 ማንም ምንም ይሁን፡ እኔ ግን የምከተለው ቃሉን ነው። ቃልን አምናለሁ። ዓለምን የሚገዛው ሮማኒዝም ነው። ሮማኒዝም የድርጅቶች ሁሉ እናት ናት። እስከ ሮም ድረስ ድርጅቶች በጭራሽ አልነበሩም፡ ሁሉም ከመካከልዋ የወጡ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስም "የአመንዝራዎች እናት፡" ይላታል። በዚህ ርዕስ ላይ ግማሽ ቀን መሄድ ይቻላል፡ ቢሆንም ግን፡ መቀጠል ያለብኝ ይመስለኛል።

417 ጠላት ባጠቃን ጊዜ፡ ያኔ፡ "ኦህ፡ እልሃለሁ፡ ና ማሕበራችን ብትቀላቀል ይሻልሃል... " ሲሉ ምን ታደርጋለህ፡ ታፈገፍጋለህን፡ ታመቻምቻለህን? ጎበዝ ወታደር፡ አያመቻምችም። ኖ፡ ሰር።

418 ታድያ ያኔ ምን እናደርጋለን? አሳባችን፡ "በክርስቶስ የነበረውን አሳብ... " ይላል መጽሐፍ ቅዱስ አይደል? "በክርስቶስ የነበረውን አሳብ፡ በእናንተ ዘንድ ይሁን።" ምን አይነት አሳብ ነበረው? ከቃሉ ጋር የጸና። ትክክል። ከቃሉ ጋር፡ ከአብ ቃል ጋር የጸና፡ ጠላትን ዘወትር ያሸንፋል። ለምሳሌ ጠላት ሲያጠቃ **እንዲህ** እና **እንዲህ** አድርጉ ሲላችሁ፡ ምን ታደርጋላችሁ? ከቃሉ ጋር ትጸናላችሁ። ትክክል።

419 ያኔ ምን ታደርጋላችሁ? ቃሉን ትይዛላችሁን። ቃሉ ምንድነው? እዚህጋ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። አንብበነዋል። የእግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ቃል ነውና። እያችሁ? ወደዚህ ተመልከቱ። "የመዳን ራስ ቁር፡ እና ሰይፍ፡ የመንፈስ ሰይፍ ያዙ።" የመንፈስ ሰይፍ! ምንድነው? መጥቶ እእምሮአችሁ አልፎ ወደ እናንተ የሚዘልቀው መንፈስ ነው፡ የመንፈስ ሰይፍ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

420 መንፈስ የሚታገለው ምንድነው? መንፈስ የሚታገለው ከምን ጋር ነው? ከስሜቶች? ከስሜታዊነቶች? ከቃል ጋር፡ ከልብ! ኧረ! ክብር! ከማን ጋር ይታገላል? ከስሜቶች ነው? ከቃል ጋር! ቃል! እስኪ እንበለው፡ ቃል! ቃል! መንፈስ የሚታገለው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ነው።

421 የእግዚአብሔርም መንፈስ ወደ ዲያብሎስ ፊት ለፊት ወጥቶ "ተጽፏል!" ይለዋል፡ አሜን! "ተጽፏል!" ዲያብሎስም መንገድ ይለቃል።

422 ምን እናድርግ? ሰይፉን እንያዝ፡ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ በ (ምን? ) በእምነት እጅ፣ በጠንካራ የእምነት እጅ፡ ሁለት-አፍ ያለው ሰይፍ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 4 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ “ወደፊትም ወደኋላም የሚቆርጥ “ሁለት-አፍ ያለው ሰይፍ—ነው።”

423 ወንድሜ፡ እርሱ ምን ያደርጋል? ቃሉን ያዙ። መንፈስን ይኑራችሁ፡ መንፈሱ ወደ ልባችሁ ይግባ። አእምሯችሁን ከፍታችሁ፡ “ቃልህ እውነት ነው፡” በሉ። አሁን፡ አንቺም እህት ሆይ፡ “ቃልህ እውነት ነው፡” በይው።

424 “ጌታ ሆይ፡ ለስሜቴ፡ ወይም ሰው ለሚናገረው፡ ምንም ትኩረት አልሰጥም። እያቆምኩት ነው፡ ከጎዳናዎቼን ሌላውን በሙሉ እየጠራረግኩ ነው፡ ውዝግቦቼ ሁሉ፡ ጥርጣሬዎቼ በሙሉ፡ የነበሩኝ አለማመኖች ሁሉ። የገጠሙኝ ስሜቶች ሁሉ፡ የነበሩብኝ በሽታዎች፡ የነበረብኝ ሌላ ነገር በሙሉ፡ ሁሉንም እየጠራረግኳቸው ነው። ያን ሁሉ አልፌያለሁ። በቀጥታ ወደ መንፈሴ እየመጣሁ ነው። ጌታ ሆይ፡ ውረድልኝ። ነጻ የሞራል ምርጫ ሰጥተኸኛልና።”

“አንተ፡ ልጄ ነህ።”

425 “እሺ፡ ልቤን እና አእምሮዬን እከፍታለሁ። ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ግባ።”

426 **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ የመንፈሱን ሰይፍ፡ እምነቱን ያዙት። ጩኹ፡ “ሃሌሉያ!” አሜን። ከዚያም ከፊትህ ያለውን ጠላት ሁሉ ቆርጠህ አውጣ። አሜን። እያንዳንዱን ጠላት፡ ቁረጡት። የቆየ—አስፈሪ መንፈስ እነዚህ እንዲሰማችሁ የሚያደርጋችሁ ከሆነ… በጌታ ቃል፡ ያንን አስወግዱት።

ኃይላችን ግን፡ ደስታው ነው፡ “የጌታ ደስታ ኃይሌ ነው።”

427 “ዞር በል ከፊቴ።” ውጉት! በቃሉ ቁረጡት። ጋኔን ቢሆን፣ ጠላት ቢሆን፣ በሽታ ቢሆን፣ ህመም ቢሆን፣ ምንም ቢሆን፣ ቃሉን ይዛችሁ ከሰይፍ ጋር ሳቡት። እንዴ ወግታችሁት፡ አልነሳም ካለ፡ ደግማችሁ ውጉት፡ አሁንም ውጉት፡ ደጋግማችሁ ውጉት። የደሮ ወይም የንስር ጫጩት ቀዳዳ እስኪያወጣ ድረስ እንደሚቆረቁር፡ እናንተም፡ ቀዳዳ እክታወጡ ድረስ፡ ቆርቁሩ። ካረጀው ከበሽታ ቅርፊት ሰርሰራችሁ ውጡ። መውጫችሁን አዘጋጁ፡ እና “ሃሌ ሉያ! ቀጣዩ የት አለ? ” በሉ፡ አሜን። ጦርነቱ ይህ ነው። ወታደር ማለት ይህ ነው። የመስቀል ወታደር ማለት ይህ ነው። የሰ፡ ሰር። እያንዳንዱን ጠላት ዘርሩት።

428 ለምን? ለምን? አስቀድመው የተወሰኑ፡ የአብርሃም፡ ንጉሣዊ ዘር ነንና። አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል የሚጻረርውን ሁሉ በካደ ጊዜ፡ ከፊት ለፊቱ የሚመጣው እንቅፋት ሁሉ ቆራርጦ መንገዱን አበጀ። “ሚስትህ በጣም አርጅታለች፡” አሉት። ነገሩን ከመንገድ ቆርጦ ጣለ። ዲያብሎስም፡ “**ይህን** ማድረግ አትችልም። **ያንን** ማድረግ አትችልም።” አብርሃም ግን ከመንገድ አስወገደው። ቆርጦ እስኪያልፍ ድረስ፡ ደጋግሞ ወጋው፡ ወጋው።

“ቀጥሎ፡ ወዴት ነው ጌታ ሆይ? ”

429 “ድንኳንህን **ወደዚያ** አንቀሳቅሰው።” ወደዚያ ወጥቶ በዚያም መሰውያን ሠራለት።

430 ሰይጣን ተነሣና፡ መጥቶ እንዲህ አለው፡ “አሁን፡ ልንገርህ አይደል፡ ይህ ትክክለኛ ቦታው አይደለም።”

“እኔ’ማ እዚህ እጠብቀዋለሁ። አንተ ግን ሂድ ራቅ ከሰፍራዬ፡” ሃሌሉያ! አለ።

431 ሎጥም እንዲህ አለው፡ “ብትወርድ ይሻልሃል። እዚህ ጥሩ ጊዜ እያሳለፍን ነው። ሁላችንም የየራሳችን ድርጅት ከፍተናል። እንዴ፡ ባለቤቴ በከተማ ውስጥ የሰነ ጽሑፍ ማህበረሰብ፡ እና የሁሉም ነገር ኃላፊ ነች። ወደዚህ እንድትወርድ፡ እመክርሃለሁ።”

ሳራም “አብርሃም... ” አለችው፡

432 “ዝም በይ ሳራ።” ሃሌ ሉያ! “ጸንተሽ ቁሚ። እግዚአብሔር ያሰቀመጠኝ እዚህ ነው። እኔ የምጸናው እዚሁ ነው።”

433 እግዚአብሔር ያሰቀመጠኝ እዚህ ነው፡

ሁሉም የኢየሱስን ሰም ኃይል ያወድሳሉ!
መላእክትም ይሰግዳሉ፡
የንጉሥ ዘውድ አምጡ፡
የሁሉም ጌታ አንግሱ።

በጠንካራው ዓለት፡ በክርሰቶሰ ላይ፡ ቆሜአለሁ፡
ሌሎች የሚሰምጡ አሸዋዎች ናቸው፡
ሌሎች የሚሰምጡ አሸዋዎች ናቸው።

434 ሞትም፡ ሌላውም ሁሉ፡ የሚያሰምጥ አሸዋ ነው። በጠንካራው ዓለት፡ በክርሰቶሰ ላይ፡ ቆሜአለሁ።

435 “የአብርሃም ንጉሣዊ ዘር።” የንጉሥ ዘር! ለምን፡ የእንግሊዝ በጣም የተመረጠው ሰራዊት የእንግሊዝ ንጉሣውያን፡ ንጉሣዊ ደም፡ ወዘተ ነው። የክርሰቶሰ ንጉሣውያን ዘር ደግሞ በመንፈሰ ቅዱሰ-የተሞላች ቤተ ክርሰትያን ናት፡ በመንፈሰ ቅዱሰ የተሞላች። ምን? የንጉሣውያን ዘር፡ በተሰፋ ቃል እንጂ፡ በሰሜት አይደለም። ነገር ግን፡ በእግዚአብሔር በተሰፋው ቃል፡ በእግዚአብሔር ቃል ጸንተው፡ መውጫ መንገዳቸውን፡ “ሃሌ ሉያ!” እያሉ ይከፍታሉ፡

ሞት መጥቶ “ቀርቧል ደጅህ ላይ ደርሷል፡” ቢላቸው።

436 “ዞር በል፡ ዮርዳኖሰ። እሻገራለሁ፡” ይሉታል። ወደ ተሰፋይቱ ምድር መሄጃ መንገድህ፡ ቆርጠህ ክፈት። አሜን።

437 ጦርነቱ ሲያልቅ ምን ይሆናል? አሁን እዘጋለሁ፡ በእርግጠኛነት። ጦርነቱ ካለቀ በኋላ፡ ቅዱሳኑም ወደ ቤት ሲመጡ፡ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ፡ ምን ይሆናል?

438 ሂትለር ፈረንሳይ ሲገባ ምን ሆነ? ለምን፡ አውሮፕላኖቹ፡ ለተወሰነ ጊዜ፡ ሰማዩን እንኳን ማየት አይቻልም ነበር አሉ። የጀርመን ጉዝ-ሰቴፕ። [ወንድም ብራንሃም የጉዝ-ሰቴፕ ድምጽ አሰመሰለ—እርታዒ።] እያችሁ፡ ድልን እያከበሩ፡ ቆመው እያለፉ ነበር።

439 ሰታሊን ወደ ሩሲያ ሲመጣ፡ ረጅም ኪሎ ሜትሮች ወደኋላ፣ አንዱ ሌላውን ታንክ እየተከታተለ፡ ምንም ነገር እሰከማይቀር ድረሰ በርሊንን ደበደቧት። አለቀ። እና እነዚህ ጀርመኖች፡ ሲሄዱ... እንደምታውቁት፡ እነሱ በሚያደርጉት፡ አሰቂኝ ነገር፡ ሩሰያውያን ጨዋታቸው ጀመሩ። አንድ ጊዜ ለንደን ውሰጥ፡ እንዴት

እንደገቡ፡ በሥዕል አይቻለሁ፡ የነገሩን ትክክለኛ ምስል፡ ምን እንደተፈጠረ፡ ሲገቡ፡ እየተጫወቱ ነው። ኦህ፡ ማይ!

440 ጦርነቱ ማለቁን ሰንሰማ፡ ጬህን፡ ፊሽካ ነፋን። ጀግኖቹ ሲመለሱ እዚያው አገኛናቸው። ጬኹ። እልል አሉ። አንድ የእኅት ልጅ በዚያ ውስጥ ነበረኝ፡ ተመልሶ ሲመጣ፡ እንዲህ አለ፡ ሽማግሌዎቹ ሁሉ... እጅግ ሰግተው የነበሩ አርበኞች፡ ከአልጋዎቻቸው መነሣት አይችሉምና፡ ስለዚህ በገቡ ጊዜ፡ የነጻነት ኃውልቱን ያዩ ዘንድ፡ መርከቡ ጣራ ላይ አወጧቸው፣ "በዚያ ቆመው የነበሩ ሽማግሌዎች ሁሉ፡ **ያንን** የነጻነት ሃውልት ሲያዩ፡ አለቀሱ፡ ሁሉም እንዲህ ይወድቁ ነበር።" ሲዋጉ፡ ለአራት ዓመታት ከቤት ርቀዋል በጦርነት-ደንግጠው፡ እና ሁሉም ነገር ሆነዋል። ነገር ግን ሚስት፡ እና ፍቅረኛ፡ እና እናት፡ እና አባት፡ እና ልጆች፡ እና የሚወዷቸውን ሁሉ፡ ከነጻነት ሃውልት ጀርባ እንደነበሩ አውቀው ነበርና። ሲታገሉለት የነበረውን ነገር ይወክላልና። ኦህ፡ ፊሽካዎቹ ተነፉ፡ ኒው ዮርክ በጩኸት ተናወጠች፡ ጀግኖቻቸው እየገቡ፡ ነበርና። ያ ግን ተራ ነገር ነው።

441 አንድ ጊዜ ቄሳር፡ ከታላቅ ጦርነት በኋላ፡ "በዚህ ታላቅ የጠላታችን ሽንፈት የድል በዓል በጣም ታዋቂው ተዋጊዬ ከጎኔ እንዲጋልብ እፈልጋለሁ፡" አላቸው። መኮንኖቹም እያንዳንዳቸው ቱንቢያቸውን አስተካክለው ጋሻቸውን ወለወሉ። እና እንደምታውቁት፡ እንዲህ እያሉ፡ እንደ—እንደ ትክክለኛ ወታደር፡ አብረው ተሰለፉ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ፡ አንድ ምስኪን ሽማግሌ፡ ቆሰሎ፡ መጣ። አቤት! ዝም ብሎ ቀና ብሎ እያየ፡ **እንዲህ** አብሮ መጓዝ ጀመረ። ቄሳርም "አንዴ ቆይ፡ ቆይ አንዴ ጠብቁኝ፡ አንተኛው፡" እንደ—አንድ መኮንን እንኳን አልለበሰክም፡ "ና እስኪ።" "እነዚህ ጠባሳዎችን ከየት አገኙህ? " አለው፡

"በጦር ሜዳ ነው፡" አለው።

442 "ወደዚህ ውጣ። አጠገቤ እንዲቆም የምፈልገው ሰው አንተን ነው፡" አለው። ለምን? ጦርነት ላይ እንደነበረ ስለአረጋገጠ።

443 አቤቱ እጁን በሰርዲን ጣሳ ቆርጦ ጥቅስ የሚፈልግ ሰውን ማረው። የጦር-ጠባሳ ያለው መሆን እፈልጋለሁ። ጳውሎስ እንደተናገረው "የኢየሱስ ክርስቶስን ምልክቶች በሰውነቴ ተሸክሜአለሁ፡" አለ። ለዚህም ነው በመሰክ ላይ መዋጋት የምፈልገው።

444 አንድ ቀን፣ ያስታጠቀን፣ የእግዚአብሔር ትጥቅ የሰጠን፡ በዚያም ጸንተን፡ የምንዋጋበትን ቃል የሰጠን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ታላቁ አለቃችን ሲመጣ፡ ታላቁ አለቃ መኮንን ተቀምጦ እየጋለበ ሲመጣ፡ ሠረገላው ላይ ወጥቼ ከእርሱ ጋር ወደ ቤት መሄድ እፈልጋለሁ፡ እናንተስ? ከዚያም ባለቤቴን ክንዴ ላይ ይዤ፣ ዞር ዞር ብዬ ተመልክቼ፡ ወንድሞቼንና ሚስቶቻቸውን፡ እና ልጆቻቸው ይዘው፡ በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ መሄድ ስንጀምር፡ ከላይ እንደዚህ፡ መላእክቶች እየሩን በመዝሙሮች ይሞሉታል፡ ስለ ክብረ በዓል ይወራል!

445 ጦርነቱ ሲያልቅም አክሊልን እንለብሳለን። ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ እናንተ የመስቀል ሰራዊት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ የእምነትን ክንድ ምዘዙ፡ እና መሳርያውን ያዙ።

446 አንቺስ እህቴ፡ ምን ትያለሽ፡ ተዘጋጅተሻል? መሳርያሽን መዘሽ፡ እንዲህ በይ፡ "እምላክ ሆይ፡ ዲያብሎስ ምንም ይበለኝ—አይገደኝም፡ ሌላ ሰውም ምንም ያህል ቢናገር፡ ዛሬ ጠዋት ግን፡ እምኛለሁ፡ እምኛለሁ።"

447 ባለፈው ቀን እንዳልኩት፡ ትንሽ… ከጥቂት እሑዶች በፊት ይመስለኛል፡ አንድ ሰው ሕልም አየ። ዲያብሎስ ደቃቅ ሽማግሌ ነገር ሆኖ፡ ወደሱ ዘንድ ሲቸኩል አየ። እና “ቡ!” አለውና፡ ወደ ኋላው ዘለለ፡ እና ዲያብሎስ ተለቅ አለ። አሁንም “ቡ!” አለው ወደኋላው ዘለለ፡ አሁንም ዲያብሎሱ ተለቀ። በመጨረሻም፡ ዲያብሎስ፡ እሱን ማሸነፍ በሚችልበት ደረጃ አደገ። የሆነ ነገር ይዞ እሱን መፋለም እንዳለበት ገብቶታል፡ እና ዙርያውን አየ። እሱን የሚፋለምበት ምንም ነገር አላገኘም። እና መጽሐፍ ቅዱስን አነሳ። አሁንም ዲያብሎስ “ቡ!” አለው፡ እሱም፡ “ቡ!” ብሎ መለሰለት፡ ከዛ በኋላ ዲያብሎስ አነሠ፡ አነሠ፡ አነሠ። በመጨረሻም፡ በቃሉ ደብድቦ፡ ገደለው።

448 ወታደር ነሽ፡ አይደል΄ዴ እህት? ያን ቃል ያዢና፡ “ተጽፏል” በይው። አሜን። “በህይወት እኖራለሁ እንጂ፡ አልሞትም። በዚህ ተበርናክል ሆኜ፡ ከሌሎቹ ጋራ፡ እግዚአብሔርን ስለ ቸርነቱ አመሰግነዋለሁ በይው።”

449 ይህን ታምናላችሁ፡ ቅዱሳን? አሜን።

አራሶቻችን ዝቅ እናድርግ።

450 አቤቱ አምላክ ሆይ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ሆይ፡ አሁንም አምላክ እንደሆንክ ዛሬ ይታወቅ። ምንም ያህል ብሰብክ፣ ሰንት ነገር ብናገር፡ ጌታ ሆይ፣ ከአንተ የሆነ ቃል ያስተካክለዋል።

451 የታመሙ ሰዎችን የሚወክሉ እነዚህ መሀረቦች እዚህ ተቀምጠዋል። እጄን በእነሱ ላይ ሰጭን፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ በረከቶችህ እና ኃይልህ በእያንዳንዳቸው ላይ እንዲያርፍ፡ እጸልያለሁ። እግዚአብሔር ሆይ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ እነዚህን መኃረቦች በቅዱስ ፊትህ እንድትቀባቸው እጸልያለሁ፣ በቃሉ ተጽፏልና። ከቃሉ ጋር የሚጻረር ነገር አይደለም። በቃሉ ግን፡ እንዲህ ተጽፏልና፡ “ከጳውሎስ አካል፣ መሃረብና ልብስ ይወስዱ ነበር። ርኩሳን መናፍስትም ከሕዝቡ ይወጡ ነበር፡ ከተለያዩ ደዌም ተፈወሱ።” አሁን፡ እኛ ቅዱስ ጳውሎስ አይደለንም፡ አንተ ግን አሁንም ያው አምላክ ነህ፡ አንተ አሁንም ያው መንፈስ ቅዱስ ነህ። በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እጆቼን በእነዚህ መሃረብ ላይ እዘረጋለሁ፡ እና እያንዳንዳቸውን እንድትባርክ እና እንድትፈውሳቸው እጠይቃለሁ።

452 እንዲሁም፡ አምላክ ሆይ፡ እዚህ አልጋ ላይ የተኛች፡ ተኝታ የቆየች ልጅ፡ አንድ ፍሬ ልጅ ናት፡ ገና ቆንጆ ትንሽ ሴት ልጅ ናት። ጌታ ሆይ፡ መኖር አልቻለችም። ሰይጣን ክፉኛ ጎድቷታል። የዚህ ምድር ተወዳጅ ሐኪሞች ልጅቷን ለማዳን፡ ያለ ጥርጥር ብዙ ጥረት አድርገዋል፡ ሊያድኗት ግን አልቻሉም። በጥበባቸው መጨረሻ ላይ ናቸው። ሌላ ምንም ማድረግ አያውቁም። ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ ሌላ የተጻፈ ምዕራፍ በመኖሩ በጣም ደስተኛ ነኝ። ሌላ ገጽ መክፈት እንችላለንና፡ በዚህ ገጽ ላይ ታላቁ ሐኪም መጥቶ ሲገባ ይታያልና። ዛሬ ጠዋት ለምክር እሱን እንጠራለን።

453 እንግዲህ፡ ጌታ ሆይ፡ “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡” ተብሎ፡ በቃልህ የተጻፈ አይደለምን? ጌታ ሆይ፣ አማኝ ካልሆንኩኝ፣ አሁን አማኝ አድርገኝ። ይህች ትንሽ ልጅ አማኝ ካልሆነች፡ አሁን አማኝ ትሁን። “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡ እጃቸውን በድውዮች ላይ

ቢጭኑ፡ ይድናሉ።” “በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ።” ተብሎ ተጽፏልና። ጌታ ሆይ፡ የአንተው—ቃላቶች ናቸው። የአንተ ነው። ቃልህ ነው። አሁንም እንደ ባርያህ...

454 እንዳልከውም፡ “ሁለት ወይም ሦስት ብትሆኑ፡ በመካከላችሁ እገኛለሁ፡ እና አንድ ነገርን በተመለከተ ተስማምታችሁ፡ ከጠየቃችሁ፡ ትቀበላላችሁ።”

455 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህች ሕፃን ምናልባት ዛሬ ጠዋት በህንፃው ውስጥ ካሉ ሁሉ ይልቅ በጣም የታመመች ሰው ናት፡ በጣም ስለታመመች፡ ከአንተ ውጪ፡ ብዙ ዕድሜ አይኖራትም። ስለዚህ፡ እያንዳንዱ ሰራዊት እዚህ እንደቆመ፡ በአንድነት ተሰማምተናል። በዚህ ጎራ መካከልም የአብራሃም ዘር ቆሟል።

456 አሁን ወደ ሰይጣን እየዘመትን ነን። አሁንም አንተ ሰይጣን፡ ትጥቃችን ስለሚያብረቀርቅ፡ ሰንደቃችን ስለሚውለበለብ፡ ለመሄድ ተዘጋጅ፡ ሰይፍ የያዙ ወንዶች እና ሴቶች፡ ሰለ ልጅቷ፡ ወደ አንተ ወደ ፊት እየገሰገሱ ናቸው። አንተ ሰይጣን ከህይወቷ ውጣ፡ ልጅቷን ለቀህ ሂድ። እንደ ሕያው የእግዚአብሔር ሠራዊት፡ እንቃወማሃለን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ልቀቃት።

457 እጄን በላይዋ እጭናለሁ። ሰይጣን ሕፃኗን አሰረህ፡ ይህን ክፉ ነገር አድርገሃል። ለሰው ልጅ ከልኩ በላይ እንደሆንክ አውቃለሁ፡ ለጌታዬ ግን፡ አትተካከለውም፡ ሰለዚህ በሰሙ መጥቼብሃለሁ። አንተ የዲያብሎስ መንፈስ፡ ልቀቃት። የበሽታ ጋኔን፡ ከዚህች ሕፃን ውጣ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ነፃ ትውጣ። ይህንን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ አውጃለሁ።

458 አሁንም፡ ሙታንን ያስነሣህ አምላክ እንደ ሆንህ ያረጋገጥክ፡ ጌታ አምላክ ሆይ፡ ይህችን ወጣት ሴት ወደ ጤናዋ እና ጥንካሬዋ እንደገና መልሳት፣ በህንጻው ውስጥም ትቁም። ሰይጣን ለቋት ሄዷል!... ? ... በደንብ ጤነኛ ትሆናለች። ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ትኑር።

የተነገረላት፡ አሁንም—ይሁንላት።

459 እጆቻችሁን ወደ ላይ አንስታችሁ፡ “እንዲጸለይልኝ እፈልጋለሁ። ታምሜአለሁ። እግዚአብሄር ያስፈልገኛል” ማለት የምትፈልጉ ሌሎች እዚህ አላችሁ? ምን ያህል ጊዜ እንዳለን አላውቅም። ሰዎች እዚህ እንዲያልፉ ለማድረግ በቂ ጊዜ አለን። ዛሬ ጠዋት እውነተኛ መጽናኛ ይሰማኛል። አዎን። አዎን። ቢሊ፡ እዚህ እንድትወርድ እፈልጋለሁ፡ ምናልባት ይህን አንድ ክፍል፡ **በዚህ** በኩል እዚህ፡ ብቻ ያዝልኝ። መጀመሪያ ይህ ክፍል ይምጣ፡ ከዚያ በኋላ **እስከዚያው** መተላለፊያ ድረስ፡ የኋለኛውን ክፍል እንወስዳለን። እና እንዲሁ እናስተናግዳቸዋለንና፡ ምንም አይሆኑም...

460 ወንድም ኔቪል እና አንዳንድ አገልጋይ ወንድሞቼ እዚህ ከጎኔ እንዲቆሙ እፈልጋለሁ፡ እዚህ፡ እናንተም እንደገና በመተላለፍያው በኩል ታሳልፏቸዋላችሁ። በጣም ጥሩ። በጣም ጥሩ። አሁን እኔ...

461 ሰንቶቻችሁ ትጥቃችሁን ታጥቃችኋል?

462 (ሌላ ሆናችሁ ትሄዳላልችሁ። ተፈውሳችሁ፡ ተሽላችሁ፡ ወደ ቤታችሁ ሂዱ።)

463 አሜን። ኦህ፡ ማይ! ሰራዊት ሆይ፡ ሁላችሁም ሰይፋችሁን ምዘዙ አሁን። ሰይፉን ምዘዙት። የመሰቀል ሰራዊት ሆይ፡ ዝመቱ፡ ዝመቱ።

በጽኑ ዓለት፡ በክርስቶስ ላይ፡ ቆሜአለሁ።
ሌሎች ሁሉ የሚሰምጡ አሸዋዎች ናቸው።

464 እሺ፡ እዚህ ጎን ወደ ታች፡ ወደዚህ ኑ። አሁን እያለፋችሁ፡ ሁላችሁም በጸሎት ሁኑ።

በኢየሱስ ስም ይህችን ሴት ፈውስ። አሜን።

ሰይፋችሁን ምዘዙት አሁን። እልል እያላችሁ፡ ወደየ ስፍራችሁ ተመለሱ።

465 [ወንድም ብራንሃም ለብዙ ሰዎች መጸለዩን ቀጥሏል፣ ብዙዎቹ ቃላቶቹ የማይሰሙ ናቸው።—አርታዒ።]... ? ...

ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት!
ወደ ሰልፍ እየዘመተ፡
የኢየሱስ መሰቀል
ከፊቱ እንደያዘ።

466 ዞር በል፡ ሰይጣን! ሰራዊት ሆይ፡ ምንድነው? ማሸነፍ የምንችል አይመስላችሁምን? እሱ ቀድሞ ተሸንፏል። በክርስቶስ ኢየሱስ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን! ዲያቢሎስ ሁሉ፡ እና ሌላው ሁሉ ይጣላል። አሜን።

ወደዚህ ኑ፡ ወንድሞቼ!... ? ...

እንድትፈወሱ እጸልያለሁ... ? ...

ወንድሜን፡ ዶክተርን ፈውሰው፡ አባት ሆይ፣ በኢየሱስ ስም፡ ፈውሰው።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህችን ሴት ፈውሳት። ነይ... ? ...

467 አሁን፡ ወሰዶታል... ከኋላ ያሉትን ወንድሞች ልጠይቅ። በሁሉም ቦታ፡ ጌታ... ? ...

468 አቤቱ አምላክ፡ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ሆይ! አምላክ ሆይ፡ በልቧ ያለውን ታውቃለህ። አንተ ሁሉንም ታውቃለህ። ለእናት እና ለአባት ለሁለቱም እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ አቀረብኳቸው... ? ...

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ እ... ? ...

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ እ... ? ...

469 እግዚአብሔር፡ ከእህቴ ጋር ይሁን። የሴቲቱን አካል ለመያዝ ሞትም እንዲወስዳት አመታት ወደ ውስጥ ዘልቀው መግባት እንደጀመሩ፡ እናውቃለን። አሁንም፡ በኢየሱስ ስም... ? ...

470 በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ጌታ፡ ይህችን ህጻን ልጅ ይባርክ። ትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ያሉ ውጊያዎች፡ በምን እንዳለፈች አውቄአለሁና። እንድትባርካት እጸልያለሁ። ዛሬ ጠዋት፡ ሰይፍ መዛ፡ ወደፊት ትመርሽ!... ? ... ጌታ ሆይ፡ ይህን ህጻን ልጅ ባርክ፡ ሰምህን እየጠራ፡ ቀርቧልና፡ ዛሬ ጠዋት፡ አብረኸው እንድትሆን እጸልያለሁ... ? ...

471 እግዚአብሔር ሆይ፡ ወንድሜ ልመናውን ሰጠው። በጌታችን በኢየሱስ ስም፡ ተናገርኩ!... ? ...

ይህንን ጸሎት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናቀርባለን።

ይህንን ጸሎት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናቀርባለን።

ይህንን ጸሎት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናቀርባለን።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እናቀርባለን… ? …

ይህንን ጸሎት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናቀርባለን።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም… ? …

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም… ? …

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ወንድሜን ፈውስ።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም… ? …

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም!

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም!

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም!

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም!

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም!

472 [አንድ ሰው፡ "አባቷ ሞቷል" አለ። አርታዒ።] አምላክ ሆይ፡ እርዳት፡ በኢየሱስ ስም።

እግዚአብሔር ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ጸለይን… ? …

እግዚአብሔር ሆይ፡ በኢየሱስ ስም!

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም… ? …

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ወንድሜን ፈውስ።

በኢየሱስ ስም… ? …

አሁን ገባችሁ?

አምላኬ ሆይ፡ ይህ ከዚህ ይራቅ… ? …

473 በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንጸልያለን!… ? … እህታችንን ዳሰሰ… ? …

474 አምላክ ሆይ፡ ያቺን ውድ ታናሽ እናት፡ በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ መሆኗን አውቄ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ አንተው፡ ታደጋት… ? … እጸልይላታለሁ።

ሰይፉን ምዘዘው፡ ኤድ፡ ወደፊት መርሽ፣ በኢየሱስ ስም።

475 አቤቱ፡ ሴቲቱን ፈውሳት። ጥያቄውን ሰጠው። በጭንቅ ጊዜ፡ ሰይፉን በፊቱ ይምዘዝ።

እግዚአብሔር ሆይ… ? … ዛሬ ጠዋት። እንድትሰራ እጸልያለሁ… ? …

476 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ወንድማችንን እንድትፈውሰው እና እንዲድን እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም… ? …

477 እግዚአብሔር ሆይ፡ እህታችንን እንድትፈውሳት፡ እንድትድን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጸልያለሁ።

478 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ወንድማችንን—እንድትፈውሰው እጸልያለሁ።

እህታችንን ፈውስ፡ ጌታ ሆይ!… ? …

አባት ሆይ፡ በኢየሱስ ስም፡ እህታችን፡ አባት ሆይ፡ ፈውሳት።

479 አባት ሆይ፡... ? ... በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አምላክ ሆይ፡ ይህችን ሴት ፈውሳት።

አምላክ ሆይ፡ ወደ አንተ እጸልያለሁ... ? ...

480 አምላክ ሆይ፡ ባርከው፡ አባት ሆይ!... ? ... ጌታ ሆይ፡ አብረውን የቆዩ ሰዎችን እንዴት እንደምንወዳቸው። ጥያቄውን እንድትፈጽም እጸልያለሁ!... ? ...

481 የሰማይ አባታችን፡ ስለ ወንድሜ እጸልያለሁ... ? ... አምላክ ሆይ፡... ? ... እርሱን፡ እግዚአብሔር ሆይ... ? ... የመስቀል ወታደር። ዛሬ ጠዋት፡ ሰይፉን መዝዞ፡ ይመርሻልና።

እግዚአብሔር፡ ጌታ ሆይ... ? ... ልመናውን፡ ሰጠው፡ እንላለን።

482 እግዚአብሔር ወንድማችን ይባርክ... ? ... እንድትፈውሰው እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ! ... ? ... የልቡን መሻት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰጠው።

483 የሰማይ አባት ሆይ፣ ይህ ታናሽ የወንጌል አገልጋይ፣ ጉሮሮውን አሰብ... ? ... የታጠበችባቸው ያንን... ? ... አምላክ ሆይ፡ ፈቃድህ ይሁን... ? ... እናም ታላቁ የእግዚአብሔር ሰራዊት፡ ሰይፎች ወደ ላይ ተነሥተው ወደ ፊት እየገሰገሰ ሳለ፡ ጌታ ሆይ፡ ድልን ሰጣት። ምስኪን ባሏም፡ ጌታ ሆይ፡ ተኝቶ ከሚሞትበት፡ ከተኛበት ከካንሰር አልጋ ወደዚህ መጥቷልና፡ ዶክተሮቹ ጋር ቢሄድም፡ ተስፋ ቆርጠውበታል። ዛሬ ጠዋት፡ እንደ መስቀል ሰራዊት፡ እዚህ ተገኝቷል። ለሥራህ፡ አበረታው፡ ጌታ ሆይ፡ በኢየሱስ ስም፡ እንጸልያለን።

484 ያቺ ምስኪን ሴት እፈልጋታለሁ... ይህ ምስኪን ሰባኪ ሌላ ነገር አለው። እዚህ ና፡ ወንድም ኪድ። ይህ ሰው በቅርቡ በካንሠር ተበልቶ ሊሞት ተቃርቦ፡ ከሆስፒታል ወደ ቤቱ፡ የተላከ ሰው ነው። [እህት ኪድ "ከአንድ አመት በፊት፡" አለች፣—አርታዒ።] ከአንድ ዓመት በፊት። ["ሁለት።"] ከሁለት ዓመት በፊት፡ ከፕሮስቴት ጋር። ሐኪሙ ለመኖር ጥቂት ቀናት ብቻ ሰጠው። እና አንድ ቀን ጠዋት፡ ማልደን፡ ወደዚያ ወጣንና፡ እንደ አንቺ፡ ለእሱም ጸለይን፣ ከዛ በኋላ አሻራውን እንኳን አላገኙትም። ተፈወሰ። አሜን። እሱ—እሱ... ["መቀበል ነበረበት።"] አሁን ከነበረው የበለጠ ክብደት ጨምሯል። እሱ እና ምስኪኗ ሚስቱ በወንጌል መስክ፡ ምናልባት ከመወለዴ በፊት ነበሩ። አሁንም እዚህ አለ... [ወንድም ኪድ "ኃምሳ-አምስት አመታት አለ።"] ኃምሳ-አምስት አመታት። እኔ ወደ ምድር ከመምጣቴ በፊት፡ ወንጌልን ይሰብኩ ነበር። እና እነሆ፡ አሁንም፡ በሰባ-አምስት ዓመቱ ተፈወሰ፡ ወይም፡ ["ሰማንያ-አንድ።"] ሰማንያ-አንድ። ["የሁለት ሳምንት፡ ሪቫይቫል ሰብሰባ፡ በየምሽቱ አካሄድን።"] የሁለት ሳምንታት ሪቫይቫል፡ ልክ የሁለት ሳምንት ሪቫይቫል ተካሄደ፡ እና በየምሽቱ ይሰበክ ነበር። በሸመገለ፡ በሰማንያ-አንድ ዓመቱ፡ ከካንሰር፡ ተፈወሰ።

485 እሺ እህቴ፡ አሁንም፡ የአንቺ ጊዜ ነው። ታምኛለሽ? **ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት**። በጣም ጥሩ፡ እህቴ። እናንተ፡ ለሁላችሁ፡ ምን እናድርግ? **የሰራዊት ጌታ እግዚ አብሔር እንዲህ ይላል**። ምን እናድርግ፡ እዚህ እንንከራተት?

486 ሰይጣን፡ አለቀልህ። አሁን መጣን። ወደ ተስፋይቱ ምድር እንመርሻለንና። ምንድነው? "ይህ ተራራ በዘሩባቤል ፊት ምንድነው? በፊቱ የሚቆመው፡ ይህ

ምንድነው? ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ።" ለምን? በባለ ሁለት-አፍ ሰይፍ ወደ መሬት እንቆርጣታለን። ትክክል ነው። በጣም ጥሩ።

ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት!
ወደ ሰልፍ እየዘመተ፡
የኢየሱስ መስቀል
ከፊቱ እንደያዘ፡
ክርስቶስ፡ የነገሥት አለቃ፡
በጠላት ላይ ይመራል፡ (በቃሉ።)
ወደ ጦርነት ወደፊት፡
ዓላማው ሲመርሽ፡ ታየ!

ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት!
ወደ ሰልፍ እየዘመተ፡
የኢየሱስ መስቀል
ከፊቱ እንደያዘ።

487 ሃሌ ሉያ! ምን አደረጉ? በጦርነት፡ ከፊት የወጣ ነገር፡ ለእስራኤል፡ ፊተኛው ነገር ምን ነበር? መጀመርያ ዘማሪዎች ይቀድማሉ። ማን ይከተላል? የቃልኪዳኑ ታቦት። ከዛ በኋላ ውጊያው ይጀመራል። እሺ። አሁንስ ታምናላችሁን? **ዘማች፡ ክርስትያን ሰራዊት፡** እንዘምራለን። አሁን ተነሰተን ቆመን፡ ውደ ሰልፍ እየመረሽን፡ ጥርጣሬዎችን ሁሉ እናስወግዳለን።

አሁን፡ ሁላችንም እንቁም።

ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት!
ወደ ሰልፍ እየዘመተ፡
የኢየሱስ መስቀል
ከፊቱ እንደያዘ፡
ክርስቶስ፡ የነገሥት አለቃ፡ ከፊቱ እንደያዘ፡
በጠላት ላይ ይመራል፡

በምን እናሸንፈዋለን? በቃሉ።

ወደ ጦርነት ወደፊት፡
ዓላማው ሲመርሽ፡ ታየ!

ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት!
ወደ ሰልፍ እየዘመተ፡
የኢየሱስ መስቀል
ከፊቱ እንደያዘ።

አንከፋፈልም፡
ሁላችንም አንድ አካል፡
በአንድ ተስፋ እና ትምህርት፡
ሌላውም በፍቅር።

488 አሁን የሚያምኑት ሁሉ፡ "አሜን፡" ይበሉ። [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ሃሌ ሉያ! ድል ነሺዎች እንደሆንን። ታምናላችሁ? ጠላት ሁሉ የት አለ? ከእግራችን በታች። እኛስ ዛሬ ምንድነን? በክርስቶስ የተነሡ ነን!

489 አሁን፡ አልቋል እህቴ። ታምኛለሽ? አሁን ወደ ቤትሽ ሂጂ። ጤንነት ተሰምቶሻል? ጤና ተሰምቶኛል ብላለች። ሁሉ ደህና ነው።

490 ስንቶቻችሁ ጤና ተሰምቷችኋል? በጮኹ ጊዜ፡ ግንቡ ፈረሰ፡ አሜን፡ ወረሱ። አሜን። ከተማዋን ወሰዱ። አሜን! አሜን! ታምኑታላችሁ?

491 አሁን፡ የምሽቱን አገልግሎት እንዳትረሱ። ወንድም ኔቪል ዛሬ ማታ ይመጣል፡ ጥሩ መልእክት ያመጣልናል። እና እሁድ፡ በሚቀጥለው እሁድ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ እዚህ እገኛለሁ።

492 አሁን እንደጀመርነው፡ እንቀጥል። አሁንም፡ ከህንጻው ሰንወጣ፡ **ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት**፡ እየዘመርን፡ እንሂድ። እና ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ ከአሁን በኋላ፡ ሰይፉን ወደ ሰገባው በጭራሽ አይገባ። ምዘዙት። ድል እንንሳ። “ድል ሊነሱ፡ ድል እየነሱ፡ ወጡ።” እሺ፡ እንደገና፡ ወደ አንደኛው ቁጥር።

ዘማች፡ የክርስትያን ሰራዊት!
ወደ ሰልፍ እየዘመተ፡
የኢየሱስ መሰቀል
ከፊቱ እንደያዘ።

**የውጊያዎች ሁሉ አውራው ውጊያ** AMH62-0311

(The Greatest Battle Ever Fought)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሁድ ጠዋት፡ መጋቢት 11፡ 1962፡ በጀፈርሰንቪል ኢንዲያና፡ ዩ.ኤሰ. ኤ.፡ ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጒሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org